# ነብዩ ሙሐመድ

# የእዝነቱ ነብይ

በኡስማን ኑሪ ቶፐባሽ

ተርጓሚ፡ ሙኒራ አብዱልመናን

አርታኢ፡ ሐሰን ታጁ

አሳታሚ፡ አልበያን ሊሚትድ

ስልክ ቁጥር፡ 0913878788 ወይም 0911051025

የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው

All rights are reserved

አንደኛ እትም ሚያዝያ 2004

AFKAD 11

Addis Ababa Ethiopia

First Edition April 2012

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

**መቅድም ..................................................5**

**የዓለማችን ኩራት ..............................................7**

የእዝነቱ ነብይ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)........................................7

አለምን እንዴት እንዳላቃት ...................................................8

**ምእራፍ ሁለት ..............................................34**

**ምሳሌ የሆነው የነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) አኗኗር........................34**

ነቢያችን በጣኦታውያን አመለካከት .......................................46

**ምእራፍ ሶስት ..............................................55**

**የእዝነቱ ነብይ ምርጥ ባህሪያት ....................................55**

የእዝነቱ ነብይ የውስጥ ንፅህና (የነፍሲያቸው ጥራት) ................56

የእዝነቱ ነብይ መተናነስ ........................................................72

ፍቅር፣ እንክብካቤና ስነ ምግባር በእዝነቱ ነብይ (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት ውስጥ..........................................................................79

ከሠዎች ጋር የነበራቸው ግንኙነት.........................................84

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ለድሆችና ለተቸገሩ ሰዎች ያሳዩ የነበረው ደግነት ..........................................................................88

ሰዎች በነብያችን ትምህርት ያገኙት ሂደታዊ ለውጥ ..................97

ከሴቶች ጋር በተያያዘ የነብያችን ባህሪ...................................100

ከእንሰሳት ጋር በተያያዘ የነብዩ ባህሪ ....................................101

የነብዩ እዝነት ለወላጅ አልባዎች...........................................105

ነቢዩ ለጎረቤት መልካም መሆንን አስመልክተው ......................106

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የወንጀለኞችና የምርኮኞች አያያዝ .............107

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ከኢስላም ጠላቶችና ሙስሊም ካልሆኑ ወገኖች ጋር በተያያዘ የነበራቸው ባህሪ ........ 109
የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይቅር ባይነት ........ 110
የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለጋስነት........ 114
የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ለጋስነት........ 115
የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሀቀኝነት፣ ታማኝነትና ግብረገብነት ........ 118
የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አይን አፋርነት ........ 120
የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ከራስ ወዳድነት የፀዳ ባህሪ ........ 121
ታማኝነታቸውና ውለታ ከፋይነታቸው ........ 125
**ማጠቃለያ** ........ 131

# መቅድም

ሁሉም የቁርአን ምእራፎች የሚጀምሩት «በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው» በሚል ሃረግ ሲሆን ይህ ሃረግ ኢስላም የእዝነት ሐይማኖት መሆኑን ያጎላል። አላህ የነቢዩ ሙሐመድን ተልእኮ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا رَحۡمَةٗ لِّلۡعَٰلَمِينَ ١٠٧﴾ الأنبياء: ١٠٧

*«ለአለማት እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም»*(አል-አንቢያ፡ 107)

ነቢዩ ሙሐመድ እንዲህ ብለዋል፡-

«ለሌሎች የማያዝን አላህ ለርሱ አያዝንለትም።»

«ከናንተ አንዳችሁ ለራሱ የሚወደውን ለ(ሰብአዊ) ወንድሙ እስካልወደደ ድረስ አላመነም።»

«ጎረቤቱ ተርቦ እያለ እርሱ ጠግቦ ያደረ አማኝ አይደለም።»

እነኝህና ሌሎች እጅግ በርካታ ቁርአናዊና የነቢዩ አባባሎች ኢስላም የእዝነት ሐይማኖት መሆኑን ያጎላሉ። የኢስላም እዝነት ለሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን ለአጠቃላይ የሰው ልጆች፣ከሰው ልጆችም አልፎ ለእንስሳት ጭምር ነው።

የኢስላም አብይ ስብእና የሆኑት ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ዋነኛ መገላጫቸው ከላይ በሰፈረው ቁርዓን አንቀፅ እንደተመለከተው እዝነት ነው። የሰው ልጅ እርስ በርስ በመጨካከንና በመበላላት ከአውሬዎች አንኳ እጅግ በልጦና ብሶ በተገኘበት በዚህ ዘመን የኢስላም የእዝነት እስትንፋስ፣ የነብያት ፈርጥ የሆኑት የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የእዝነት ትምህርትና ምሳሌ ከአየርና ከውሃ የበለጠ በእጅጉ

ያስፈልገዋል፡፡
ይህ መፅሐፍ ከእኚህ ታላቅ ስብእና ዘርፈ ብዙ አንፀባራቂ ባህያት መካከል በዚህ አጀንዳ ላይ ብቻ በማተኮር ጥቂት ብርሀን ለመርጨት ይሞክራል፡፡

ደራሲው ቱርካዊው ሼኽ ኡስማን ኑሪ ቶፕባሽ ነብዩን እንድንወድና እንድናደንቅ በሚያደርጉ እጅግ መንፈሳዊ በሆኑ ስራዎቻቸው ብዙ ጠቅመውናል፡፡ በዚህች መፅሐፍም ለነብዩ ያለንን ፍቅር ይበልጥ ይጨምሩልናል፡፡

የመጽሐፏ ተርጓሚ እህት ሙኒራ አብዱልመናን የመጀመሪያ የትርጉም ስራዋ ይህች መጽሐፍ ብትሆንም እንደ ጀማሪ ተርጓሚ ሳትንገዳገድ ይበል በሚያሰኝ አኳኋን ተርጉማልናለች፡፡ አላህ ብዕሯን ይባርክላት፡፡ ተጨማሪ ስራዎችን ታስነብበን ዘንድም ብርታቱን ይለግሳት፡፡

ሐሰን ታጁ

ሚያዝያ 2004

# ምዕራፍ አንድ

# የዓለማችን ኩራት

## የእዝነቱ ነብይ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)

⇒ ለሠውም ሆነ ለጅኖች አለም ዕዝነት በሆኑት ምርጡ ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ላይ የአላህ ሰላምና እዝነት ይውረድ።

⇒ ለሠውም ሆነ ለጅኖች ዓለም መልዕክተኛ በሆኑት ምርጡ ነብዩ ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ላይ የአላህ ሠላምና እዝነት ይውረድ።

⇒ የሁለቱ ቅዱስ መስጂዶች (መካና መዲና) ኢማምና ኸጢብ በሆኑት ውዱ ነብይ ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ላይ የአላህ ሠላምና እዝነት ይውረድ፡

⇒ የሁሴንና የሀሠን አያት በሆኑት ውዱ ነብይ ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ላይ የአላህ ሠላምና እዝነት ይውረድ፡

የልዕልና ባለቤት የሆነው አላህ (ሡ.ወ) አለማችንን ማብቂያ በሌለው እዝነቱ አካቧታል። የእርሱ ፍቅርና እዝነት ውጤት የሆነውን የሠውን ልጅም ከየትኛውም ፍጡር በላይ ከፍ አድርጎታል። አላህ (ሡ.ወ) የሠው ልጅን የዚህ ታላቅ ስፍራ ባለቤት ለመሆን የሚያስችሉትን ባህሪያት አላብሶታል።

ይህን ትልቅ ስፍራ ለማስጠበቅ እና ቡራኬውን ዘልአለማዊ ለማድረግ ለሠው ልጅ ተጨማሪ ስጦታ ሠጥቶታል። ይህም በመልዕክተኞቹና ነብዮቹ አማካኝነት መመራት ነው። በዚህም እጅግ ፍፁም ወደ ሆነው የአላህ መንገድ ያቃርበዋል። የዚህ ስጦታ ጣሪያው ደግሞ የነብያት መደምደሚያ የሆኑት የነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ብርሀን ነው። የነብዩ ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ወደዚች ምድር መላክ ለመላው የሠው ዘር ስጦታ ነው።

# አለምን እንዴት እንዳላቃት

ከፍጡራን ሁሉ የላቁ የሆኑት ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ወደዚች ምድር የመጡት በሠኞ ንጋት ረቢአል አወል 12 ነበር፡፡

ከሳቸው ውልደት ጋር የአላህ እዝነት አለምን አጥለቀለቃት፡፡ የንጋትና የምሽት ቀለማት ተለወጡ፣ ስሜቶች ጥልቅ ሆኑ፡፡ እያንዳንዱ ነገር አዲስ ትርጉምና አዲስ ደስታ ፈጣሪ ሆነ፡፡ ጣኦታት ተንኮታኮቱ፡፡

የዒራን ንጉስ ግዛት ቤተ መንግስትና ማማዎች ፈራረሱ፡፡ የሳቫ ሀይቅ ውሀ አቅጣጫውን በመቀየሩ ሀይቁ ሙሉ ለሙሉ ደረቀ፡፡ የጭቆና ስሮች ተነው መጥፋት ተያያዙት፡፡ ልቦች በመለኮታዊ ቡራኬና ሀዘኔታ ተሞሉ፡፡

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አባት ለንግድ ወደ ደማስቆ ተጉዘው ነበር፡፡ወደ ቤት በመመለስ ላይ እያሉ መዲና ሲደርሱ ልጃቸው ከመወለዱ ከሁለት ወራት በፊት ህይወታቸው አለፈ፡፡

በአረቦች ባህል መሠረት ይህ ውድ ህፃን ከጡት እናቱ ሀሊማ ጋር ለአራት አመታት ቆየ፡፡

ይህ የተባረከ ህፃን 6 አመት ሲሞላው አሚና የባሏን ቀብር ለመጎብኘት ህፃን ልጇን እና የቤተሰቡን አገልጋይ የነበረችውን ኡሙ አይመንን ይዛ ወደ መዲና ተጓዘች፡፡ አሚና በመንገድ ላይ ህመም አጋጠማት፡፡ ከቆይታ በኋላም አብዋ በተባለች ስፍራ ህይወቷ አለፈች፡፡

ገጣሚው እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፡-

የአለም ምርጧ አበባ ዛሬ ተለየችን

በአብዋ ከተማ ተሰናበተችን

የፈካች ነበረች አሚና ውዳችን

ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ወላጅ አልባ ሆነው ከኡሙ አይመን ጋር ወደ መካ ተመለሱ፡፡ በ8 አመታቸው አያታቸው አብዱል ሙጠሊብን አጡ፡፡ ብዙም ሳይቆይ መከታቸው የሆኑትን አጎታቸውን አቡጧሊብን በሞት አጡ፡፡ ከአጠገባቸው ያሉ አለኝታና ዘመዶቻቸውን በሙሉ በጊዜ ተነጠቁ፡፡ ከዚያ በኋላ ብቸኛው ተንከባካቢያቸው ጌታቸው ብቻ ሆነ፡፡ የሚታዩና አጠገባቸው ያሉ ተንከባካቢዎችን ማጣታቸውና አላህ ብቻ የቀራቸው መሆናቸው ለመላው የሠው ዘር ምሳሌ ያደርጋቸዋል፡፡

የልጅነትና የወጣትነት ጊዜያቸው በከፍተኛ ግብረገብና ያለምንም አይነት ህግን የጣሠ ተግባር ማለፍ ከትልቅ ቦታ የሚደርሱ ሠው ለመሆናቸው ማሣያ ነበር፡፡

25 ዓመት በሞላቸው ጊዜ ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ኸዲጃን (ረ.ዐ) አገቡ፡፡ ኸዲጃ (ረ.ዐ) እጅግ የተከበረችና የአረብ ጎሳዎች መሪ የሆነው የቁረይሽ ዝርያ ነበረች፡፡ አስተዋይዋ ኸዲጃ (ረ.ዐ) የነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ድጋፍ ሆነች፤ በንብረቷና በህይወቷ ነብዩን አገለገለች፡፡ ኸዲጃ (ረ.ዐ) ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) 15 አመት የምትበልጥ፣ ባሏ የሞተባትና ልጆች ያሏት ነበረች፡፡ ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ከሷ ጋር በነበራቸው ያማረ ግንኙነት ለድፍን አለም ምሳሌ ለመሆን በቅተዋል፡፡

ነብዩ ብቻቸውን ለትግል በተጋለጡበት ወቅት የመጀመሪያዋ ደጋፊቸው ኸዲጃ ነበረች፡፡ ለምሳሌ ነብዩ በሂራ ዋሻ በመጀመሪያው መለኮታዊ መልዕክት ከአላህ በተጣለባቸው ከባድና ሠፊ ሃላፊነት ደንግጠው ወደ ቤታቸው ወደ ኸዲጃ በመመለስ፡-

"ሐዲጃ ሆይ ከቶ ማን ያምነኛል? ሲሉ ጠየቁ"  ይህች የተባረከች ሚስት ግን ይህን ስትል መለሰች።

"አላህ ፈፅሞ አይተውህም፤ ዘመዶችህን ትንከባከባል፣ የኑሮ ጫናን መቋቋም ላቃታቸው ሸክማቸውን ትችላለህ፣ ለድሆች ትደርሳለህ፣ ለእንግዶች ደግ ነህ፣ ሠዎች በቀጥተኛ መንገድ ላይ ለሚያጋጥማቸው ችግር ሁሌም ትረዳቸዋለህ። የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እኔ እቀበልሀለሁ፤ አምንብሀለሁም፣ ወደ አላህ መንገድ በመጀመሪያ ጋብዘኝ።[1]

ኸዲጃ (ረ.ዐ) የመጀመሪያዋ አማኝና የመጀመሪያዋ ደጋፊ ነበረች። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ጥልቅ የሆነ ፍቅሯን፣ ስርአቷንና ደግነቷን መቼም ረስተው አያውቁም። ከሞተች በኋላም ቢሆን ለቤታቸው እርድ በፈፀሙ ቁጥር ስጋ ወደ ቤተሰቦቿ ይልኩ ነበር።[2]

ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ኸዲጃን (ረ.ዐ) ረስተው አያውቁም። የመጀመሪያ የትዳር 24 ዓመታቸውን፣ የወጣትነትና የጉብዝና ጊዜያቸውን ያሳለፉት ከኸዲጃ (ረ.ዐ) ጋር ብቻ ነበር። ከኸዲጃ (ረ.ዐ) በኋላ ያገቧቸው ሚስቶችም በአብዛኛው ባለቤታቸው የሞቱባቸውና ከሳቸው በእድሜ የሚበልጡ ነበሩ። ብቸኛዋ ወጣትና ልጃገረድ ሚስታቸው አይሻ (ረ.ዐ) ነበረች። አይሻ ስለ ሴቶችና ሀይማኖታዊ ጉዳዮች ከፍተኛ በሆነ የአእምሮ ብቃት መረጃዎችን ሠብስባለች። ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሞት በኋላም ወንዶችንና

---

[1] ቡኻሪ፣ ዘካት 1 ሙስሊም ኢማን 12 ነሳኢ ሠላት 10 አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠናድ ቅፅ417-418

[2] ሙስሊም ፋዲል አል-ሠሀባ 75 ኢብን ሂባን አል-ሠሂህ XV፡467

ሴቶችን ሠብስባ ይህን እውቀቷን ታካፍል ነበር፡፡ ይህም ለቀጣዮቹ ኢስላማዊ አስተሳሰቦች መሠረት ለመሆን ችሏል፡፡

ለዚህም እንደ ምስክርነት አቡ ሙሳ አል አሻሪ የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ዋንኛ ወዳጅ (ሠሃባ) ይህን ይላሉ፡-

“እኛ የረሱል (ሠ.ዐ.ወ) ወዳጆች ስለማንኛውም ሀዲስ ጥያቄ በኖረን ጊዜ አይሻን (ረ.ዐ) እንጠይቅ ነበር፡፡ እናም ምንጊዜም አጥጋቢ መልሶችን እናገኝ ነበር፡፡”

ሌላው የዚህ ጋብቻ ምክንያት የነብዩንና የአቡበከርን (ረ.ዐ) ወዳጅነት ለማጠናከር ነበር፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ንፁህ ከነበረ የወጣትነት ጊዜና የተረጋጋ ቤተሰባዊ ህይወት በኋላ በ40 አመታቸው ነበር ለነብይነት የተመረጡት፡፡ ለ40 ዓመት 6 ወራት ሲቀራቸው አላህ (ሡ.ወ) በመካ የሚገኘው ሂራ ዋሻን ለመለኮታዊ መማሪያነት ከፈተላቸው፡፡

በዚህ መንፈሳዊ የመማሪያ ስፍራ፣ ቅዱስ የሆነው ትምህርት ቀጠለ፡፡ በአርባ አመታቸው ሠዎችን የመምራት ብቃትና የነብይነት ማረጋገጫ ተሰጣቸው፡፡

﴿ ٱقْرَأْ بِٱسْمِ رَبِّكَ ٱلَّذِى خَلَقَ ۝١ خَلَقَ ٱلْإِنسَٰنَ مِنْ عَلَقٍ ۝٢ ﴾ العلق: ١ - ٢

‹‹አንብብ. በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም›› ‹‹ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)፡፡›› **(ዐል-አለቅ፡ 1-2)**

ከተመረጡም በኋላ የመጀመሪያዎቹ 6 ወራት ቅድስናውን የሚያስተነትኑባቸው ነበሩ፡፡ በሂራ የተዘራው ለመላው የሠው ዘር የሚበጅ መለኮታዊ መልዕክት እስከ አለም መጨረሻ የሚቆይ ነው፡፡ ነብዩን (ሠ.ዐ.ወ) ወደዚህ የመራቸው ለሠው ልጆች የነበራቸው ጥልቅ ፍቅር እንደዚሁም ለነበሩበት ማህበረሰብ የዘቀጠ የህይወት መስመር የነበራቸው ጥልቅ ሀዘኔታ ነው፡፡ በነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ንፁህ ልብ አማካኝነት

ሰማያዊው ቁርዓን ለሰው ልጆች ቅርብ ሆነ፡፡ ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ተራ ሰው ሊሸከመው የሚከብደውን ሃላፊነት ተሸከሙ፡፡ ልክ የከርሰ ምድር ብረት ወደ ጠቃሚና አብረቅራቂነት ለመለወጥ እንደሚያልፈው ሂደት ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በሂራ ዋሻ በሚያገኙት መለኮታዎ መልዕክት ሂደትን አለፉ፡፡ ይህንን ተዓምር አይቶ መቀበል የማይችል አእምሮ ማግኘት እጅግ ከባድ ቢሆንም ወደ ዚህች ምድር ሚስጥር በልባቸው አማካኝነት መመልከት በማይችሉት፣ ማስተንተን ባቃታቸውና በመካ ዋንኛ የኢስላም ጠላት በሆኑት አቡ ለሀብና አቡ ጃህል ጨለማ ጥላ ስር ያደሩ ሠዎች ፈፅሞ ሊረዱት አልቻሉም፡፡[3]

የነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት በመለኮታዊ መልዕክቶችና ክብር የተሞላ ነበር፡፡ የትኛውም ነብይ ከነበረው ክብር በላይ አላህ (ሱ.ወ) ክብር አጎናፅፏቸዋል፡፡ ልዑሉ አላህ (ሱ.ወ) ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) በብቸኝነት ተወዳጁ ሲል ጠርቷቸዋል፡፡ የሚዕራጅን (ወደ አላህ የተደረገ መለኮታዊ መነሳት) ክብርንም ሠጥቷቸዋል፡፡ ቀደምት ነብያትን በሙሉ በእየሩሳሌም ከሚእራጅ በፊት በመሪነት ሲያሠግዱ ታላቅነታቸው ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም አላህ (ሡ.ወ) በቁርአኑ ከነብያት ሁሉ ለሡ ቅርብ መሆናቸውን እንዲህ ሲል ያስተምረናል፡፡

﴿ ثُمَّ دَنَا فَتَدَلَّىٰ ۝٨ فَكَانَ قَابَ قَوْسَيْنِ أَوْ أَدْنَىٰ ۝٩ ﴾ النجم: ٨ - ٩

‹‹ከዚያም ቀረበ፤ ወረደም፡፡ ፤ (ከእርሱ) የሁለት ደጋኖች ጫፍ ያህል ወይም (ከዚህ) ይበልጥ የቀረበ ኾነም፡፡››**(አል-ነጅም፡ 8-9)**

ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ለ13 ዓመታት ሠዎችን ወደ ቀጥተኛው መንገድ ሲጣሩ ከቆዩ በኋላ ወደ ሰውር ዋሻ ተሠደዱ፡፡ በዚህ ግዜ ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) የተጓዙበት ምክንያት ለትምህርት ወይም መለኮታዊ መልዕክት

[3] ቲርሚዝ፣ ሙናቂብ፡ 624

ሊወርድላቸው ሳይሆን የአላህን ሚስጥሮች እንዲገለፅላቸውና ልባቸውን ለማንፃት ነው። ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) በሰውር ዋሻ በነበራቸው ቆይታ ብቻቸውንም አልነበሩም። ከነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ቀጥሎ ታላቅ ስብዕናነታቸው ከተመሠከረላቸው አቡበከር ሲዲቅ (ረ.ዐ) ጋር ነበሩ። ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ለአቡበከር ይህን ብለዋቸው ነበር፡-

﴿ لَا تَحۡزَنۡ إِنَّ ٱللَّهَ مَعَنَاۖ ﴾ التوبة: ٤٠

‹‹አትዘን አላህ ከእኛ ጋር ነውና።›› **(አል ተውባህ 40)**

ቅዱስ ቁርአን በዚህ አንቀፅ ከአላህ ጋር መሆንና በአላህ መብቃቃትን ያስተምረናል።

ስለዚህም ሰውር ዋሻ ልብን ማስተማሪያ የመጀመሪያ ትምህርት ቤት ሆኖ እናገኘዋልን። እዚህ ላይ ነው ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ለአቡበከር በልባቸው ያለውን ሚስጥር ማካፈል የጀመሩት። ዘመን ተሻጋሪው ዘላለማዊው ወዳጅነትም እዚህ ነው የተወለደው። አቡበከር (ረ.ዐ) ነብዩን (ሠ.ዐ.ወ) አስከትሎ ያሥወጣቸው ፍቅር ነው። አዎ፣ በፍቅር ህግ መሰረት አንድን ሰው ከወደድን እርሱን ብቻ ሳይሆን እርሱ ሚወዳቸውን ነገሮች ጭምር እንወዳለን። ምናልባትም ይህን አይነቱን ፍቅር የኛ ደካማ አይምሮ ላይረዳው ይችላል።

በአንድ ወቅት ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ይህን ሲሉ ተናገሩ፡- "ከአቡበክር (ረ.ዐ) ንብረት እንደተጠቀምኩት ከማንም አልተጠቀምኩም" አቡበከር (ረ.ዐ) እንባ ባቀረረ አይን እየተመለከቷቸው ይህን መለሡ "እኔና ንብረቴ የእርሶ አይደሉምን"?[4]

---

[4] ኢብን ማጃህ፣ አህመድ ኢብን ሃንባል

ከዚህ ታሪክ ልቦቻችን ብዙ መማር ይችላሉ፡፡ ግን ይህ በልቦቻችን የመማር አቅም ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ አቡበክር (ረ.ዐ) ከነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ጋር በኖሩት ጥልቅ ሀሴት ተጎናፅፈዋል፡፡ እያንደንዷ እርምጃቸው ለነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) እና በነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) መንገድ ብቻ ነበር፡፡ ለምሳሌ፡-

በአንድ ወቅት ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ)፡- ‹‹ወታደሮቻችንን እርዱ›› አሉ፡፡ አቡበከር ያላቸውን ንብረት በሙሉ ይዘው መጡ፡፡ ነብዩም (ሠ.ዐ.ወ)፡- ‹‹ለቤተሰብህ እና ለልጆችህ ምን አስቀረህ?›› አሏቸው፡፡ አቡበከርም ፍፁም እምነትን በተሟላ አኳኋን "አላህንና ረሱልን (ሠ.ዐ.ወ)›› ሲሉ መለሡ፡፡[5]

መአዊያ ቢን አቡ ሱፊያን ስለ አቡበከር (ረ.ዐ) እንዲህ ሲል ይናገራል፡- "ይህች አዱንያ አቡበከርን አትፈልገውም፡፡ እሱም አይፈልጋትም" እዚህ ላይ መርሳት የሌለብን ነገር ግን ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) አቡበከር እንዲቸገሩም ሆነ እንዲደኸዩ ፈፅሞ አይፈልጉም ነበር፡፡ አቡበከር (ረ.ዐ) ሙሉ ንብረታቸውን ለኢስላም መስጠታቸውም ልዩ አጋጣሚ ነው፡፡ አቡበከርም (ረ.ዐ) ሆኑ ቤተሰባቸው በአላህ ላይ ከፍተኛ የሆነ መመካትና ትዕግስት ባለቤት ነበሩ፡፡

ወደ ሰውር ዋሻ ስንመለስ በዚህ ዋሻ ውስጥ የነዚህ ሁለት ምርጥ ሰዎች (የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እና አቡበከር (ረ.ዐ)) ጠባቂ፣ ተንከባካቢና ከለላ የነበረው የልዕልና ባለቤት የሆነው አላህ (ሱ.ወ) ነው፡፡ ጠላቶቻቸውም በሚፈልጓቸው ሠአት የዋሻው መግቢያ በሸረሪት ድር ተሸፍኖ ነበር የተመለከቱት፡፡ ይህ የተከሰተው በአላህ ፍቃድና ተአምር ሲሆን ረሡል (ሠ.ዐ.ወ) እና አቡበከር ከገቡ በኋላ ሸረሪት መጥታ መግቢያው በር ላይ

---

[5] ቲርሚዝ፣ ዳርሚና ሐኪም

ድር አደራችበት። በዚህም የተነሳ ከሀዲያን ከዋሻው ውስጥ ማንም እንደሌለ አስበው ተመለሱ።

አሪፍ ኒሀት አሲያ የተባለ ገጣሚ ክስተቱን እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፡-

ሸረሪቷ ያደራችው

ልቃቂቷን ያኖረችው

አይደል ከምድር ከሰማይ

እንጅ በከሃድያን ዓይን ላይ

እነዚህ ውድ የአለማችን ሠዎች በአላህ ጥበቃ ቁባ ከተሠኘች በመዲና አቅራቢያ የምትገኝ ስፍራ ደረሱ። በጉጉት ሲጠባበቃቸው የነበረው የመዲና ህዝብ በደስታ ተሞልቶ "ጠልአል በድሩ አለይና" "ሙሉ ጨረቃ ወጣችልን" በማለት ተቀበላቸው። ቀኑ ረቢአል አወል 12 ነበር። ከዚህች እለት ጀምሮ አዲስ አቆጣጠር (ሂጅራ) ተጀመረ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮም መዲና የኢስላም መናገሻ ከተማ ሆነች። ጨለማው ኩፍር (ክህደትም) ወደቀ። መዲና የሚገኘው የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) መስጂድም ሆነ የቁባ መስጂድ የዚህ የተቀደሰ ጉዞ ማስታወሻና የታሪካችን አንድ ክፍል ሆኑ።

የኢስላም ስጦታ የሆነው ቸርነትም በመዲና በከፍተኛ ሁኔታ ታየ። አንሷሮች (ረዳቶች) ለሙሀጂሮች (ለስደተኞች) ንብረታቸውን አካፈሉ÷ እንዲህ በማለት፡- "ይሄ ንብረቴ ነው። ግማሹ ያንተ ንብረት ነው። ግማሹ ደግሞ የኔ ነው" በዚህ መንገድ መዲና በኢስላም ታሪክ ላይ ሊሻር በማይችል ሁኔታ ተፃፈች። እንደ አዛን፣ ረመዳን፤ ኢድ እና ዘካ የመሳሰሉት ኢስላማዊ ትእዛዞች እና ስርአቶች የኢስላም አካል ሆኑ። ታላላቅ የኢስላም ጦርነቶችም የተካሄዱት በመዲና ነው። የኢስላም በክህደት ላይ የመጀመሪያውን ድል የተቀዳጀበት የበድር ጦርነትም የመዲና ውጤት ነው። ከበድር በኋላ ባህላዊው እና በጎሳ ላይ

የተመሰረተው መደጋገፍ እና ዝምድና በመንፈሳዊ ወንድማማችነት ተተካ።

ለምሳሌ አቡበከር (ረ.ዐ) ከሀዲ ከነበረ ልጃቸው ጋር ተፋልመዋል። አቡ ኡበይዳ ኢብን ጃራ (ረ.ዐ) ከአባቱ ጋር ፊት ለፊት የተጋጠመ ሲሆን፣ ሀምዛም (ረ.ዐ) ቢሆን ከወንድሙ ጋር ጎራዴ ለጎራዴ ተጋጥሟል። እኚህ ሰዎች ለእምነታቸው ሲሉ ከቅርብ የስጋ ዘመዶቻቸው ጋር ጦርነት ገጥመዋል። ምክንያቱም ዘመዳቸው ኢስላም፣ ወንድማቸው በ"ላኢላሀ ኢለላህ" የተሣሠራቸው ሠው ሆኗል። ከዚህም በተጨማሪ በበድር ፍልሚያ ላይ አላህ ተአምሩን አሳይቷል። ከሰማየ ሠማያት መልአክቶቹን ከአማኞች ጋር አብረው እንዲፋለሙ ልኳል። ከዚህም በኋላ ሁሉን አዋቂ የሆነው አላህ (ሡ.ወ) አማኞችን ከአጉል መኩፈስ እና በራስ መመካት ለመጠበቅ ሲል ይህን የቁርአን አንቀፅ አወረደ።

﴿ فَلَمۡ تَقۡتُلُوهُمۡ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ قَتَلَهُمۡۚ وَمَا رَمَيۡتَ إِذۡ رَمَيۡتَ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ رَمَىٰۚ وَلِيُبۡلِيَ
ٱلۡمُؤۡمِنِينَ مِنۡهُ بَلَآءً حَسَنًاۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ١٧ ﴾ الأنفال: ١٧

«አልገደላችኋቸውም ግን አላህ ገደላቸው፤ (ጭብጥን ዐፈር) በወረወርክም ጊዜ አንተ አልወረወርክም፤ ግን አላህ ወረወረ፤ (ወደ ዓይኖቻቸው አደረሰው)፤ ለአማኞችም ከርሱ የኾነን መልካም ጸጋ ለመስጠት (ይህን አደረገ)። አላህ ሰሚ ዐዋቂ ነውና።»**(አል አንፋል:17)**

በኡሁድ ጦርነት አንድ ታላቅ ሰው ተሠዋ። የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አጎት የሆነው ሀምዛ (ረ.ዐ)። በዚህ ጦርነት ሀምዛን ጨምሮ 70 ሠሀቦች በአንድ ጊዜ ተሰውተዋል። ለሀምዛ በተደጋጋሚ ዱዐ (ፀሎት) ይደረግለት ነበር። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለሀምዛ ከፍተኛና ጥልቅ የሆነ ፍቅር ነበራቸው። እንዲህም ሲሉ ይገልፁት ነበር፡- "ሀምዛ የልቤ አንድ አካል ነው።"

የኡሁድ ጦርነት ብዙ አስፈሪና ሠቅጣጭ ክስተቶችን ለሙስሊሞች አምጥቷል። በዚህ ፈተና ምክንያት ግን ሙስሊሞች በአላህ ላይ ያላቸው እምነት ጨመረ፣ የእስልምና አስተምህሮት አንድ አካል የሆነውን በአላህ

ምርጫ መስማማትና ሁሉን አድራጊነቱን ማመንን ተማሩ። በኡሁዱ ጦርነት ከተከሠተው የሠሀቦች ህልፈትና መሠዋት በተጨማሪም ምድርንና ሰማይን ያንቀጠቀጠ ክስተት ተፈጥሮ ነበር።

በነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ላይ በደረሰ ጥቃት ከጉንጫቸው አካባቢ ደሙ፣ ጥርሳቸው ተሰበረ። ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ደማቸውን በመጥረግ ወደ ምድር እንዳይወርድ ተከላከሉ። በእሳቸው ጉዳት የአላህ ቁጣ እንዳይከሰት በመፍራታቸውም ይህን ዱአ (ፀሎት) አደረጉ፡- "አላህ ሆይ÷ ህዝቤ ስላንተ ምንም አያውቅም እባክህን ምራቸው" [6]

ይህ ሀዲስ የሚያስረዳን፡-

"የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ደም ባፈሰሱት ሠዎች ላይ የአላህ ቁጣ ጨምሮ እንደነበር ነው" [7]

ይህን ሁሉ መደናገጥ ባስከተለው ኡሁድ ጦርነት ላይ እንኳን የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ይህን ይሉ ነበር፡-

"አንቱ የአላህ መልዕክተኛ በእርሶ አምነናል፤ ከአላህ ያመጡልንን መልዕክት (ቁርአን) ከልባችን ተቀብለናል። እርሶን እንደምንታዘዝና እንደምንከተል ቃልኪዳናችን ነው። የፈለጉትን ይበሉን፤ የፈለጉትን

---

[6] ቡኻሪ፣ አንቢያ 54፣ ሙስሊም፣ ጂሀድ 104፣ ኢብን ማጃህ፣ ፊታን 23፣ አህመድ ቢን ሀምበል፣ አል ሙስናድ፣ I፤ 380

[7] ኢብን ይስሀቅ ሲራ፣ ገፅ 311፣ አህመድ ቢን ሀንበል፡አል ሙስነድ፡ II 319፡ኢብን አቢ ሸይባህ፤ አል ሙሰነፍ፣ VII 373

ይዘዙን እኛ ከእርሶ ጋር ነን። እርሶን በላከልን አላህ ይሁንብን፤ ከባህር ቢሰምጡም አብረኖት እንሰምጣለን፤ ማንኛችንም አንቀርም...." [8]

የነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ይህን በሚናገሩበት ወቅት በከፍኛ የእምነት ምጥቀት ላይ ነበሩ።

በእርግጥ በኡሁድ ጦርነት የነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረቦች የረሱልን ትዕዛዝ በመዘንጋት ለምርኮ በመሻማታቸው አላህ ማስጠንቀቂያውን ላከ። ድሉንም አዘገየባቸው።

የኡሁድ ተራራ በነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ልብ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ነበረው። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የዕሁድ ተራራን እና የኡሁድ ሰማዕታትን መቃብር አዘውትረው ይጎበኙ ነበር። ይህንንም ይሉ ነበር፡- "እሁድን እንወደዋለን። እሱም ይወደናል።"[15] ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለእሁድ ያላቸውን ጥልቅ ስሜት ስለሡ ደጋግመው በመናገር አዘውትረው በመጎብኘት ይገልፁ ነበር።

በኻንዳቅ (የምሽጉ) ጦርነት ሶሀቦች ሁሉ ሞክረውት ያቃታቸውን ድንጋይ (አለት) ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) መስበር ችለው ነበር። በመጀመሪያው ስንዘራ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የ"ቄሳር" ቤተ መንግሥትን ተመለከቱ፤ በሁለተኛው የኪስራ (የፐርሺያው ንጉስ) ቤተ መንግሥትን ተመለከቱ ለሶስተኛው ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የሠንዓ (የመን) ቤተ መንግሥት ሲወድቅ መመልከታቸውን ተናገሩ። በነዚህ ሂደቶች በአማኞች ልብ ውስጥ ተስፋ አበበ። በየትኛውም የዓለም ዙሪያና ክፍል ሀቅ (ኢስላም) በውሸት

---

[8] ቡኻሪ፤ መጋዚ 4፣ ሙስሊም ጂሀድ 83፣ አህመድ ኢብን ሀንበል፣ አል ሙሠነድ I 389፣ 428፣ 457. ኢብን አቢ ሽይባህ፣ አል ሙሠናፍ VII፣6

(ክህደት) ላይ የበላይ እንደሚሆን ምልክት አገኙ። የማይቻል ብለው የሚያስቡት ሁሉ እንደሚቻል እያመኑ መጡ።

የኻንዳቅ ጦርነት ታላቅ ስቃይ፣ ድካም፣ ርሃብ፣ ውርጭና ጨለማ ነበረበት። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይህን ግዜ ዱአ ያደርጉ ነበር።

"ጌታዬ ሆይ! እውነተኛይቱ ሀገር አኺራ (ከሞት በኋላ) ናት። እባክህን አንሷሮችን (ረዳቶች)ን እና ሙሀጅሮችን (ስደተኞች)ን እርዳ!" [16]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በዚህ ዱአቸው ይህች አለም አላፊ መሆኗን፣ የዚህ ዓለም ስቃይና መከራ ከመጪዋ አለም (አኺራ) ጋር ሲነፃፀር ምንም እንዳልሆነ ያስረዱናል። በተከታዮቻቸውም (ለባልደረቦቻቸውም) አላማቸው መጪው ዓለም (አኺራ) እንዲሆን ያሥተምሩ ነበር።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በሁደይቢያ ስምምነት ጊዜ ሙስሊሞች ተከታታይ ጦርነቶችን እንደሚያሸንፉና የመካ ህዝቦችም ለከተማዋ ትክክለኛ ባለቤቶች (ሙሀጀሮች) እጃቸውን እንደሚዘረጉ ተናግረው ነበር።

በችግር ስቃይና ጭቆና ተውጣ የነበረችው መካ በሙስሊሞች ሠላማዊነት፣ ይቅር ባይነት፣ ወደ መልካም መጣራት፣ ፍቅርና ጥበቃ ደመቀች። የአመታት ሠቆቃ ወደ ደስታ ተቀየረ። ከዚም በመቀጠል ለአላህ እንደ ማመስገኛ በታሪክ ታላቅ የሆነ የይቅርታ ስርዓት ተካሄደ። ብዙ ሙስሊሞችን የገደሉና በወንጀል ተጨማልቀው የኖሩ ሰዎች በተመለከቱት ይቅር ባይነት የተነሳ ወደ ኢስላም ገቡ።[9]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በመጨረሻው ሐጃቸው (ሐጀተል ወዳ) እምነታችን እንደተሟላ አስተላለፉ። ይህም ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የነብይነት ጊዜያቸውን

---

[9] ቡኻሪ ኢቲሳም፣ ሙስሊም ፊዳኢል10፣ ኢብን ማጃህ፣ ማናሲክ 104፣ ሙዋታ፣ መዲና 10፣ አህመድ ኢብን ሀንባል፤ አል ሙሳናድ III 140.

እንዳጠናቀቁና ወደ አላህ መመለሻ ጊዜያቸው እንደተቃረበ ያሳይ ነበር፡፡ ለባልደረቦቻቸውም እንዲህ ሲሉ ጠይቀው ነበር፡፡

"ባልደረቦቼ ሆይ! ኢስላምን አስተላልፌላችኋለሁን?"

ሶሀቦችም ‹‹አዎን›› ሲሉ መለሱላቸው፡፡ ጥያቄውን 3 ጊዜ በመደጋገም 3 ጊዜ መልሱን ከሠሙ በኋላ እጃቸውን ወደ ላይ በማንሳት ይህን ተናገሩ-

"አላህ ሆይ ምስክሬ ሁን፤ አላህ ሆይ ምስክሬ ሁን፤ አላህ ሆይ ምስክሬ ሁን"

ከዚህ በኋላ ነው ቅዱስ የሆነው እምነት ባለቤትነት እስከ ቂያማ ድረስ ወደ ሙስሊሙ ማህበረሰብ የተላለፈው፡፡[10]

የተወሰኑ ረዳቶች (አንሷሮች) በረሱል መካን መግባት ተጨንቀው ነበር፡፡ ይህን ሲሉም እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር፡፡

"የልዕልና ባለቤት የሆነው አላህ (ሡ.ወ) መካን ለነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ከፈተላቸው፡፡ ከእንግዲህ ተመልሰው መዲና አይመጡም"

ከቆይታ በኋላ ይህን ሀሳብ ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ጋር ተወያዩበት፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡-

"ይህን ከማድረግ በአላህ እጠበቃለሁ! ህይወቴም ሞቴም ከእናንተ ጋር ነው፡፡[18]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለቃላቸው ታማኝነታቸውን ወደ መዲና በመመለስ አረጋግጠዋል፡፡

---

[10] ቡኻሪ፣ ጅሀድ 34፣ አቡ ዳውድ፣ ሶላት 12 ንናሳኢ፣ መሳጂድ 12 አህመድ ቢን ሀንባል፣ አል ሙሠናድ፣VI 289

ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) የመጨረሻው ነብይ ሲሆኑ ከሳቸው በፊት ግን አላህ (ሡ.ወ) የተለያዩ ነብያትን ለተለያዩ ህዝቦች ልኳል፡፡

⇒ አደም (ዐ.ሠ) መላኢኮች እንዲሰግዱላቸው የታዘዙላቸው ነብይ፣

⇒ ኑህ (ዐ.ሠ) ምድር በውሃ የተጥለቀለቀላቸው ነብይ፣

⇒ ሁድ (ዐ.ሠ) በመብረቅ ምድር የተገለበችላቸው ነብይ፣

⇒ ሳሊህ (ዐ.ሠ) የከሀዲያንን ቤት መሠረት ያናጉ ነብይ

⇒ ኢብራሂም (ዐ.ሠ) እሳት ወደ ውብ መናፈሻነት የተቀየረችላቸው ነብይ፣

⇒ ኢስማኤል (ዐ.ሠ) የታማኝነት፣ ለአላህ ታዛዥነት፣ በአላህ የመመካት ምልክት የሆኑ ነብይ፡፡ የኢስማኤል (ዐ.ሠ) ታሪክ በየአመቱ በሚደረገው ቅዱስ የሀጅ ጉዞ ላይ ይታወሳል፡፡

⇒ ይስሀቅ (ዐ.ሠ) ለእስራኤል የተላኩ ነብዮች በሙሉ የእርሳቸው ዝርዮች የሆኑላቸው ነብይ

⇒ ሉጥ (ዐ.ሠ) ወገኖቹ በግብረ ሶዶማዊ ተግባር በመዋጣቸው በሰዶምና ገሞራ በእሳት እንዲጠፉ የተደረገላቸው ነብይ፡፡

⇒ ዙልቀርነይን (ዐ.ሠ) ከምስራቅ እስከ ምዕራብ የአላህን አንድነት ለማስተማር የተጓዙ፣ የለፉ፡፡

⇒ ያዕቁብ (ዐ.ሠ) የፅኑ ፍቅርና የትዕግስት ምሳሌ የሆኑ ነብይ፡፡

⇒ ዩሡፍ (ዐ.ሠ) ውበታቸው ከጨረቃ የላቀ፡፡ በገርነታቸው በእስር ቤት በብቸኝነት ከኖሩ በኋላ የግብፅ ንጉስ ለመሆን የበቁ፤ ከአስቸጋሪና ፈታኝ ከሆኑ ሁኔታዎች ጋር ተጋፍጠው ያሸነፉ ነብይ፡፡

⇒ ሹአይብ (ዐ.ሠ) ውብ የሆነ የንግግር ክህሎት የተቸራቸው ነብይ ሲሆኑ በንግግሮቻቸው የህዝባቸውን ቀልብ በማሸነፍ በጥልቅ ደስታ ይሞሉ ነበር፡፡

⇒ ከድር (ዐ.ሠ) መለኮታዊ ሚስጥሮችን ለሙሣ (ዐ.ሠ) ያስተማሩ

⇒ ሙሣ (ዐ.ሠ) የፈርኦን የግፍ አገዛዝ እንዲያበቃ ያደረጉ እና ቀይ ባህርን በዱላ የከፈሉ ነብይ፡፡

⇒ ዳውድ (ዐ.ሠ) በድምፃቸው ውበት ተራሮችን፣ ድንጋይን፣ የዱር እንሰሳትን ሳይቀሩ ያስደስቱ የነበሩ ነብይ፡፡

⇒ ሡለይማን (ዐ.ሠ) ለሀብትና ንብረታቸው÷ እንዲሁም ለስልጣን በልባቸው ውስጥ ቅንጣት ቦታ ያልሰጡና የአላህ ባሪያነታቸውን የሚሹ ነብይ

⇒ ኡዘይር (ዐ.ሠ) ከሞት በኋላ የመቀስቀስ ምሳሌ የሆኑና ከመቶ አመታት ህልፈት በኋላ መልሰው የተቀሠቀሱ ነብይ፡፡

⇒ አዩብ (ዐ.ሠ) ትዕግስትን በህይወታቸው ያስተማሩና የትዕግስት ምሳሌ የሆኑ ነቢይ

⇒ ኤልያስ (ዐ.ሠ) ከአላህ (ሡ.ወ) ሰላምታ የተላከላቸው ነብይ፡፡ "ሰላም በኤልያስ ላይ ይሁን" ቅዱስ ቁርዓን 37፡130

⇒ ዙልኪፍል (ዐ.ሠ) እጅግ ንጹህ ልብ የነበራቸው እና የአላህ ቡራኬ የበዛላቸው ነብይ፡፡

⇒ ሉቅማን (ዐ.ሠ) ውጫዊም ሆነ ውስጣዊ ሠውነትን በማከም የታወቁ፣ በምክሮቻቸው ዘወትር የሚወሱ፡፡

⇒ ዘከሪያ (ዐ.ሠ) እጅግ የተሰቃዩ ነብይ ሲሆኑ በአላህ ላይ ባላቸው ፍፁም መመካት ሠውነታቸውን ለሁለት ሲከፈል እንኳን አላንገራገሩም፡፡

⇒ ያህያ (ዐ.ሠ) አባታቸውን እጅግ አድርገው የሚወዱ እና ሞትና መከራን የተጋፈጡ፡፡

⇒ ዒሳ (ዐ.ሠ) ነፍሳቸው እጅግ የፀዳች፣ በአላህ ፍቃድ የታመመን የመፈወስና የሞተን በማስነሳት ተዓምር ያሳዩ ነብይ

በአጠቃላይ አምላካችን አላህ (ሡ.ወ) መልዕክቱን በነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) አማካይነት ከማጠቃለሉ እና እሳቸውን ለአለም እዝነት አድርጎ ከመላኩ በፊት ወደ አንድ መቶ ሀያ ሺህ የሚጠጉ ነብዮችን በተለያየ ግዜ ለተለያዩ ህዝቦች ልኳል፡፡

ከታሪክ መዝገቦች እንደምንረዳው ሱወይባ የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የጡት እናቶች ከነበሩት ሴቶች አንዷ ናት፡፡ ይህች ሴት የአቡለሀብ ባሪያ የነበረች ሲሆን የነብያችንን መወለድ ለአቡለሀብ ለማብሰር የመጀመሪያዋ ሰው ነበረች፡፡ አቡለሀብም በተሰማው ደስታ (ደስታው ከጎሳው ክብር ጋር የተያያዘ ነው) የተነሳ ይህችን ባሪያ ነፃ አወጣት፡፡ ይህም የሆነው በእለተ ሰኞ ነበር፡፡ ይህ የአቡለሀብ ደስታ ከጎሳ ኩራት ጋር የተያያዘ ቢሆንም እንኳን ምን ግዜም ሠኞ ሠኞ የጀሀነብ ቅጣት ቀለል ይልለታል፡፡

አቡለሀብ ከሞተ በኋላ አንዳንድ ሰዎች በህልማቸው ተመልክተውት ይሄን ጥያቄ ይጠይቁታል፡-

"አቡ ለሀብ እንዴት ነህ?"

እሡም እንዲህ ሲል ይመልሳል፡- "በጀሀነም እሳት እየተቃጠልኩ እገኛለሁ፡፡ ሰኞ ሰኞ ግን ቅጣቴ ትንሽ ቀለል ይልልኛል፡፡ በዚህ ቀን በጣቶቼ ውሀ እስብና እጠጣለሁ፡፡ በዚህም የመቀዝቀዝ ስሜት ይሠማኛል፡፡ ይህም የሆነልኝ በነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) መወለድ ተደስቼ በሠኞ ቀን ሰውባን ነፃ ስላወጣኋት ነው፡፡ ለዚህም አላህ ምንዳዬን ሰኞ ሰኞ የጀሀነም እሳትን በመቀነስ ከፈለኝ፡፡

ኢብን አል ጃዚሪ ይህን ይላሉ፡-

"እንደ አቡለሀብ ያለ ከሀዲ እንኳ በነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) መወለድ ላሣየው ደስታ (ምንም አንኳን ደስታው ከጎሳ ኩራት ጋር ቢያያዝም) ምንዳ አገኘ። አማኞችም ለረሡል (ሠ.ዐ.ወ) ፍቅር ሲሉ ሰኞ እለትን ሊያከብሩና ሊያስቡ ይገባል።"

የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ልደት የማሰቢያ ትክክለኛው መንገድ በእለቱ የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ስለ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) መወለድና በዚህ የተነሳ ለአለም ስለ ፈነጠቀው ብርሀን መወያየት ነው። የነዚህ ዝግጅቶች ዋነኛው ኣላማ በነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) መወለድ ምክንያት ስለተለወጠችው አለም ማስተዋወቅ፣ ተስፋ ላጣው ተስፋ መስጠት፣ የኢስላምን መልዕክት ለረሳው ማስታወስ፣ ለማያውቀው ማሳወቅ፣ ወላጅ አልባዎችን ማፅናናት እና የቸገራቸውን መርዳት ነው። እንዲሁም ቁርዓንን በጋራ የመቅራት ፕሮግራሞችም ለዚህ ቀን ትውስታ ትክክለኛ መንገድ ነው።[11]

እኚህ ወላጅ አልባ ነብይ (ሠ.ዐ.ወ) ለአንዲት ቀንም ትምህርት ቤት ሄደው አልተማሩም። ግና ለመላው የሠው ዘር አስተማሪ፣ ሚስጥራዊውን ዓለም አስረጂና የእውነት ጠበቃ ሆኑ።

ሙሳ (ዐ.ሠ) ህግና ደንብን አመጡ። ዳውድ (ዐ.ሠ) አላህን በማስታወስና በዝማሬ ችሎታቸው ይታወቃሉ። ኢሳ (ዐ.ሠ) ለሠው ልጆች ግብረገብና መልካምነትን ከማስተማራቸው በላይ በዚህ ቁሳዊ ዓለም ለአላህ ሲሉ

---

[11] ዩሡፍ ኢብን ኢስማኤል አል ነበሀኒ፣ አል-አንዋር፣ አል-ሙሐመዲያን ሚን አል መወሂብ አል-ዱንያህ ገፅ 28-29 (በሌላ ዘገባ 14 በአል-ሠነዐ አል ሙሠነፍ VII 478 አል በይሀቂ፣ ሹአብ አል ኢማምን I261፡አል መርዋዚ፡አል ሡና I 82 ኢብን ሀጅጋር አል አስቃላኒ

መቆጠብን አስተምረዋል። ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) እኚህን ሁሉ ነገሮች በአንድነት ለሰው ልጅ አምጥተዋል። ህግና ደንቦችን አስተምረዋል። ነፍሶቻችንን እንዴት እንደምናፀዳ በተግባር አሳይተውናል። ከአላህ ጋር በንጹህ ልቦና መገናኘት አስችለውናል። የሰው ዘርን በሙሉ ስለ ግብረገብነትና ሞራላዊ ድርጊቶች አስተምረዋል። ከምንም በላይ በአላህና ስለ አላህ መደሰትን፣ ውጫዊም ሆነ ውስጣዊ ውበትን፣ ጀግንነትን፣ አዛኝነትን፣ ለፍጡራን መቆርቆርን በባህሪያቸው አስተምረውናል።

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) 40ኛው ዓመት ያለምንም ጥርጥር የሠው ዘር ታሪክ የለውጥ ጅማሬ ነበር።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለ40 ዓመታት በህዝባቸው ውስጥ ሲኖሩ ሀገረ ገዢ ወይንም ሰባኪ አልያም ህዝብ ፊት ተናጋሪ ወይም ወታደር እና ተዋጊ አልነበሩም። ስላለፉ ነብያትም ሆነ ስለታሪክ፣ ስለመጨረሻው ቀን እንዲሁም ስለ ገነትና ገሀነም አንዲትም ቃል ተናግረው አያውቁም። በከፍተኛ ግብረገብ እና ስርአት ብቻቸውን የሚኖሩ ሰው ነበሩ። በሂራ ዋሻ ውስጥ ትዕዛዝ ከደረሳቸው በኋላ ግን ብዙ ነገራቸው ተለወጠ።

መላው አረቢያ በአዲሱ መልዕክት ተሸበረች። ንግግራቸው በአድናቆት አፍን አስከፈተ። ባህሪያቸው ሁሉን አስደመመ። የመካ ባህል የነበረው የግጥምና የስነፅሁፍ ውድድር በአንድ ግዜ ቆመ። ገጣሚያን ግጥሞቻቸውን በካዕባ ግድግዳዎች ላይ መለጠፋቸውን አቆሙ። መካ ቅፅበታዊ ለውጦችን ማስተናገድ ጀመረች። የታዋቂው አረብ ገጣሚ የኢምሩል ቃይስ ሴት ልጅ እንኳ ቁርአንን ስትሰማ በመደመም ይህን ተናገረች፡-

"ይህ የሠው ልጅ ቃል ሊሆን አይችልም! እንዲህ ያለ ቃል በአለም ካለ የአባቴ ግጥሞች ከካዕባ ግድግዳዎች ላይ መነሳት አለባቸው! አዎ ሂዱና ከካዕባ ግድግዳ ላይ ሁሉንም አንስታችሁ እኚህን አንቀጾች ለጥፉ።"

ቁርአንን የሚመስል አንዲት አንቀጽ እንኳ እንዲያመጡ ነብዩ የሰው ልጆችን ጋብዘዋል፡፡ ይህ ግብዣ አሁንም ድረስ ምላሽ አላገኘም፡፡

አላህ (ሡ.ወ) በቁርአኑ፡-

﴿ وَإِن كُنتُمْ فِي رَيْبٍ مِّمَّا نَزَّلْنَا عَلَىٰ عَبْدِنَا فَأْتُوا بِسُورَةٍ مِّن مِّثْلِهِ وَادْعُوا شُهَدَاءَكُم مِّن دُونِ اللَّهِ إِن كُنتُمْ صَادِقِينَ ﴿٢٣﴾ ﴾ البقرة: ٢٣

‹‹በባሪያችንም ላይ ካወረድነው፥ በመጠራጠር ውስጥ ብትኾኑ፥ ከብጤው አንዲትን ምዕራፍ አምጡ፤ እውነተኞችም እንደኾናችሁ ከአላህ ሌላ መስካሪዎቻችሁን ጥሩ፡፡›› **(አል-በቀራ፡ 23)**

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የዘመኑን ኋላ ቀር አስተሳሰብና ባህል በማጥፋት እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ የማያረጅ ስልጣኔና አስተሳሰብን አስተዋወቁ፡፡

ቅዱስ ቁርዓን እጅግ ብዙ ሳይንሳዊ ተአምራት፣ ትምህርታዊ ጉዳዮችና ትንቢቶችን በውስጡ የያዘ ሲሆን በማንም ሆነ መቼም መታረምና መከለስ የማያሻው መፅሐፍ እንደሆነ ከዘመን ዘመን እያረጋገጠ ኖሯል፡፡ ባለንበት ዘመን የሚገኙ አዳዲስ ሳይንሳዊ ግኝቶች በብዛት በቁርዓን ውስጥ የተገለፁ እውነቶችን መስካሪ ናቸው፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለመላው የሠው ዘር የእውነት ተቆርቋሪ እና እውነተኛ ወዳጅ መሆናቸውን ተናግረዋል፤ አሳይተዋልም፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ መመሪያዎችን ያስቀመጡ ሲሆን የመንግሥትና የውጭ ግንኙነት መሠረታዊ መርሆዎችን አስቀምጠዋል፡፡ እነዚህ መርሆዎች ምናልባትም እድሜን ሙሉ በሚፈጅ ጥናትና ምርምር ሊገኙ የሚችሉ ናቸው፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ግን ያለምንም አስተማሪና ትምህርት እኚህን ሁሉ የጥናት ዘርፎች ተክነዋቸው ነበር፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ከነብይነት በፊት ጦር መሳሪያ ይዘው ባያውቁም፣ ለአንዲት ቀን ወታደር ሆነው ባያውቁም፤ ለንግግርም ሆነ ለቅስቀሳ ወጥተው ባያውቁም (በአንድ ወቅት ምስክር ከመሆናቸው በቀር) እጅግ ጀግና ወታደር፣ መቼም ተስፋ የማይቆርጥ እና ቆራጥ መሪ ሆኑ። ነቢያችን (ሠ.ዐ.ወ) ግጭትና ግርግርን አጥብቀው የሚጠሉ ቢሆንም በአላህ መንገድ ጥሪ እንዳያደርጉ የከለከሏቸውን እና ጥቃት ያደረሱባቸው ቡድኖች ለመመከት ግን ደም አፋሳሽ ጦርነቶችን ተቋቁመዋል። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እጅግ አዛኝና ሠላማዊ ከመሆናቸው የተነሳ ግድ ካልሆነ በቀር ጦርነት ማወጅን አይወዱም ነበር። በዘጠኝ አመታት ውስጥ መላው አረቢያን የተቆጣጠሩት በንፅፅር ደካማ በሆነ የወታደር ኃይል ነበር። በአላህ በመመካትና በእሡ እርዳታ።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እና ተከታዮቻቸው ባልሰለጠነ ጦርና ባልተሟላ የጦር መሳሪያ የዘመኑን ታላላቅ ሀይሎች (ቢዘንታይን እና ፐርሺያ) ለማሸነፍ በቅተዋል። የዚህ ድል ሚስጥሩም ከፍተኛ የሆነ መንፈሳዊ ጥንካሬና ግብረገብነታቸው ነበር።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አመፀኛ የሆኑትን የመካ ሰዎች በጥበብ እና በእርግጠኝነት ያናግሩ ነበር። ለምሳሌ፡- "ሀይማኖቱን (ኢስላምን) ተቀበሉና ተከተሉኝ! አሉ። አቡ ጀሀልም በተቃውሞ ይህን አለ፡-

"እኛ እንኳን ብንቀበልህ የሙደርና ራቢአ ጎሳዎች አይቀበሉህም"

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይህን መለሡ።

"ቢፈልጉም ባይፈልጉም ይቀበሉኛል፣ እነሱ ብቻ ሳይሆኑ የፐርሺያ እና የቢዛንታይን ህዝቦችም ይከተሉኛል።"[1220]

---

[72] ኢብን ኢስሀቅ ሲራ ገፅ 190 (በተመሳሳይ ዘገባ አህመድ ቢን ሀንበል አል ሙስነድ IV 128፣ 3፣ ኢብን አቢ ሽይባህ፣አል ሙሠናፍ VI፡ 311

ይህ ቃል ኪዳን ብዙም ሳይቆይ ተከሰተ። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የነበሩትን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሁሉ በመቋቋም በሠው ልጅ ታሪክ ትልቁን የባህሪና የአኗኗር አብዮት አምጥተዋል። ጨቋኞችን ታግለዋል። የተበዳዮችን እንባ አብሰዋል። ለወላጅ አልባዎች ፍቅርና እንክብካቤ የነበራቸው ነብይ የቲሞችን ያፅናኑ እና ፀጉራቸውን ይደባብሱ ነበር።

ማህሙድ አኪፍ የተባለ የቱርክ ታወቂ ገጣሚ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፡-

ወላጅ አልባው ህፃን አርባ አመት ደፈነ

በንጹህ እስትንፋስ ሰላም አሰፈነ።

የጭቁን አለኝታ የሰው ዘር ጠበቃ

የጨቋኞች ጠላት የግፈኛ አለቃ

ፍትህን ያስፋፋ የዕዝነት አስተማሪ

የእውቀት ባለቤት ነገርን መርማሪ

ያለን ሁሉ ፀጋ በሡ የተገኘ

ከርሱ የተማርነው በርሱ የተቃኘ

እድገታችን ስኬታችን

ህብረተሰብ ልጆቻችን

ሁሉ በነብዩ በአላህ መልዕክተኛ

ጌታችን አድርገን ሁሌ ቀጥተኛ።

መስክርልን ያኔ በዕለተ ቂያማ

ባንተ ማመናችን አንድም ሳናቅማማ

እሱን መውደዳችን በሙሉ ልባችን

ፈሩን ተከትለን ባለን በአቅማችን።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባይላኩ ኖሮ የሰው ልጅ በዋጠው ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ በኖረ፣ ጨቋኞች አቅም አልባውን ማሰቃየት የአደባባይ ተግባራቸው እንደሆነ በቀረ፣ ማህበረሰብ በዘቀጠ ግብረገብ መኖሩን በቀጠለ ነበር፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በአላህ እዝነት ለሠው ዘር ባይላኩ ኖሮ የዓለም የሀይል ሚዛን ወደ መጥፎ ባጋደለ፣ ምድራችን የግፈኞች የግል ንብረት በሆነች ነበር፡፡ ገጣሚው ይህን ሁኔታ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፡-

እርሶ ባይላኩ የአላህ መልዕክተኛ

መልካሞች ባልኖሩ በሆን ሀዘንተኛ

አበቦች ባልፈኩ ድሃ በተገፋ

እምነት ባልተገኘ ተውሂድ ባልተስፋፋ

አላህን ባላወቅን እንዲሁ በዳከርን

በክህደት ጨለማ ተውጠን በቀረን

ኢስላም ሀይማኖቶች ሁሉ የበላይና የሠው ልጅ ሊኖረው የሚችለው ትልቁ ሀብት መሆኑን አምላካችን አላህ (ሡ.ወ) በቁርአኑ እንዲህ ሲል ያስረዳናል፡-

اليوم أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ ٱلْإِسْلَامَ دِينًا ۚ المائدة: ٣

‹‹ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ›› **(አል-ማኢዳህ፡ 3)**

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለመጨረሻ ጊዜ ከመታመማቸው በፊት ጀነቱል ባቂ በመባል ወደሚጠራው መዲና ውስጥ የሚገኝ የመቃብር ስፍራ በመሄድ ይህን ዱአ አደረጉ፡-

"ታላቁ ጌታዬ ሆይ እዚህ የተኙ ሰዎችን መማር አታቋርጥ"[13]

በዚህም ተግባር ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እየተሠናበቷቸው ነበር፡፡

ከዚህም መልስ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረቦቻቸውን ለመሰናበት ሰብስበው እንዲህ በማለት ነገሯቸው፡-

"ልዑሉ አላህ ለባሪያው ሁለት ምርጫ ሠጠው፡፡ የዚህችን አለም መስህብ ወይስ የጀነትን በረከት፣ ባሪያውም ጀነትን መረጠ፡፡"

ይህን ተናግረው ሲጨርሱ እንስፍስፉ አቡበከር ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) እየተሰናበቷቸው እንደሆነ ገባቸውና አለቀሱ፡፡ ይህንንም ተናገሩ፡-

"የአላህ መልእክተኛ ሆይ እናቴና አባቴ ይሠውልዎት፡፡ ራሳችን፣ ገንዘባችን፣ ቤተሰባችን እና ልጆቻችን ለእርሶ መሰዋዕት ይቅረቡ፡፡"

ሌሎች ሶሀቦች ግን ምስጢር አዘሉን የረሡልን ንግግር መረዳት አልቻሉም ነበር፡፡ አቡበከር በሰውር ዋሻ ውስጥ ከረሡል (ሰ.ዐ.ወ) ጋር መኖራቸው ይህን ሚስጥራዊ ንግግር ከሌሎቹ በተሻለ በፍጥነት እንዲረዱት ረድቷቸዋል፡፡ [14]

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ስለ አቡበከር ይህን ብለው ነበር፡- "እኔ ልብ ውስጥ ያለ ነገር ሁሉ አቡበከር ልብ ውስጥ አለ" ሠሀቦችም አቡበከር ሲያለቅሱ በመመልከታቸው እርስ በራስ መጠያየቅ ጀመሩ፡፡

"አቡበከር (ረ.ዐ) ጌታውን መገናኘትን በመረጠ የአላህ ባሪያ ተግባር ለምን ያለቅሳል? አሉም፡፡

---

[13] ሙስሊም ጀናዝ 102፡ ነሳዒ፣ ደናዚ 103፡ ኢብን ሀርባን አል ሠሂህ (ሠ.ዐ.ወ) 444

[14] ቡኻሪ፣ ሠላት 80፡ ሙስሊም፣ ፊዳኢል አል-ሠሀባ 2 ቲርሚዚ ማናቂብ 15፡ ዳሪሚ፣ ሙቀዲማ14፡ ነሳኢ ጀናኢዝ 69፡ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠናድ III18

በጀነት የሴቶች መሪ የሆነችው እናታችን ፋጢማ (ረ.ዐ) በአባቷ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ማለፍ ሀዘኗን ስትገልፅ እንዲህ ትላለች፡፡

"በረሡል (ሰ.ዐ.ወ) ወደ መጪው አለም መጓዝ ሰበብ በውስጤ የተፈጠረው ሀዘን በቀን ላይ ቢወድቅ ድቅድቅ ጨለማ በዋጠን ነበር፡፡"[15]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሁለት መመሪያ ትተውልናል፡፡ ቁርአንና ሡና፡፡

እነዚህ ሁለት ምንጮች የነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ዘልአለማዊ ትዕዛዝ ናቸው፡፡ በዚህች አለምም ሆነ በቀጣዩ ዓለም ደስታን የፈለገ ሰው ሊከተላቸው የሚገቡ መመሪያዎች፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ወደ መዲና ከተመለሡ በኋላ ለ13 ቀናት የቆየ ከፍተኛ ህመም አጋጠማቸው፡፡ ከ13 ቀናት ህመም በኋላ የአለማችን ምርጡ ሠው በሠኔ 8/632 እ.ኤ.አ ወይም ረቢአል አወል 12 አ.ሂ ወደናፈቁት ጌታቸው ሄዱ፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) በሁለቱ ትከሻዎቻቸው መሀከል የነብይነታቸው ምልክት ነበራቸው፡፡ ሶሀቦች ይህን ምልክት ለመሣም እጅግ ይመኙ ነበር፡፡ በሞቱ ጊዜም በዚህች ምልክት ነበር ባልደረቦቻቸው መሞታቸውን ያረጋገጡት፡፡ ኢማም በይሀቅ እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል፡-

"የአላህ መልዕክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) መሞታቸውን እርግጠኛ መሆን አልቻሉም ነበር፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) ፊታቸው በቀድሞው ውበቱ ነበርና፡፡ አስማ (ረ.ዐ) የነብይነት ምልክታቸውን ለመመልከት ስትፈልግ ጠፍቷል፡፡ ይህም

---

[15] አል-ነብሀኒ፤ አል-አንዋር አል-ሙመዲያህ ሚን አል-መወሀባ አል-ላዱንያ ገፅ 593

እዚህች ምድር ላይ የነበራቸውን ጊዜ እንደጨረሱ እና ወደ አላህ እንደተመለሱ ማስረጃ ነበር፡፡[16]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ያመጡትን መልዕክት አስተላልፈውና አስተምረው፣ የሠው ልጆችን ስነ ምግባር ቀይረው፣ በእምነቱ የላቀ ማህበረሰብ ፈጥረው በመጨረሳቸው ወደ ዘላለማዊ አለም ተጠሩ፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ህዝባቸውን (ኡመታቸውን) በማህሸር (የትንሳኤ ቀን መሠብሰቢያ በሆነችው አደባባይ) እየጠበቁ ነው፡፡

አዎ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በሲራጥና ከውሠር ወንዝ ህዝባቸውን (ኡመታቸውን) እየጠበቁ ነው፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በረቢአል አወል 12 ሠኞ ቀን ተወልደው በተመሳሳይ ቀን አረፉ፡፡ አቡ ቃታዳ እንዲህ ሲሉ ይተርካሉ፡-

"ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሰኞ ቀን ስለመፆም ተጠየቁ፡፡ እንዲህ ሲሉም መለሱ

"ይህ ቀን የተወለድኩበትና በነብይነት የተመረጥኩበት ቀን ነው"[17]

"ዘላለም እንደሚቆይ የተመሰከረለትን ኢስላማዊ ሀገር (መዲና) የመሠረቱትና ወደርሱ የገቡትም በሰኞ ቀን ነበር፡፡

---

[16] ኢብን ሳዕድ፣ አል ጦበቃት II 2 71፡ አል በይሀቅ፣ ደላኢል- አል ኑቡዋህ VII 219

[17] ሙስሊም ሲያም 196፣ አህመድ ኢብን ሀንባል፣ አል ሙሠናድ v299፡ ኢብን ሂባን አል ሳሂህ VIII 403፣ አል በይሀቂ አል ሠናን አል ኩብራ IV 286

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በሰኞ ቀን ረቢአል አወል (12) መወለድ፣ በሰኞ ወደ መዲና መጓዝና ሰኞ ወደ መጨረሻው ዓለም መሄድ የአላህ (ሡ.ወ) ጥበብና ታላቅነት ማሳያ ነው፡፡ ቀኑም የተከበረ መሆኑን ማሳያ ነው፡፡

ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ህልፈት በኋላ መልዕክታቸው ቀጣይና ዘላለማዊ ቢሆንም እንኳን ባልደረቦቻቸውና ያላይዋቸው ህዛባቸው (ኡመታቸው) ይናፍቃቸዋል፡፡ ኡስማን ሠፊ አዚዝ ማህሙድ ሁደይ የተባለ ቱርካዊ ገጣሚ ይህን ብሎ ነበር፡-

አንቺ የውሸት አለም ከቶ ማን ያምንሻል

የሰው ዘርን አውራ ነቢዩን ወስደሻል፡፡

# ምእራፍ ሁለት

# ምሳሌ የሆነው የነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) አኗኗር

﴿ نُّورٌ عَلَىٰ نُورٍ ﴾ النور: ٣٥

«በብርሃን ላይ የኾነ ብርሃን» (አን-ኑር፡ 35)

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አኗኗር ለእያንዳንዱ የምድራችን ሠው ምሳሌ የሚሆን ነው። ምርጥ የሀይማኖት አባትነት ምሳሌ፣ ምርጥ የሀገር አስተዳዳሪ፣ ትልቅ የፍቅር አስተማሪና የመተናነስ ምሳሌ፣ የመታዘዝ፤ የመለገስና የደግነት መምህርና ምሳሌም ነበሩ። ለቤተሰባቸው የነበራቸው ፍቅር ከማንም በላይ ሲሆን ለደካሞች በማዘንም የሚደርስባቸው አልነበረም። የበደላቸውን በምህረት በማሸነፍና አላህን በመገዛት አቻ ያልተገኘላቸው ነብይ ናቸው።

ገንዘብና ንብረት ያላችሁ እንደሆነ የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት ተመልከቱ። የነበራቸውን መተናነስ አስተውሉ። በዚህ ባህሪያቸው ነበር መላ አረቢያን ይገዙ የነበሩትና የሀያላንን ልብ ያሸነፉት።

አቅመ ደካማ ከሆናችሁ፤ በግፈኞች ከትውልድ ከተማቸው የተባረሩትንና የተገፉትን ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት ተመልከቱ።

ወራሪና ግፈኛም ከሆናችሁ፤ በበድርና በሁነይን ግፈኞችን ያሸነፉትን ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ተመልከቱና ሳይረፍድ ተመለሱ፡

በጦርነት ከተሸነፋችሁ (አላህ ይጠብቃችሁና) ፍፁም በአላህ በመመካት በኡሁድ ጦርነት የተጎዱና የተገደሉ ወገኖቻቸውን ካነሱት ነብይ (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት ተማሩ።

አስተማሪ ከሆናችሁ ለህዝቦቻቸው ለስላሳና ማራኪ በሆነ መንገድ የአላህን ትዕዛዝ ያስተማሩትን ነብይ ህይወት ተመልከቱ።

ተማሪ ከሆናችሁ፤ ከጂብሪል አጠገብ ተቀምጠው በተመስጦ የተማሩትን ነብይ አስተውሉ።

የኃይማኖት አስተማሪ (ሠባኪ) ከሆናችሁም በመልካም አንደበታቸው እውቀትንና የአላህን መልዕክት ያስፋፉትን ነብይ ምሳሌያችሁ አድርጉ።

እውነትን ማገልገልና ከጠላቶቿ መታደግ ከፈለጋችሁና ደጋፊ ካጣችሁ ያለጥርጥር በግፈኞች መሀል ስለ እውነት የተናገሩትን ነብይን መመልከትና መከተል አለባችሁ።

ጠላቶቻችሁን ካሸነፋችሁ፤ ኃይላቸውን ካዳከማችሁና በነሡ ላይ የበላይነት ከተቀዳጃችሁ፤ የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት ተመልከቱ። ግፈኞችንና የበደሏቸውን ሠዎች ካሸነፉና ድልን ከተቀዳጁ በኋላ ወደ መካ ሲገቡ የነበራቸው መተናነስና ትህትና፣ ለግፈኞች የነበራቸው ይቅርታ ትምህርት ይሁናችሁ።

ገበሬም እንደሆናችሁ በበኒ ነድር፤ በኸይበርና አፍዳክ በግብርና የተካኑ ህዝቦችን መርጠው ያሰማሩትን ነብይ አስታውሱ።

ብቸኞች፣ ዘመድና ወላጅ ያጣችሁ እንደሆናችሁ እናታቸውን አሚናን እና አባታቸውን አብደላን የተነጠቁትንና እህት ወንድም የሌላቸውን ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ተመልከቱ።

ወጣቶችም በወጣትነታቸው ጠንካራ ሠራተኛና የአጎታቸውን የአቡ ጧሊብን ፍየል ጠባቂ የነበሩትን ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት አስተንትኑ።

የቢዝነስ ሰዎች፣ ለንግድ ምትጓዙ ከሆናች፣ የታማኙንና ነጋዴዎችን ከመካ እስከ ሶሪያ (ቡስራ) ነጋዴዎችን ይመሩ የነበሩት የሙሐመዱል አሚን (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት ምሳሌያችሁ ይሁን።

ዳኝነት ወይም ፍርድ ሰጪነት ስራችሁ እንደሆነ የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ፍትሀዊነት እንዲሁም አስታራቂነት ከልባችሁ ይኑር። ሀጀረል አስወድን

(ጥቁሩን ድንጋይ) ካዕባ ላይ በማስቀመጥ ሠበብ የተነሳ ሊጋደሉ የነበሩ የመካ ጎሳዎችን እንዴት እንዳስመሟቸው ተመልከቱና ጥበብንና መላን መሳሪያችሁ አድርጉ። ወደ ታሪክ መለስ በሉና ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በመዲና መስጂዳቸው ደሀንና ሀብታምን እንዴት እኩል እንዳደረጉ አስታውሱ።

ባሎችም ብትሆኑ ለባለቤቶቻችሁ ጥልቅ ፍቅር፣ እንክብካቤና አክብሮት የነበራቸውን የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት መመሪያችሁ አድርጉ።

አባወራዎችም ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለፋጡመቱ ዛህራ ምን አይነት አባት ለሀሰንና ሁሴይን እንዴት ያሉ አያት እንደነበሩ አስታውሱ። ያላችሁበት ሁኔታ ምንም ይሁን ምን፣ ራሳችሁን በምንም ሁኔታም አግኙት፤ ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ዘልአለማዊና ምርጥ መምህር፣ እንዲሁም መሪ ይሆኗችኋል።

የእሳቸውን መንገድ በመከተል ሁሉንም የህይወታችንን ገፅታ ማስተካከልና ማሳመር እንችላለን። በሳቸው ብርሀን ሁሉን ጨለማ መግፈፍና እውነተኛ የሆነ ደስታን መጎናፀፍ እንችላለን።

ፍትህ በአለም ላይ ሰፍኖ ከተመለከታችሁ፤ ድሀውና ሀብታሙ በፍቅር ተሳስሮ ብታዩ፣ ባለስልጣኑ የበታቹን ሲንከባከብ ብትደርሱ፤ ጤነኛው በሽተኛውን ማስታመም ስራው አድርጎት ብትመለከቱ፤ ወላጅ አልባና ባለቤታቸውን ያጡትን የሚንከባከብ ማህበረሰብ ቢያጋጥማችሁ በእርግጠኝነት ይሄ የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እና የምርጥ ተከታዮቻቸው ውጤት ነው።

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ምርጥ ስብእና ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎችን ጭምር ስለ እሳቸው እንዲመሰክሩ አስገድዷል። ለምሳሌ እንግሊዛዊው የታሪክ ተመራማሪ ቶማስ ካርላይል። Heroes Hero-worship and the Heroic in History በተሰኘውና ጀግና ናቸው ስለሚላቸው ሠዎች

በፃፈው መፅሐፍ ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) የምርጦች ሁሉ ምርጥ ሲል ገልጿቸዋል፡፡

ባለንበት ክፍለ ዘመን እንኳን ላሄይ ከተማ (ሆላንድ ውስጥ) በተለያየ ዘርፍ ምርጥ ምሁራን በተደረገ የአለማችንን 100 ምርጥ ሰዎች የመምረጥ ሂደት ምሁራኑ ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ለመምረጥ ተገድደዋል፡፡

ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) በነበራቸው ፍፁማዊ የግብረገብነት ምርጥ ባህሪ ጠላቶቻቸውን ሳይቀር ማስመስከር ችለዋል፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለሠው ልጆች እውቀትንና ብርሀንን የሠጡ የምንግዜም ባለውለታ ናቸው፡፡

በነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ዙሪያ የተለያየ ዘር፣ ቀለም፣ ቋንቋና ታሪክ የነበራቸው ሠዎች ነበሩ፡፡ ግን ሁሉም ከነብያችን መልካም ባህሪ ተጠቅመዋል፡፡ ቀጥተኛውንም መንገድ ተመርተዋል፡፡ ይህም ኢስላም ምን ያህል ለዘረኝነት ቦታ እንደሌለውና መላውን የሠው ዘር በእኩል አይን እንደሚያይ ያሳያል፡፡

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ተከታይ ከነበሩት መሀከል እኚህን እናገኛለን፤ የአቢሲኒያ (ሀበሻው) መሪ ነጃሺ፣ የመአን ጎሳ መሪ የሆነው ፈርዋን፣ የሁመይር ጎሳ መሪ የሆነው ዙልኪላህ፣ የፌሩር ገዢው ዳይላሚ፣ የየመኑ ማራብቡድ እንዲሁም የኡማኖቹ ኡበይድ እና ጃዕፋር ይገኙበታል፡፡ ከገዢዎችና ባለ ስልጣኖች ወጣ ብለን ደግሞ ደህና ባሪያ የነበሩትን ቢላል፣ ያሲር፣ ኸባብ፣ አማር እና አቡ ፋቅያህ÷ ከእንስት ባሪያዎች ደግሞ ሱመያ፣ ሉባዓን፣ ዚኒራ፣ ናህዲያ እና ኡሙ አባስ ይገኙበታል፡፡

ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ተከታዮች ውስጥ የአመራር ብቃት ያላቸው አስተዋይና ሚስጥር ፈቺ የሆኑ እንዲሁም በእደ ጥበብ የተካኑ ሰዎች ነበሩበት፡፡ በነዚህ ተከታዮቻቸው የተነሳ ሀገራት ሠላም ሆነዋል፣ ምድር

የፍትሀዊነት ጣዕም አጣጥማለች፡፡ የሠው ልጆች በወንድማማችነት ተሳስረዋል፡፡

ላፋይቴ የተሰኘ የፈረንሳይ ምሁር (በፈረንሳዩ 1789 አብዮት ላይ ከፍተኛ የምሁርነት ድርሻውን የተወጣ) በአለም ላይ ሰፍነው የቆዩ የፍትህ ስርአቶችን በሙሉ ከመረመረና ካጠና በኋላ ኢስላማዊ ህግ ከሁሉም እንደበለጠበት እንዲህ ሲል አስቀምጦታል፡-

አንተ የደረስክበትን የፍትህ ደረጃ ከቶም ማንም ደርሶበት አያውቅም"

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በመንፈሳዊ ጥንካሬያቸው ከፊል አውሬነት ያጠቃው የነበረውን ማህበረሰብ አስተሳሰብና ባህሪ ቀይረው በአንድ ሀይማኖት፣ ባንዲራ፣ ባህል፣ ስልጣኔና መንግስት ስር አስቀመጡት፡፡

ያንን ያልተገራ፣ ያልተማረ ህግ አልባ ህዝብ ወደ ሰለጠነ ባህሪ ለወጡት፤ በምቀኝነትና በወንጀል የተጨማለቀውን ህብረተሰብ አላህን ወደ መፍራት አሸጋገሩት፡፡

ለዘመናት ምሳሌ የሚሆኑ ሠዎችን ማፍራት ተስኖት የነበረን ማህበረሰብ በባህሪያቸውና በእውቀታቸው የሚያስደምሙ ሰዎችን እንዲያበቅል አደረጉት፡፡ በዚህ ብቻ አላበቁም፡፡ እውቀቱን አፍኖ ከመቀመጥ ይልቅ በአለማችን ሁሉም አቅጣጫዎች ማዳረስን የሚሻ ትውልድ አበረከቱ፡፡ የሠው ልጅ የተፈጠረበት አላማ ታወሰ፤ ተተገበረ፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የሠውን ልብ በመማረክ ወደር የላቸውም፡፡ የሳቸውን ያህል ከቶ ማንም የብዙሀንን ልብ ሊያንበረክክ አልበቃም፡፡ እኚህ ውድ ነብይ ከዚህ ሁሉ በኋላ እንኳን ከህዝባቸው የተለየ ኑሮ መኖር አላሻቸውም፡፡ እንደ ጥንቱ በመተናነስና በትህትና ይኖሩ ነበር፡፡ ድሀ እና ቀን ከሌት የሚለፉ፤ በሚጎረብጥ ፍራሽ ላይ የሚተኙ፤ የተሸቀጠቀጠ አለባበስ ፈፅሞ የማይታይባቸው፣ ከድሆች በታች ዝቅ ብለው የሚኖሩ ሰው ነበሩ፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ከረሀብ የተነሳ ሆዳቸውን በድንጋይ የሚያስሩባቸው ጊዜያት ነበሩ፡፡ እንዲህም ሆኖ አመስጋኝ ባሪያ!!

ያለፈውና የሚመጣው ሀጢያትህ ሁሉ ተምሯል›› ብሎ አምላካችን አላህ (ሱ.ወ) በቁርአኑ ገልፆላቸው እንኳ ቀን ከሌት ዱአ ያደርጉና ጌታቸውን ይቅርታ ይለምኑ ነበር፡፡

ረሱላችን (ሠ.ዐ.ወ) አብላጫውን ጊዜያቸውን ከችግረኛ፣ አይዟችሁ ባይ ካጡና ከብቸኛ ሰዎች ጋር የሚያሳልፉ ሲሆን፣ ለእርዳታ በተጠሩ ግዜም ቀድሞ ደራሽ ነበሩ፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ወደ መካ በድል ተመልሰው በመጡ ጊዜ በመካ ታላቅ ሰው ተደርጎ ይቆጠር የነበረ ግለሰብ በመሽቆጥቆጥ "የአላህ መልዕክተኝ ኢስላምን ያስተምሩኝ" አላቸው፡፡ ነብያችንም፡-

"ተረጋጋ ወንድሜ! ንጉስም ሀገር ገዢም አይደለሁም" በፀሀይ የደረቀ ስጋን እመገብ የነበረ ወላጅ አልባ ጥንት የእናትህ ጎረቤት ነኝ"[18] ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በዚህ መልሳቸው ማንም አርጎት የማያውቀውን የመተናነስ ደረጃ አሳይተውናል፡፡

በዚሁ እለት ከነብዩ ጋር በሂጅራ ወቅት በሰውር ዋሻ አብረዋቸው የነበሩት አቡበከር አቅማቸው የደከመ አባታቸውን የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) መልእክት እንዲሠሙ በማለት በትከሻቸው ተሸክመው ወደ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይዘዋቸው መጡ፡፡ ነብዩም (ሠ.ዐ.ወ) ይህን አሉ፡-

[18] ኢብን ማጃህ አጥ አይዳህ 36 አል ሀኪም አል ሙስታድሪክ II 506፣ አል ጦበራኒ አል ሙዓጅም አል አውሳጥ II 64.

"አቡበከር ሆይ÷ ያረጁ አባትህን ለምን አንገላታህ? እኔ አልመጣም ነበርን?[19]

ብዙ ሀገራት በነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አስተዳደር ስር ገቡ፣ ግዛታቸው መላ አረቢያን አጠቃለለ፡፡ የፈለጉትን ሁሉ ማድረግ የሚያስችል ስልጣን ነበራቸው፡፡ ረሡላችን (ሠ.ዐ.ወ) ግን በመተናነስና በትህትናቸው ዘለቁ፡፡ ምንግዜም ቢሆን እሳቸው በምንም ነገር ላይ ስልጣን እንደሌላቸውና ሁሉም ነገር ከአላህ (ሡ.ወ) እንደሆነ ያስተምሩ ነበር፡፡

በአንድ ወቅት የመዲና ነጋዴዎች እጅግ ብዙ ገንዘብ ለገሱ፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሁሉንም ለችግረኞች አከፋፍለው ህይወታችውን እንደነበረ በመተናነስ መኖር ቀጠሉ፡፡ እንዲህ ሲሉም ተናገሩ፡፡

"የኡሁድ ተራራን የሚያክል ወርቅ ባገኝ እንኳን ከ3 ቀን በላይ አላቆየውም፡፡ እሱንም እዳዬን ለመክፈል"[20]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በቤታቸው እሳት ሳይነድ (ምግብ ሳይበስል) ቀናት ያልፉ ነበር፡፡ ብዙ ጊዜያት እንደተራቡ ወደ መኝታቸው ተጉዘዋል፡፡

አንድ ቀን ኡመር (ረ.ዐ) ወደ ረሱል (ሠ.ዐ.ወ) ቤት መጡ፡፡ ወደ ውስጥ ሲገቡም ነብዩ ከቴምር ቅጠል ከተሰራ ፍራሽ ላይ ተኝተው ነበር፡፡ ደረቆቹ የቅጠሉ ጠርዞች በውዱ የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሰውነት ላይ

---

[19] አህመድ ኢብን ሀንበል፣ አልሙስነድ vi፣349፣ኢብን ሂባን፣ አል ሳሂህ ፣ xvi 187አል ሀኪም አል ሙስታድራክ III 48.

[20] ቡኻሪ፣ ሙስሊም፣ ኢብን ማጃህና አህመድ ኢብን ሀንባል.

ሰንበሮችን አውጥቷል፡፡ በአንድ ጥግ ትንሽ ዱቄትና ውሃ አዩ፡፡ ከነዚህ ነገሮች በቀር በቤት ውስጥ ፈፅሞ አንድም ነገር የለም፡፡ በዚህ ወቅት ታዲያ መላው አረቢያ በነብያችን (ሡ.ዐ.ወ) አስተዳደር ስር ነበረች፡፡ ኡመር እጅግ ደነገጡ፡፡ አምባቸውንም ማቆም አልቻሉም፡፡

ነብያችን (ሡ.ዐ.ወ) "ኡመር ሆይ! ለምን ታለቅሳለህ?" ሲሉ ጠየቁት፡፡ ኡመርም (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ መለሡ፡-

"እንዴት አላለቅስ የአላህ መልዕክተኛ?! የሮምና የፐርሺያ ንጉሶች በምቾት ሲንደላቀቁ የአላህ መልዕክተኛ ከቴምር ዛፍ ቅጠል የተሰራ ደረቅ ፍራሽ ላይ ይተኛሉ?!"

ነብያችን (ሡ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡-

"ኡምር ሆይ! ቄሳርና የፋርስ ንጉስ በዚህች አለም ይደሰቱ፤ ለኛ ግን የቀጣዩ ዓለም ደስታ በቂያችን ነው፡፡!"[21]

ቀጥለውም፡-

"ይህ አለም ለኔ ከቶ ምን ያደርግልኛል?! የኔና የዚህች አለም ግንኙነት እንደ በጋ መንገደኛ ነው፡፡ ከዛፍ ጥላ ስር አረፍ ብሎ ሲነጋ መልሶ እንደሚጓዘው፡፡"[22]

ነብያችን (ሡ.ዐ.ወ) ለህይወት ያላቸው አመለካከት ፍጹም ምርጥ ነበር፡፡

ለጠንካራም ሆነ ለደካማ፣ ለሀብታምም ሆነ ለደሀ ተከታዮቻቸው ምሳሌ የሆነ ህይወት ነበራቸው፡፡ ይህችን ዓለም በተለዩበት ወቅት ከአንዲት

---

[21] አህመድና ጦበራኒ

[22] ቲርሚዚ፣ ቤን ማጃህና አህመድ

ነጭ በቅሎ፣ ሰይፍ እና በፈድክ ከሚገኝ በስጦታ የተገኘ መሬት ውጭ ሌላ ንብረት አልነበራቸውም፡፡

ካለፉ በኋላም ሠዎች ንብረታቸውን ለቤተሰቦቻቸው እንዳይሰጡ ሲሉ ከልክለው ነበር፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በዚህች ምድር ላይ በቆዩበት ጊዜ ሁሉ አንድም ቀን ለሀብትና ለንብረት ትኩረት ሳይሠጡ በአንድ አላህ ማመንን (ተውሂድ) ለመገንባት ሲደክሙ ኖረዋል፡፡

አይሻ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት አንዲት የአንሷር ሴት ወደ ቤታቸው መጣች፡፡ የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ፍራሽ በአንድ ጥግ ተቀምጦ በተመለከተች ግዜ እጅግ ደንግጣ ወደ ቤቷ በሩጫ በመመለስ በበግ ፀጉር የተሞላ ምቹ ፍራሽዋን ይዛ ተመለሰች፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ወደ ቤት በሚመጡበት ግዜ ፍራሻቸው ወደ ምቹና ያማረ ፍራሽ መቀየሩን ሲመለከቱ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ፡-

"አይሻ ሆይ! ይሄንን ፍራሽ ለባለቤቱ መልሺ! እኔ ብፈልግ ኖሮ ጌታዬ አላህ (ሱ.ወ) የብርና የወርቅ ተራራ ባንድነት አብረውኝ እንዲጓዙ ያደርግ ነበር"[23]

አላህ (ሡ.ወ) በቁርአኑ እንዲህ ይለናል፡-

﴿ لَقَدْ جَآءَكُمْ رَسُولٌ مِّنْ أَنفُسِكُمْ عَزِيزٌ عَلَيْهِ مَا عَنِتُّمْ حَرِيصٌ عَلَيْكُم بِٱلْمُؤْمِنِينَ رَءُوفٌ رَّحِيمٌ ﴿١٢٨﴾ ﴾ التوبة: ١٢٨

‹‹ከጎሳችሁ የሆነ. ችግራችሁ በርሱ ላይ ጽኑ የሆነ. በናንተ (እምነት) ላይ □ሚ□□ በምእመናን (ላይ) ርህሩህ አዛኝ የኾነ መልዕ□ተኛ. በእር□□ መጣላችሁ፡፡›› **(አት-ተውባህ፡128)**

---

[23] አህመድ ኢብን ሀንባል፤ ኪታብ አል ዙሀድ ገፅ 53፤ አል-በይሀቅ ሹአብ አል ኢማን!! ገፅ 173 ኢብን አቢ አሲም ኪታብ አል ዙሀድ !ገፅ 14

ይህ ሁሉ ተነግሮ የማያልቅ ምርጥ የነብያችን ባህሪ ምክንያቱ ልዑል ጌታችን አላህ (ሱ.ወ) ነብያችንን ለሠው ልጅ ፍፁም ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ ከፍ አርጎ ስለፈጠራቸው ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ነብያችንን በማህበረሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ስፍራ ይሰጠው ከነበረው ወላጅ አልባነት ጀምሮ እስከ ከፍተኛው ሀገር አስተዳዳሪነትና ምርጥ ነብይነት ደረጃ አደረሳቸው፡፡ ይህን ያደረገው በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ የህብረተሰቡ ክፍሎች ለነብዩ የተለየ ወገንተኝነት እንዲሰማቸውና ነብያችንን የራሳቸው ወገን አድርገው እንዲያስቡ አድርጓል፡፡ ለዚህም እጅግ ቀላል ምሳሌ "ሙሐመድ" የሚለው ስም በማህበረሰባችን የትኛውም ክፍል ውስጥ ያለ ወላጅ ለልጆቹ በደስታ የሚያወጣው ስም መሆኑ ነው፡፡

ለምሳሌ በቱርክ ሙሐመድ የሚለው ስም "ሜህሜቲጅክ" በትርጉም ትንሹ ሙሀመድ በማለት ወላጆች በብዛት ልጆቻቸውን ይሰይሙበታል፡፡ ይህም ልጆቻቸው የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ባህሪ ይዘው እንዲያድጉ ካላቸው ጉጉትና ምኞት ነው፡፡ ይህም ህፃናቱን በጨቅላ አይምሯቸው የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ባህሪያት የመላበስ ጉጉት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በልጅነትም ሆነ በወጣትነታቸው ቅንጣትም የባህሪ ጉድለት አልታየባቸውም፡፡ እንደ አብዛኞቹ የዓለማችን መሪዎችም ባህሪያቸው ድንገተኛ ለውጥ አይደለም፡፡ አብሯቸው የኖረ እንጂ፡፡ ይህም በአላህ (ሡ.ወ) የመመረጣቸው ውጤት ነው፡፡

በአለማችን ስለ አመራርና አስተዳደር እንዲሁም መልካም ባህሪ በመፃፍና በማስተማር የሚታወቁ ፈላስፎችን ብንመለከት ያስተማሩትንና የሰበኩትን ራሳቸው መኖር ሲያቅታቸው እናገኛለን፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ግን ከዚህ እጅግ በተለየ ሁኔታ የተግባር ሠው ነበሩ፡፡

እንደ ምሳሌ ጀርመናዊው ፈላስፋ ፍሬድሪክ ኒቼ ስለ ፍፁም ሰው የሚያወራው መፅሐፍ ቢኖረውም በግል ህይወቱ ግን ያለውን መሆን

ሲያቅተው ታሪክ ይዘግባል፡፡ ኢስላማዊው ግብረ ገብነት ግን ከዚህ ፍፁም በተለየ መልኩ በአስተማሪያችን በነብዩ ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) በተግባር ተኑሮ እናገኘዋለን፡፡ ለዚህም ነው ኢስላም ከሌሎች አስተሳሰቦች የሚልቀው፡፡

ሌላ ምሳሌ እንውሰድ፡፡ አርስቶትል ስለ ግብረ ገብነት የሚያወራ መመሪያ አለው፡፡ ግና የአርስቶትልን የግብረ ገብነት መርህ ተግብሬ ደስተኛ ሆኛለሁ የሚል አንድም ተከታይ አናገኝለትም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ፈላስፎች በልብ ንፅህና ሂደት ስላላለፉና መለኮታዊ ስላልሆኑ ነው፡፡ ነብያት ተግባርና ቃላቸው በአምላካቸው ሲደገፍ፤ የፈላስፎች መርህ ግን በኮንፈረንስ ክፍሎችና በመፅሀፍ ገጾች ተወስኖ ይቀራል፡፡ የሰዎችን የእለት ተእለት ኑሮ ሠብሮ መግባትም ይሳነዋል፡፡

አስተማሪያችንና መሪያችን ነብዩ ሙሐመድ ግን ከነብይነት በፊት በመልካም ባህያቸው የታወቁና በማህበረሰባቸው "ሙሐመድ ታማኙ" በመባል ይጠሩ የነበሩ ሠው ናቸው፡፡ የሚያውቋቸው ሰዎች በሙሉ መልካም ባሪያቸውንና ስነ ምግባራቸውን ይመሰክሩ ነበር፡፡ ለዚህም ነው ትልቅ ክብርና ግምት የሚሠጡትን የካዕባን ጥቁር ዲንጋይ (ሀጀረል አስወድ) የማስቀመጥ መፍተሄ ያለምንም ተቃውሞ ለርሳቸው የሰጧቸው፡፡ ነብያችን በወጣትነታቸው ከየትኛውም አመፅና የተበላሸ ስነ ምግባር ፍጹም የራቁ የነበሩ ሲሆን ከነብይነታቸው በፊት የተቀላቀሉት ብቸኛው ቡድን "ሂልፍ አል ፍዱል" የተባለ የወጣቶች ቡድን ነበር፡፡

ይህ ቡድን፡- ፍትህን ለማስፋትና፤ ፍትሀዊ ውሳኔዎችን ለማስፈፀም የተቋቋመ የፍቃደኞች ስብስብ ነበር፡፡ መመሪያቸውም እንዲህ ይል ነበር፡-

"በመካም ይሁን ከመካ ውጭ የማንኛውም ሰው መብት ከተጣሰ አጥፊውን እንቃወማለን፤ በደሉ እስኪካካስ ድረስ ከተበዳዩ ጎን እንቆማለን፤ ፍትህንና ሠላምን እናረጋግጣለን"

ይህ ግፈኞችን የመቃወምና ፍትህን የመደገፍ ተግባር ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) እጅግ ስቧቸው ነበር። ከነብይነት በኋላም ይህን ብለዋል፡-

"ከአብደላህ ኢብን ጁደን ቤት ከአጎቶቼ ጋር ተቀምጬ ነበር፤ ቀይ ግመል (የዚህች አለም ሀብት) ቢሠጠኝ እንኳ እንዲህ ያለ ቡድንን በመቀላቀል የምደሰተውን ያህል አልደሰትም። ያ ውል ዛሬም ቢፈጸም ቡድኑን ከመቀላቀል ወደ ኋላ አልልም፡"[24]

አይን ደማቅ የብርሀን ፍንጣቂን አለማየት እንደማይችለው ሁሉ ይህ ለሠው ዘር የበራ ሻማ ማንም ፈፅሞ መካድ አይችልም። ከዚህ በፊት የተጠቀሰው የታሪክ ምሁር ቶማስ ካርላይል የ"ጀግኖች ጀግና አማኞችና የጀግኖች ታሪክ" የሚል መፅሐፍ[25] የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) መወለድ የሰው ዘር ከጨለማ ወደ ብርሃን መሸጋገር ብሎ ይገልፀዋል።

ኢንሳይክፒድያ ብሪታኒካም ቢሆን የትኛውም የሐይማኖት መሪም ሆነ ሠባኪ ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ከደረሰበት ላይ መድረስ አይችልም ብሎ ይመሰክራል።

ስታንሌ ለጌ-ፖሌ የተባለ ደራሲ እንዲህ ሲል ይመሰክራል፡- "ሙሐመድ ጠላቶቹን ያሸነፈበትና የቁረይሽ ግፈኞች ይቅር ያለበት ቀን ታላቅነቱን ያስመሰከረበት ቀን ነው"

አርቱር ጊልማን የተባለ ፀሐፊ ደግሞ እንዲህ ይላል፡- "ነብዩ ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) በመካ ሰዎች የደረሰባቸው ሁሉ በደል ለበቀል በቂ ምክንያት

---

[24] ኢብን ሰዕድ አል ጠበቃት 1፡129፡ኢብን ሂሻም አል ሲራ አል ነበውያህ 1፡133-134፡ አህመድ ኢብን ሀንባል አል ሙሠናድ I, 190-193፡ አል በይሀቂ አል ሱነን አል ኩብራ VI,367

[25] ገፅ 51ን ተመልከቱ

ነበር። እሳቸው ግን ምንም አይነት ደም መፍሰስ እንዳይፈፀም ከለከሉና ታላቅነታቸውን አስመሰከሩ፤ ለአላህም አመስጋኝ ሆኑ።"

## ነቢያችን በጣኦታውያን አመለካከት

የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) እውነተኛነት ጣኦታዊያን ሳይቀሩ ይመሰክራሉ። ከዋንኛ የኢስላም ጠላቶች አንዱ የሆነው አቡ ጃህል ለነብያችን ይሄን ብሏል፡-

"ሙሐመድ ሆይ! እኔ ውሸታም አልልህም፡ ያመጣኸውን ሀይማኖት ግን ፈፅሞ አልወደድኩትም"[26]

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ቀንደኛ ጠላቶች ሳይቀሩ የርሳቸውን እውነተኝነት ጠንቅቀው ያውቃሉ። ፊት ለፊት ለመካድ ቢሞክሩም። ይህንንም አላህ (ሡ.ወ) እንዲህ ሲል ይገልፅልናል።

﴿ قَدْ نَعْلَمُ إِنَّهُۥ لَيَحْزُنُكَ ٱلَّذِى يَقُولُونَ ۖ فَإِنَّهُمْ لَا يُكَذِّبُونَكَ وَلَٰكِنَّ ٱلظَّٰلِمِينَ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ يَجْحَدُونَ ﴿٣٣﴾ ﴾ الأنعام: ٣٣

‹‹እነሆ ያ የሚሉህ ነገር እንደሚያሳ-ዝንህ በእር□□ □እናውቃለን፤ እነርሱም (በልቦቻቸው) አያስተባብሉህም. ግን በዳዮቹ በአላህ አንቀጾች ይክዳሉ።›› **(አል-አንዓም፡ 33)**

በወቅቱ (628) እ.ኤ.አ ፐርሺያን ያሸነፈው የቢዛንታይን ንጉስ ሄራክሊየሥ በሶሪያ እያለ ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ደብዳቤ ደረሰው። ደብዳቤው ወደ ኢስላም የሚጋብዘው ነበር። ሄራክሊየስ ከንጼት ይልቅ ለደብዳቤው ፍላጎት አሳየ። ስለዚህ ሀይማኖት የማወቅና የመማር ጉጉት

---

[26] ቲርሚዚ- ተፍሲር ስራ 6፡1 አል-ሀኪም አል ሙስታድረክ II 345

አየለበት፡፡ ለዚህም ጉዳይ ሲል ነብዩን በቅርበት የሚያውቅ ሰው ተፈልጎ እንዲመጣለት አዘዘ፡፡ በዚህ ግዜም የኢስላም ቀንደኛ ጠላት የነበረው አቡ ሱፍያን ከሲራራ ነጋዴዎች ጋር በሶሪያ ነበር፡፡ ፍለጋ ላይ የነበሩት የንጉሡ አገልጋዮች አቡ ሡፍያንን እና ሌሎች ነጋዴዎችን ይዘው ሄዱ፡፡ ወቅቱ በሂጅራ አቆጣጠር 6ኛ አመት ነበር፡፡

ሂረክለስም በአልያ እና በይተል መቅደስ አካባቢ ነበር፡፡ እነ አቡሡፊያን በአስተርጓሚ ማናገር ጀመረ፡፡

አቡ ሱፍያን ቢን ሐርብ አውግቶኛል በማለት ቢን አባስ እንዳስተላለፉት ሂረቅል ወደ አቡ ሱፍያን ልኮ ከባልንጀሮቹ ጋር አስመጣው። ያኔ አቡ ሱፍያን ገና አልሰለመም። ለንግድ ወደ ሻም ተጉዞ ነበር። ሂረቅል ኤል (በይተል መቅዲስ) ውስጥ እያለ አገኙት።[27] ታላላቅ የሮም መሳፍንትና ልዑላን በተገኙበት አስጠርቶ ስለ ነቢዩ ሙሐመድ በአስተርጓሚ በኩል ጠየቃቸው። መጀመሪያ ያቀረበላቸው ጥያቄ፡- «ለዚህ ሰው ዝምድና የሚቀርበው ማን ነው?» የሚል ነበር። አቡ ሱፍያን፡- «እኔ» ሲል መለሰ። ከፊት ለፊቱ አስቀመጠው። ባልንጀሮቹንም ከርሱ ጀርባ አስቀመጣቸው። ለአስተርጓሚውም፡- «ነብይ ነኝ ስለሚለው ሰው እጠይቀዋለሁ። ከዋሸኝ ባልንጀሮቹ ያስተባብሉ።» ሲል አዘዘ። አቡ ሱፍያን ክስተቱን እንዲህ ሲል ተርኳል፡-

በአላህ እምላለሁ፣ ውሸቴ እንዳይጋለጥብኝ ባልፈራ ኖሮ እዋሸው ነበር። «ዘሩ እንዴት ነው?» በማለት ጠየቀኝ። «ከተከበረ ቤተሰብ የተገኘ ነው» አልኩት። «ከዚህ ቀደም ነቢይ ነኝ ያለ ሌላ ሰው ከወገኖቻችሁ መሐል አለን?» አለኝ። «የለም» አልኩት። «ከአያት

---

[27] ቀይሰር ፋርሶችን አሸንፎ ድል በማግኘቱ፣ ፋርሶች ኪስራን ገድለው የሮማን ምድር በመመለስ እጅ ሰለሰጡት እና ክርስትያኖች እየሱስ ተሰቅሎበታል የሚሉትን መስቀል ፋርሶች ስለመለሱለት አምላክን ለማመስገንና መስቀሉን ወደቦታው ለመመለስ በ629 (ዓ.ል) ወደ ኤል ሄዶ ነበር።

ቅድመ አያቶቹ መሐል ንጉስ አለን?»አለ። «የለም»አልኩት። ተከታዮቹ ባላባቶችና የተከበሩ ሰዎች ናቸው ወይስ ተራና ደካማ ሰዎች» ሲልም ጠየቀኝ። ተራና ደካማ ሰዎች ናቸው አልኩት። «ቁጥራቸው እየጨመረ ይሄዳል ወይስ ይቀንሳል?» አለ። «በየጊዜው ይጨምራል።»አልኩት። ሐይማኖቱን ከተቀበለ በኋላ ወደናንተ ሐይማኖት የሚመለስ አለን?» ሲልም ጠየቀኝ። «የርሱን ሐይማኖት ክዶ ወደኛ ሐይማኖት የሚመለስ አንድም ሰው የለም» አልኩት። «ነብይ ነኝ ከማለቱ በፊት በመዋሸት ይታወቃልን?» አለ። «አይታወቅም» አልኩት። «ሸፍጥ ፈጽሞ ያውቃልን?» አለ። «አያውቅም። ግና ለተወሰነ ጊዜ ስለተራራቅን ምን እንደሚሰራ አናውቅም» አልኩት። ተጨማሪ ነገር ልናገር ነበር። ግና ፋታ አልሰጠኝም። «ተዋግታችሁታልን?» አለኝ። «አዎ» አልኩት። «ውጊያችሁ እንዴት ነበር?» አለኝ። «በጣም የተፋፋመ ነበር። አንዳንድ ጊዜ እኛ ሌላ ጊዜ እርሱ እናሸንፋለን።» አልኩት። «ምን ምን ያዛችኋል?» አለኝ። «አላህን በብቸኝነት አምልኩ። ከርሱ ጋር ምንንም ነገር አታጋሩ። አባቶቻችሁ የሚሉትን (ከንቱ ነገር) ተው፣ ይለናል። ሶላት እንድንሰግድ፣ ሶደቃ እንድንሰጥ፣ ቁጥብ እንድንሆን፣ ዝምድናን እንድንቀጥል ያዘናል።» አልኩት። እንዲህ አለ፦

«ስለ ዘሩ ስጠይቅህ ከተከበረ ዘር መሆኑን ነግረኸኛል። መልዕክተኞች የሚነሱት ከተከበረ ዘር መሐከል ነው። ከርሱ በፊት ነብይ ነኝ ብሎ የተነሳ ሰው ስለመኖሩ ስጠይቅህ እንደሌለ ነግረኸኛል። ቢኖር ኖሮ የርሱን ፈለግ ተከትሎ ነው እልህ ነበር። ከአያት ቅድመ አያቶቹ መሐል ንጉስ እንደነበር ስጠይቅህ የለም ብለኸኛል። ንጉስ ቢኖር ኖሮ የአያቶቹን ንግስና ፈልጎ ነው እልህ ነበር። ነብይ ነኝ ከማለቱ በፊት በውሸታምነት ታውቋት እንደሁ ስጠይቅህ እውነተኛ መሆኑን ገልጸህልኛል። በሰው ላይ ለመዋሸት ያልደፈረ ሰው በአላህ ላይ አይዋሽም። ተከታዮቹ የተከበሩ ሰዎች ናቸው ወይስ ደካሞች ብዬ ስጠይቅህም ደካሞች ናቸው ብለኸኛል። የነብያት ተከታዮች እነርሱ ናቸው። ቁጥራቸው ይቀንሳል ወይስ ይጨምራል ስልም ጠይቄህ እየጨመረ እንደሚሄድ ነግረኸኛል። እምነት እስኪሞላ ድረስ

በባህሪው እንደዚህ ነው። የርሱን ሐይማኖት ከተቀበለ በኋላ የሚያፈነግጥ ይኖር እንደሆነ ጠይቄህ እንደሌለ ነግረኸኛል። እምነት ልቦናን ሲቆጣጠር እንደዚሁ ነው። ሸፍጥ ይፈጽም እንደሆነ ጠይቄህ እንደማይፈጽም ነግረኸኛል። ነብያት ባህሪያቸው እንደዚሁ ነው። ምን እንደሚያዛችሁ ጠይቄህም አላህን በብቸኝነት እንድታመልኩና ከርሱ ጋር ሌላን አካል እንዳታጋሩ እንደሚያዛችሁ፣ ጣኦት አምልኮን እንደሚከለክላችሁ፣ በሶላት፣በምጽዋትና በቁጥብነት እንደማያዛችሁ ገልጸህልኛል። የተናገርከው እውነት ከሆነ ይህ ሰው እነዚህ እግሮቼ የረገጡትን ምድር ይቆጣጠራል። እንደሚነሳ አውቅ ነበር። ነገር ግን ከናንተ መሐል ይሆናል ብዬ አልጠበቅኩም። እንደማገኘው ባውቅ ኖሮ እርሱን ለማግኘት ሁሉንም ዓይነት ጥረት አደርግ ነበር። አብሬው ብሆን ኖሮም እግሮቹን አጥብ ነበር።»

ከዚያም የአላህን መልዕክተኛ ﷺ ደብዳቤ አስጠርቶ አስነበበው። የደብዳቤው ይዘት እንደሚከተለው ነው፡-

*በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው።*

*የአላህ ባሪያና መልዕክተኛ ከሆነው ሙሐመድ ወደ ሮማው ንጉስ ሂረቅል የተላከ መልዕክት ነው። ቅኑን ጎዳና በተከተሉ ሁሉ ላይ ሰላም ይስፈን። ሰላም ታገኝ ዘንድ ስለም። ከሰለምክ አላህ እጥፍ ምንዳ ይሰጥሐል። እምቢ ካልክ ግን የሕዝቦችህን ሁሉ ሐጢአት ተሸካሚ ትሆናለህ።*

﴿ قُلۡ يَٰٓأَهۡلَ ٱلۡكِتَٰبِ تَعَالَوۡاْ إِلَىٰ كَلِمَةٖ سَوَآءِۭ بَيۡنَنَا وَبَيۡنَكُمۡ أَلَّا نَعۡبُدَ إِلَّا ٱللَّهَ وَلَا نُشۡرِكَ بِهِۦ شَيۡـٔٗا وَلَا يَتَّخِذَ بَعۡضُنَا بَعۡضًا أَرۡبَابٗا مِّن دُونِ ٱللَّهِۚ فَإِن تَوَلَّوۡاْ فَقُولُواْ ٱشۡهَدُواْ بِأَنَّا مُسۡلِمُونَ ٦٤ ﴾ آل عمران: ٦٤

*«የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በመካከላችን የጋራ ወደሆነች ትክክለኛ ቃል ኑ፤ (እርሷም) ከአላህ ውጭ ሌላን አካል ላናመልክ፥ በርሱ ላይ አንድንም አካል ላናጋራ፥ ከፊላችን ከፊሉን ከአላህ ውጭ አማልክት አድርጐ*

*ላይይዝ ነው።" በላቸው። እምቢ (ይህንን ጥሪ አንቀበልም) ካሉ፦ "እኛ ሙስሊሞች መሆናችንን መስክሩ።" በላቸው።» (አሊ ዒምራን 64)*

አንብቦ ሲጨርስ ጉርምርምታ ተሰማ። የእስልምና መልዕክት በመሳፍንቱና በልዑላኑ ዘንድ ተቃውሞ ገጠመው። እንድንወጣ አዘዘን። ስንወጣ ለባልንጀሮቼ፦ «የቢን አቢ ከብሻህ (የሙሐመድ) ጉዳይ የበኑ አስፈርን (የሮሞችን) ንጉስ እንኳ እስኪያስፈራ ድረስ እውቅና አገኘ» አልኳቸው። አላህ ለነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ድልን እንደሚያጎናጽፋቸው ከዚህች እለት ጀምሮ እርግጠኛ ሆንኩ። በመጨረሻም እኔው ራሴ እስልምናን ተቀበልኩ።[28]

የቤዛንትይኑ ንጉስ አስተያየት ከንጉሱ የግል አመለካከት የመጣ ሳይሆን ከጅምሩ ትክክለኛ ኃይማኖት ከነበረውና በሰዎች ከተበረዘው ክርስትና በአንድ አምላክ የማመን የጥንት አስተምህሮት የተገኘ ውጤት ነው፡፡ በእርግጥ በወቅቱ ክርስትና በአንድ አምላክ ከማመን ይልቅ ወደ ስላሴና በየቤተክርስትያኑ ወደሚሰቀሉ ምሎስሎች ተሸጋግሮ ነበር፡፡ ከዚህ መበረዝ የተረፉ ትክክለኛ የነብዩላህ ኢሳ (ዐ.ሰ) ተከታዮች ግን የነብዩ ሙሐመድን ﷺ መልዕክት በሠሙ ግዜ ሲጠብቁት የነበረው ነብይ እንደሆነ በማወቅ ወዲያውኑ ወደ ኢስላም ጠቅልለው ገብተዋል፡፡ ለምሳሌ ከመካ ግፈኞች ሸሽተው የሄዱትን የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ተቀብሎ በክብር ያስተናገደው የሀበሻው ንጉስ ይህን ነበር ያለው፡-

"በእኔ እምነትና እናንተ በምትሉት መሀከል የዚህች መስመር ያክል እንኳ ልዩነት የለም"

የሀበሻው ንጉስ እስልምናን መቀበሉ በተለያዩ የታሪክ መዛግብት ላይ የተመዘገበ ሲሆን ሄራክለስ ግን ወደ እስልምና መግባት አለመግባቱ

---

[28] ቡኻሪ 1/4፣ ሙስሊም 2/97-99

በግልፅ የተዘገበ ነገር የለም፡፡ ነገር ግን የዚህ ንጉሥ አድራጎት ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) የማያውቋቸው ሠዎች እንኳን ምን ያህል እንደመሠከሩላቸውና እንደጓጉላቸው ያሳያል፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የመካ ግፈኞች ከትውልድ መንደራቸው እንዲሰደዱ ባደረጓቸው ወቅት እንኳን ንብረቶቻቸውን በአሊይ (ረ.ዐ) አማካኝነት እንዲመለስላቸው አድርገው ነበር የተሠደዱት፡፡ ታማኙ ነብይ፡፡

ገጣሚው ከሚል ኢድፕ ኩርክኩግሉ ከረሡል (ሠ.ዐ.ወ) ምርጥ ባህሪ የማይማሩትን ይህን ሲል በግጥም ይኮንናል፡-

ልባችሁ ማየት ተስኖታል ምንኛ ከሠራችሁ

በምድርም በአኺራም ቅጣቶች አሉላችሁ

እምነት የሌላችሁ የመንፈስ መሀይሞች ናችሁ፡፡

አምላካችን አላህ ሆይ! ነብያችንን ከታዘዙትና የርሳቸውን ባህሪ ካንፀባረቁት ያድርገን! አሚን፡፡

የአላህ መልዕክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) የእዝነትና የርህራሄ ጫፍ ነበሩ፡፡ ከእርሳቸው የእዝነት ሽርፍራፊ እንኳ ለመድረስ የሚቻል አይደለም፡፡ ብዙ በደል ያደረሱባቸውን ጠላቶች እንኳ ወደ ቀጥተኛው መንገድ ለመምራት ከልባቸው ለፍተዋል፡፡ ለበደላቸው ምላሻቸው ለነሱ መፀለይ ነበር፡፡

ዘይድ ኢብን ሀሪሳ በመገረም ይህን ጠየቃቸው፡-

"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እነሡ ይበድሉዎታል፣ እርሶስዎ ግን ለነሱ አላህን ይለምናሉ?"

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ)ም ይህን አሉ፡-

"ሌላ ምንስ ማድረግ እችላለሁ? የተላክኩት ለምህረት እንጂ ለቁጣ አይደለም!" [29]

ይህ ብቻውን ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የነበራቸውን ቅን ልብ አያሳየንምን? ክሪሽና ቡድሀን አምላክ ብለው የሚያስቡ፣ እየሱስን (ኢሳን) የአምላክ ልጅ ብለው የሚጠሩ፣ ፊርዐውን እና ኑምሩድን ጌታ ብለው የያዙ የሰው ልጆች ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አምላክ ነኝ ቢሉ ሳያንገራግሩ ይቀበሏቸው ነበር፡፡ ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ግን፡- “የአላህ መልእክተኛ የሆንኩ ሰው እንጂ ሌላ ምንም አይደለሁም” ሲሉ ያስተምሩ ነበር፡፡

﴿ قُلْ إِنَّمَآ أَنَا۠ بَشَرٌ مِّثْلُكُمْ يُوحَىٰٓ إِلَيَّ أَنَّمَآ إِلَٰهُكُمْ إِلَٰهٌ وَٰحِدٌ فَمَن كَانَ يَرْجُوا۟ لِقَآءَ رَبِّهِۦ فَلْيَعْمَلْ عَمَلًا صَٰلِحًا وَلَا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِۦٓ أَحَدًۢا ﴿١١٠﴾ ﴾ الكهف: ١١٠

«እኔ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት. ወደኔ የሚወረድልኝ ቢጤያችሁ ሰው ብቻ ነኝ፤ የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፤ መልካም ሥራን ይሥራ፤ በ□ታውም መገዛት አንድንም አያጋራ. በላቸው፡፡» **(አል-ከህፍ፡ 110)**

አንድ ሠው ወደ እስልምና በሚገባበት ወቅት በሚያሠማው የምስክርነት ቃል ላይ ‹‹ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛና ባሪያ ነው›› እንዲል ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) አስረግጠው ይናገሩ ነበር፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ዘወትር ከሠው የተለየ ልዩ ኃይልና መለኮታዊነት እንደሌላቸው ያስተምሩ ነበር፡፡ ለምሳሌ በአንድ ወቅት ይህን ብለዋል፡-

"ማንም ቢሆን በሠራው ብቻ ጀነትን አያገኝም" ተከታዮቻቸው በሙሉ በመገረም፡-

---

[29] ሙስሊም፡ ብር አቡ ያላ አል-ሙሠናድ xl.35

"የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እርሶም ቢሆኑ?" ሲሉ ጠየቁ፡፡ እሳቸውም ይህን ሲሉ መለሱ፡-

"አዎ፤ እኔን ጨምሮ…! የአምላኬ እርዳታና እገዛ ባይጨመርበት ኖሮ፣ ጌታዬ በምህረቱ፤ በአዛኝነቱ ባይከብበኝ ኖሮ ጀነትን ባላገኝሁ፣ ስራዎቼ የጀነትን ዋጋ ባልቻሉ ነበር…."[30]

ይህ መልዕክት በጥልቅ ሀቀኝነትና ታማኝነት የተሞላ እውነተኛ መልዕክት ነው፡፡ ትክክለኛ የቁርአንን አስተምህሮት መረዳት ከሻን ወደ ረሡል (ሠ.ዐ.ወ) ባህሪያት መጠጋት መቻል አለብን፡፡

የሁሉም ነብያት መልእክት በቦታና በጊዜ የተገደበ ነው፡፡ ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ሲቀሩ፡፡ እርሳቸው ግን መላውን የሠው ዘር የመምራት ኃላፊነት ከአላህ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከመምራትም በተጨማሪ ህዝባቸውን በባህሪ የማረቅና የማስተካከል፡፡ ቁርዓን ከተወረደላቸው የመጀመሪያው ቀን ጀምሮ እስከ መጨረሻዋ መልዕክት ድረስ ጥቃቅን ጉዳዮችን ሳይቀር አስተምረዋል፤ ሀገር ገንብተዋል፤ ትውልድ ቀይረዋል፤ ተከታዮቻቸውም የርሣቸውን ተግባራት አንዷት ሳትቀር በአስተማማኝ ሰንሰለት አስተላልፈውታል፡፡ ይህም የመጨረሻው ትውልድ ሳይቀር ተምሳሌቱ ያደርጋቸው ዘንድ ያለመ የአላህ ጥበብ ነው፡፡

አረቦች በባህላቸው እጅግ በሚሣሱለት ነገር እንጂ በሌላ አይምሉም፡፡ አላህም በቅዱስ ቁርዓኑ በተለያዩ ትልቅ ቦታ ያላቸው ነገሮች ሲምል እናስተውላለን፡፡ አምላካችን አላህ (ሡ.ወ) በነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) እንጂ በሌላ ነብይ ሲምል አናገኝም፡፡

---

[30] ቡኻሪና ሙስሊም

ቱርካዊው ገጣሚ ሼኽ ጋሊብ ይህን ሁኔታ እንዲህ ሲሉ በግጥም ይገልፁልናል፡-

የንጉሶች ንጉስ

ለተቸገረ ሰው መንፈስ የምታድስ

ሰብአዊነት የምታውቅ ከሁሉ ምትበልጥ

ሁሌም ቀናተኛ መንገድህ ሚመረጥ

መሪያችን አህመድ

ንጉሱ ሙሐመድ

ሙሐመድ ሙስጠፋ

አንቱ የአለም ተስፋ

አላህ የመረጦት የሰው ልጆች መሪ

ከሁሉ በላጩን ጀነትን አብሳሪ

ሌላው የነብያችን ልዩ መገለጫ አምላካችን አላህ ከሌሎች ነብዮች በተለየ መልኩ በተለያዩ የመዓረግ ስሞች የጠራቸው መሆኑ ነው፡፡

ለምሳሌም በቅዱስ ቁርዓን ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) በነዚህ ስሞች ተጠቅሰው ይገኛሉ፡፡

"ነብዩ ሆይ" "ረሡል" "ሙዘሚል" "ሙደሲር"

የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ስም በጠራንበትም ሆነ ሲጠራ በሠማንበት ወቅት በእሳቸው ላይ ሠለዋት ማውረድን መርሳት ፈፅሞ የለብንም፡፡ ምክንያቱም በዛች የጭንቀት ቀን ሽፈአቸው (ጥብቅናቸው) ያሻናልና፡፡

# ምእራፍ ሶስት
# የእዝነቱ ነብይ ምርጥ ባህሪያት

በታሪክ ሂደት ውስጥ እንደ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እያንዳንዱ ድርጊትና የየደቂቃው ህይወቱ የተዘገበ አንድም ሠው ሆነ ነብይ የለም፡፡

አኗኗራቸው፣ አነጋገራቸው፣ ስሜታቸው፣ ቃላቶቻቸው ሁሉም ነገር ተመዝግቧል፡፡ ይህም ለታሪክ ታላቅ ግብአት ሆኗል፡፡

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት ለትውልድ ሁሉ ተምሳሌት ነው፡፡ እስከ መጨረሻው ትውልድ ድረስ የርሳቸውን ህይወት መርማሪና ምሳሌነታቸውን ተከታይ ነው፡፡ በቅዱስ ቁርአን አል-ቀለም ምዕራፍ እንዲህ ተብሏል፡፡

﴿ وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٍ ﴿٤﴾ ﴾ القلم: ٤

«አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ፡፡» **(አል-ቀለም 4)**

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ቅዱስ ቁርዓንን በቃል አስተማሪ ብቻ ሳይሆኑ ቁርአን ላይ የተፃፈውን በተግባር ማሳያ ነበሩ፡፡ ጃቢር እንደዘገበው ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይህንን ብለዋል፡-

"ልዑል አላህ (ሡ.ወ) የላከኝ ስነ ምግባርን እንዳሟላ ነው"[31]

---

[31] ሙወጠእ ሁስኑ አል ኹሉቅ 8፡ አል-በይሀቅ አል-ሱነን አል-ኩብራ x 191፣ አል-ጦበራኒ አል-ሙዕጀም አል-አውሰጥ VII74

አብዱላህ ኢብን ሠላም (አይሁድ የነበረና ወደ እስልምና የገባ) ነብያችንን ሙሀመድ (ሠ.ዐ.ወ) ባገኛቸው ወቅት ፊታቸውን በመመልከት "ይህን አይነት ገፅታ ያለው ሠው ፊፀሞ ዋሾ ሊሆን አይችልም።"[32] በማለት ነበር በቀጥታ ወደ እስልምና የገባው።

## የእዝነቱ ነብይ የውስጥ ንፅህና (የነፍሲያቸው ጥራት)

ከዚህ በፊት ለመጥቀስ እንደተሞከረው ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ከአላህ (ሡ.ወ) የተላኩልን መለኮታዊ ስጦታችን ናቸው።

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እያንዳንዷ እንቅስቃሴና የእለት ተእለት ህይወታቸው እውነተኛ እስልምናን መኖር ለሚፈልጉ ሠዎች ተምሳሌት ነው።

ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት መማር የምንችላቸው ቁም ነገሮች፦

1. አንዳንድ ተግባራት በነብያችን አቅም ብቻ ሊፈፀሙ መቻላቸው። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይህን አስመልክቶ ለተከታዮቻቸው ደጋግመው ማስጠንቀቂያ ይሠጡ ነበር። ለምሳሌ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የውስጥ እግራቸው እስኪሰነጠቅ ድረስ ለሊት ቆመው ይሰግዱ ነበር። ለተከታታይ ቀናት እህል ሳይቀምሱ ይፆሙ ነበር።

2. አንዳንድ የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ድርጊቶች ለእሳቸው ብቻ የተሰጡ መሆናቸው። ለምሳሌ ከ4 በላይ ማግባትና ምንም አይነት ምፅዋት ለራሳቸውም ሆነ ለልጆቻቸው መከልከል። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ከጦርነት በሚገኝ ምርኮ ክፍፍል ላይ እጅግ ጠንቃቃ ነበሩ። እጅግ ፍትሀዊም

---

[32] ቲርሚዚ ቂያማ 42፡42፣ ኢብን ማጃህ ኢቃማ 174 ዳሪሚ ሶላት 156 አህማድ ኢብን ሀንባል አል-ሙስናድ V:451

ጭምር፡፡ ይህንንም እንዳስጠበቁ እስከ መጨረሻዎቹ እስትንፋሳቸው ቆይተዋል፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አምላካችንን አላህ (ሱ.ወ) ሊገናኙ በነበረበት የመጨረሻው ወቅት እጅግ ታመው ነበር፡፡ በከባድ ህመም መሀከል ግን ለባለቤታቸው አይሻ (ረ.ዐ) በቤት ውስጥ ያለውን ከ6-7 ዲናር ለችግረኞች እንድታከፋፍል ነገሯት፡፡ ከቆይታ በኋላ ዲናሮቹን ማከፋፈሏን ሲጠይቋት አይሻ ረስታው ነበር፡፡ ምክንያቱም እሳቸውን በመጠበቅ ተጠምዳ ነበርና፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ሀቢቡና መሐመድም(ሠ.ዐ.ወ) ይህን አሉ፡-

"ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ እነዚህ ዲናሮች ለችግረኞች ሳያከፋፍል አምላኩን መገናኘት አይሻም፡፡"

ከዛም በመዲና ለነበሩት 5 የአንሷር (ረዳቶች) ቤተሰብ አከፋፈሉና ይህን ተናገሩ፡-

"አሁን ምቾት ይሠማኛል"[33]

ከዛም ቀለል ያለ እንቅልፍ ወሰዳቸው፡፡ ኡበይዱላህ ኢብን አባስ እንዲህ ሲል አውግቷል፡- አንድ ቀን አቡዘር ይህን አለኝ፡-

የወንድሜ ልጅ ሆይ! አንድ ታሪክ ላጫውትህ፡፡

አንድ ጊዜ ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ጋር ነበርኩ፡፡ እጄን በመያዝም ይህን አሉኝ፡-

"አቡዘር ሆይ! የኡሁድ ተራራ ወደ ወርቅ ቢለወጥልኝ እንኳን በአላህ መንገድ ነው የማጠፋው፡፡ አንዲት "ቂራጥ"[34] እንኳ አስቀርቼ አልሞትም፡፡" እኔም አልኩ፡-

---

[33] አህመድና ኢብን ሂባን

"የአላህ መልእክተኛ ሆይ "ቂራጥ" ነው ቂንጣር[35] የማይተውት"

"አቡዘር ሆይ፣ እኔ እቀንሳለሁ። አንተ ትጨምራለህ! እኔ መጪውን አለም እፈልጋለው አንተ ይህችን አለም ትፈልጋለህ! ፈፅሞ አንዲት ቂራጥ እንኳ አላስቀርም። ቂራጥ! ቂራጥ! ቂራጥ!

"ቂራጥ" የምትለውን ቃል 3 ጊዜ ደጋገሟት[36]

ይህ የነብያችን ንግግር የሳቸውን ፍፁማዊ ደረጃ ያሳየናል። ይህንን ፍፁማዊነት ተከታዮቻቸው መድረስ አይጠበቅባቸውም። የሣቸው ከፍተኛ የሆኑ የነብይነት ስኬቶች ሁሉ ይሞከሩ ቢባል ምናልባትም ለህብረተሰቡ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አንዳንድ ድርጊቶች ከሠው ልጅ አቅም በላይ ናቸውና።

ለዚህም ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይህን ይሉ ነበር።

"እኛ ነብዮች ምንም አይነት ንብረት (ቁስ) ትተን አናልፍም"[37] ስለዚህ ይህ ከፍተኛ ልግስና ሁሉንም ሰው ላያጠቃልል ይችላል።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በሌላ ንግግራቸው እንዲህ ይላሉ፦ "ለአንድ አማኝ ድህነቱ ስጦታው ነው።"[38] በድህነታቸው አያፍሩም ነበር። ይህ ማለት ግን ረሡል (ሠ.ዐ.ወ) ድህነትን ያበረታታሉ ማለት ወይም ለህብረተሰቡ ደሀ መሆንን እየመከሩ ነው ማለት አይደለም። እንደውም ይህን ሲሉ ያሥተምሩ ነበር፦

---

[34] ቂራጥ እጅግ ትንሽ የሚዛን ልኬት የአምስት ባቄላ ክብደት= ግራም

[35] ቂንጣር ቂራጥን እንደ ግራም ከወሰድን ቂንጣር ኪሎ ግራምን ይተካልናል።

[36] ቡኻሪና ሙስሊም

[37] ቡኻሪና ሙስሊም

[38] አል-ዳይላሚ አል-ፊርደውስ 11:70

"ከተቀባዩ የሠጪው እጅ በላጭ ነው"[39]

በዚህም አባባላቸው ሠዎች ሀላል በሆነ (በተፈቀደ መልኩ) ሀብትና ንብረትን) እንዲያፈሩ ያበረታቱ ነበር፡፡

ስለዚህም የተጠቀሡ ምሳሌዎች በሙሉ ድህነትን ለማበረታታት ሳይሆን ለአላህ ውሳኔ እጃችንን እንድንሠጥና በሡ እቅድ እንድንስማማ ለማስተማር ነው፡፡

3. በ"ዙህድ" (ልብን ከዚህች ዓለም ጋር በማለያየት) መኖርና ተቅዋን (አላህን በመፍራት ከአሻሚ ነገሮች መራቅን) ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባህሪ መማር እንችላለን፡፡ ግን ይህን ስንል መቶ በመቶ ከአለማዊ ህይወት መውጣትን ወይም የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ደረጃ ላይ ለመድረስ የማይችሉትን መሆንን እየመከርን አይደለም፡፡ አማኞች በሙሉ ይህችን አለም የሚረሡና የሚተዉ ከሆነ ምድራችን የከሀድያን መፈንጫና የአማኞች መጨቆኛ ትሆናለች፡፡

ስለዚህም ዘሁድ እና ተቅዋ ከቁሳዊ አለም መገለል ሳይሆን በመንፈስ መምጠቅ ነው፡፡

ጀላሉዲን ሩሚ እንዲህ ብለዋል፡- “በዚህች ዓለም ህይወት አለቅጥ መዘፈቅ ትርጉሙ መለኮታዊ ህይወትን አለማወቅ እንጂ ንብረት ማፍራት፣ ማግባት ወይም መልበስ እንዳይመስላችሁ! ይህን በደንብ ተረዱ"

ከፍተኛ ገንዘብ ኖሮት የንብረቱ ፍቅር በልቡ ያልገባና መልካምን የሠራ ሠው ፈፅሞ ከ"ዙህድ" እና "ተቅዋ" ፅንሰ ሀሳብ ያልወጣ ሲሆን፣ ጥቂትም ንብረት ኖሮት የሡ ፍቅር ከልቡ የተቀመጠና አላህን ያስረሳው ሠው እሱ ከስሯል፡፡

---

[39] በኂሪና ሙስሊም

ነብዩላህ ሡለይማን (ዐ.ሠ)፣ እንዲሁም የነብያችን ወዳጆች አቡበክር (ረ.ዐ)፣ ኡስማንን (ረ.ዐ)፣ ጠልሀ (ረ.ዐ) እና አብዱረህማን ኢብን አውፍ (ረ.ዐ) የዚህ ሚዛናዊነት ምርጥ ምሳሌዎች ናቸው።

ተቅዋ የአላህን ውሳኔ አሜን ብሎ በመቀበል ንብረትንም ሆነ ችግርን ከአማኞች ጋር መጋራትን ያጠቃልላል።

አይሻ (ረ.ዐ) ይህን አስተላልፈዋል፡-

"ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ለሁለት ቀናት በተከታታይ ዳቦ እንኳን ሳይመገቡ ነው ከዚህ አለም የተለዩት"[40]

አነስ (ረ.ዐ) ደግሞ ይህን አስተላልፈዋል፡-

"ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ዳቦ ብቻና ሊበላሽ የደረሰ ስብ ብቻ ተጋብዘው ተቀብለው ያውቃሉ። የጋባዦቹን ቀልብ ላለመስበር። በቦታውም በነፃነት ተጫውተው ይመለሡ ነበር።"[41]

ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ሀላል የሆነን ምግብ ከመብላት ራሳችንን አቅበን እንዳንቸገር አስጠንቅቀውናል። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ራሳቸው ሀላል ምግቦችን በበቂ ሁኔታ ይመገቡ ነበር። ሆኖም ሀላል ስለሆነ ብቻ እስኪጠግቡ መብላት ፈፅሞ የነብያችን ፈለግ አይደለም።

በአንድ ወቅትም አንድ ሰው ከልክ በላይ ሲመገብ ተመልክተው፡- "ሆድህ እስኪሞላ ድረስ (ያለ ልክ) አትመገብ። አለልክ የሚጠግቡ ሰዎች ረጅሙን ረሀብ ይራባሉና" ሲሉ መክረውታል።[42]

---

[40] ቡኻሪና ሙስሊም

[41] ቡኻሪ ጂሀድ 89 ቲርሚዝ ቡዩእ፣ 7 ነሳኢ ቡዩእ 58፣ ኢብን ማጃህ ሩሁን፣ ዳረሚ ቡዩእ 44፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል ሙሥናድ I 236.

[42] ቲርሚዝ ሲፈቱል ቂያማ 37፣ ኢብን ማጃህ አቲማህ 50፣ አል ጠበራኒ አል ሙዕጃም አል-አውሰጥ IV 249፣ አል በይሀቅ ሹአብ አል ኢማን V፡27

በሌላ ሀዲስ "ማንም ቢሆን ከጨጓራ በላይ አስቸጋሪ መጋዘን አልሞላም። ትንሽ መጠን ምግብ ሠው ቆሞ እንዲሄድ ለማስቻል በቂ ነው። አንድ ሠው ሲመገብ ከሆዱ ሲሶውን ለምግብ፣ ሲሶውን ለውሃ፣ ሲሶውን ደግሞ በቀላሉ መተንፈስ እንዲያስችለው ክፍት መተው አለበት"[43]

ይህ ምክር ፍፁም መልካምና ጥበበኛ በሆነ መንገድ ደህና ሀብታሙን ያቀራርባል። ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.0.ወ) መራብን ሆነ መጥገብን ከልክለው ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተስማሚ የሆነ መሀከለኛ አመጋገብን መርጠውልናል።

እስልምና ከሠው ልጅ ታሪክ የመደብ ልዩነትና አጥፍቶ ሁሉንም በአንድነት ማስተሳሰር የቻለ ኃይማኖት ነው።

"ሀገር አስተዳዳሪ (ኸሊፋዎች) በጀርባቸው ምግብ ተሸክመው ለድሆች ያደረሱበት ታሪክ ተመዝግቧል። ለአቅመ ደካሞች ምግብ አብስለው ማብላታቸውም የሚታወቅ የታሪክ ክስተት ነው"[44]

ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.0.ወ) ዙህድን እጅግ ውብ በሆነ መልኩ አብራርተውታል።

"ዙህድ ማለት የተፈቀደላችሁን (ሀላል ነገር) በራሳችሁ ላይ ክልክል (ሀራም) ማድረግ አይደለም። ሀብትን መጥላትም አይደለም። ይልቁንም ዙህድ ማለት በእጃችሁ ካለው ነገር ይልቅ ከአላህ እጅ ላይ ባለው

---

[43] ቲርሚዝ፣ኢብን ማጃህ አላማህ 50 አህመድ

[43] ሱዩጢ ታሪክ አል- ኹለፋ ገፅ 91-92

[44] ሱዩጢ ታሪክ አል- ኹለፋ ገፅ 91-92

መተማመን እንዲሁም በአስቸጋሪ ግዜ ለፅናታችን እንደምንሸለም መተማመን ነው።[45]

ለዙህድ ትክክለኛ መረዳትና በልብ መኖር የዘወትር ምሳሌ መሆን የሚችሉት ነብያችን ሙሀመድ (ሠ.ዐ.ወ) ናቸው።

ዙህድ በህይወት ውስጥ ደስታን የሚያመጣ ነው። ልባችን ለዚህች ጠፊ ዓለም እንዳይገዛ ከመጠን ያለፈ ፍላጎታችንን በመቆጣጠር በዚህች ምድር ደስታ ውስጥ ከመጥፋት ይልቅ ወደ አላህ በመጠጋት፣ ከአላህና ከረሡል በላይ ምንንም ነገር ባለመውደድ፣ አላህን ከመገዛት የሚያዘናጉ ነገሮችን በማስወገድ የመጪውን አለም ማስቀደም ነው። ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦

"ዙህድ ልብን ያረጋጋል። ደስተኛ ያደርጋል፤ የዚህች አለም ፍቅር ግን ሀዘንንና ህመምን ያስከትላል"[46]

በሌላ ሀዲስ፦ "ለዚህች አለም ፍላጎት አይኑርህ። አላህ ይወድሀል። በሠዎች እጅ ባለም ነገር ላይ ፍላጎት አይኑርህ - ሠዎች ይወዱሀል።"[47] በሌላ ሀዲስ፦

"ነጭ በጥቁር ላይ የበላይ አይደለም። የትኛውም ዘር በየትኛው ላይ የበላይ አይደለም። መበላለጥ ያለው (መመዘኛው) በተቅዋ ነው"[48]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይህንንም ይናገሩ ነበር፦

---

[45] ቲርሚዚ ዙህድ 29 ኢብን ማጃህ ዙሁድ 1 ፣አል-ጠበራኒ አል ሙእጃ አል አውሳጥ III 57፣አል በይሀቂ ሹአብ አል-ኢማን VII 215

[46] አህመድ ገፅ 47 (አል-ቁዳይ)

[47] ኢብን ማጃህ ዙህድ 1፣ አል ሀኪም አል ሙስተድራክ IV348 አል ጠበራኒ አል ሙጀመዕ አል-ከቢር VI 193 አል-በይሀቅ ሹአብ አል ኢማን VII 344

[48] አህመድ ኢብን ሀንባል አል ሙሠናድ V 158፣ አል-በይሀቂ ሹአብ አል-ኢማን IV 289.

"የአላህ መላዕክት ያዘዘኝ ሀብት እንዳካብት ወይም ነጋዴ እንድሆን አይደለም። ይልቁንስ የሡን ልዕልና እንድናገር፣ በሡ መንገድ እንድኖር እና እንዳገለግለው ነው።[49] በሌላ ሀዲስ፦

"ለሠላት በምትቆሙበት ጊዜ የመጨረሻችሁ ሠላት የሆነ ያህል አሳምሯት። ነገ የምትፀፀቱበትን ነገር አትናገሩ፤ ግዴለሾች የሚመኙትን ሁሉ አትመኙ።[50]

በአንድ ወቅት ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይህን ተጠየቁ፦

"የአላህ ምርጥ ሠዎች እነ ማናቸው?"

"ንፁህና ምርጦቹ ራሳቸውን ከሀጢያት፣ ከጥርጣሬ፣ ከማታለል፣ ከመዋሸትና ከቅናት ያፀዱ ናቸው።"[51]

ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ክልክል (ሀራም) እና የተፈቀደ (ሀላል) ነገሮች ላይ እጅግ ጠንቃቃ ነበሩ። እንደውም ከሚያጠራጥሩ ነገሮች ራሳቸውን ያርቁ ነበር።

አንድ ጊዜ ሀሠን (የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የልጅ ልጅ) ህፃን በነበረበት ወቅት በመስጂድ ተቀምጦ የዘካ ቴምሮች እንዴት እንደሚከፋፈሉ እየተመለከተ ነበር። ከዛም አንዲት ቴምር አንስቶ ጎረሰ። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ)

---

[49] ኢብን አቢ አሲም፣ ኪታብ አል-ዙህድ I 391 አል-ደይላሚ አል-ፊርዶስ IV 95፣ አቡ ኦአይም አል-ኢስ በሀኒ ሂልያቱ አል-አውሊያ II 131፣ ኢብን አዲይ አል-ካሚል ፊ አል ዱ አፋእ III68.

[50] አህመድ ኢብን ሀንባል አል ሙሠናድ V 412 (ኢብን ማጃህ ዙህድ 15)አል ጠበራኒ አል ሙጀማል አል ካቢር IV 154.

[51] ኢብን ሂባን አል ሠሂህ II 76 ኢብን አቢ ሻይባህ አል ሙሳነፍ VI 167

[51] ቡኻሪ ዘካ 60 ሙስሊም ዘካ 161 ነሳኢ ጠሃራ 105፣ ሙዋጣእ ሠደቃ 13፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሰናድ I 200

"አውጥተህ ጣለው! አውጥተህ ጣለው! እሱን ቴምር አውጥተህ ጣለው! እኛ ሰደቃ እንደማንበላ አታውቅምን?"[52] በማለት ቴምሩን ከአፉ አውጥቶ መሬት እንዲጥል አደረጉት፡፡

መውላና ጀላሉዲን ሩሚይ ይህን ይላሉ፡- "ስንመገበው የሚያስደስተንና ለአምልኮ የሚያነሳሳን ምግብ ሀላል (የተፈቀደ) ነው፡፡ ስንመገበው የሚያሳንፈን፣ ከአምልኮ የሚያዘናጋንና ቀልባችንን የሚያደርቅ ምግብ በእኛ ላይ ሀራም (የተከለከለ) ነው፡፡

"በህይወታችሁ ውስጥ የተፈቀዱ ነገሮችን ብቻ ተጠቀሙ፡፡ ከተከለከሉና ከአጠራጣሪ ነገሮች ራሳችሁን አርቁ፡፡ በዚህም የቀልብ ምጥቀትንና የእምነትን ጥፍጥና ታገኛላችሁ፡፡ አምላካችን አላህ (ሡ.ወ) በቁርአኑ ይህን ብሏል፡-[53]

﴿ قَدْ أَفْلَحَ ٱلْمُؤْمِنُونَ ۝١ ٱلَّذِينَ هُمْ فِي صَلَاتِهِمْ خَٰشِعُونَ ۝٢ ﴾ المؤمنون: ١ - ٢

«ምእመናን ፍላጎታቸውን ሁሉ በእርግጥ አገኙ. (ዳኑ)፡፡ እነዚያ □እነሱ በስ□□ታቸው ውስጥ. (አላህን) ፈሪዎች» **(አል-ሙእሚኑን፡ 1-2)**

ሐይማኖት በውስጡ ብዙ ነገሮችን ያካተተ እምነት ሲሆን አላማውም በመጪው አለም ደስታን መስጠት ብቻ እንደሆነ ብዙሀን የማህበረሰባችን ክፍል ያምናል፡፡ ግና ይህ ስህተት ነው፡፡ ሀይማኖት በመጪው ዓለም ደስታን ከመፍጠርም በላይ በዚህች ዓለምም የተረጋጋና ሠላማዊ የሆነ ማህበራዊ ህይወት የመፍጠር አላማ አለው፡፡

በአንድ ምሽት ኡመር (ረ.ዐ) እንደተለመደው በመዲና መንገዶች ላይ እየተንሸራሸሩ ነበር፡፡ ሳያስቡት የአንድ እናትና ልጅ ንግግር ወደ

---

[52] ቡኻሪ ዘካ 60 ሙስሊም ዘካ 161 ነሳኢ ጠሃራ 105፣ ሙዋጣእ ሠደቃ 13፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሰናድ I 200

[53] ሩሚ ጀላሉዲን ማትናዊ ማናዊ (ጣህራን 1378 VI 1645-48 ከን ሠፊቅ መስነቪ ቴርሴሜሲ (ኢስታንቡል 1997) V II ገፅ 120

ጆሯቸው ገባ። ከዛም ንግግሩ ስለሳባቸው ጠጋ ብለው ማዳመጥ ያዙ። እናትየው ይህን አለች፡-

"ነገ በምንሸጠው ወተት ላይ ውሃ ጨምሪበት"

ልጅ! ‹‹እናቴ ሆይ! ኸሊፋው በወተት ላይ ውሀ ጨምሮ መሸጥን እንደከለከሉ አልሰማሽምን?" እናት፡- በመናደድ ጮክ ብላ፡-

"አሁን በዚህ ምሽት እኛ እዚህ ወተት ውስጥ ውሃ መጨመራችንን ከሊፋው በምን ያውቃል?››

ልጅ ግን ቀልቧና ልቧ በአላህ ፍርሀት ህያው ነበርና ይህን አለች፡- "እናቴ፣ እሺ ዑመር (ረ.ዐ) አላየም እንበል፤ ሁሉን አዋቂ ፈጣሪ አላህ (ሱ.ወ)ስ የማያይ ይመስልሻል? ድርጊታችንን ከሰው መደበቅ እንችል ይሆናል። ከአላህ ግን ፈፅሞ ምንም መደበቅ አንችልም።››

የአማኞች መሪ የሆኑት ዑመር (ረ.ዐ) በዚህች ሴት ተደሰቱ። የልጃቸው ሚስት እንድትሆንም ፈለጉ። ከዚህ ጥምረትም ዑመር ኢብን አብዱልአዚዝ (በብዙዎች ትክክለኛው 5ተኛ ኸሊፋ እንደሆኑ የሚታመኑት) ተገኙ።

በዚህች አለም ላይ ደስተኛ ለመሆን የተፈቀዱና የተከለከሉ ነገሮችን ድንበር መጠበቅ መቻል አለብን። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሲናገሩ፡-

"ልባችሁ የተጠራጠረበትን ነገር ተዉ፣ ጥርጣሬ የሌለበትን ነገር ብቻ ፈፀሙ።" [54]

ይህ ማለት ግን ከተፈቀደልን ነገርም ራሳችንን መከልከል ወይም በተፈቀዱ ነገሮች ላይ ብዥታን መፍጠር አይደለም።

---

[54] ቡኻሪ ቡዩ 3 ቲርሚዝ ቂያማ 60 አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠነድ III 153.

ኢስላም ምንግዜም ቢሆን ሚዛናዊነትንና መሀከለኛውን መንገድ ይሻል፡፡ አላማውም ሠዎችን መከልከልና ማስጨነቅ አይደለም፡፡ ደስታን፣ የተረጋጋ ህይወትንና ንፅህናን ማምጣት እንጂ፡፡ ደስተኛና ሠላማዊ ልብ ለማግኘት ፍፁም ወደ ሆነው የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ልብ መመልከት እና እርሱን መከተል አለብን፡፡

ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ፍፁም ከሀጢያት የፀዱ ነበሩ፡፡ ሆኖም ግን እግራቸው እስኪሠነጠቅ በለሊት ይሠግዱና እስኪደክማቸው ድረስ ቁርዓን ይቀሩ ነበር፡፡ አላህን ከማንም በላይ ይፈሩ፣ ይወዱና ያስታውሱ ነበር፡፡

ሠላት (ስግደት) ከአምላካችን ጋር የምንገናኝበት መድረክ እንደመሆኑ መጠን አማኞች ከግዴታ ሠላት በተጨማሪ የፍቃደኝነት (ሡና) ስግደቶችን ደጋግመው ይሰግዳሉ፡፡ ነፍስያችን ሠላትን እንዳንሰግድ ልታከላክለን ትችላለች፡፡ ምክንያቱም ወደ አለማዊ ነገሮች ልትመራንና ከአላህ ልታርቀን ትሻለችና፡፡ በዚህ ብቻ እንኳን ኢስላም ትክክለኛው ሀይማኖት፤ ሠላትም የአምልኮዎች ቁንጮ መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡

ነፍስያውን ማሸነፍ ያቃተውና እሷን የተከተለ ሰላትን ይርቃል፤ በነፍስያው ላይ ድል ያደረገ ሠላትን ያዘወትራል፤ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይህን እውነት እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል፡-

"ሁለት ሠዎች በተመሳሳይ ቦታ እየሠገዱ እንኳን ሠላታቸው የሠማይና የምድርን ያህል ይራራቃል፡፡"[55]

ፆምን ብንመለከት ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለተከታታይ ቀናት ያለ ምግብ ይፆሙ ነበር፡፡ ባልደረቦቻቸው ይህን ማድረግ ሲሹ፡-

---

55 አቡ ሠዒድ አል ሻሺ (ዲ335) ሙሠነድ አል ሻሺ I.86.

"እንደኔ ልታደርጉ አቅሙ የላችሁም።"[56] ይሏቸው ነበር። ኢብን አባስና አባታቸው (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፦-

"ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለተከታታይ ቀናት ከፆሙ በኋላ በሚያፈጥሩበት ወቅት እንኳን በቤታቸው ያለው ምግብ ደረቅ ዳቦ የሚሆንበት ጊዜ ብዙ ነበር"[68]

አነስ ኢብን ማሊክ እንደዘገቡት በአንድ ወቅት እናታችን ፋጡማ (ረ.ዐ) ለነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ዳቦ ጋግራ ይዛ መጣች።

"ይሄ ምንድን ነው?" ሲሉ ጠየቋት

"ይሄ ቆንጆ ዳቦ ነው፡ ለእርሶ ሳላመጣ መብላት አልቻልኩም አለች።" እሳቸውም፦- "ይህ አባትሽ በሶስት ቀን ውስጥ የተመገበው የመጀመሪያው ምግብ ነው" አሉ።[57]

አቡሁረይራ እንዳስተላለፉት ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ከረሀብ የተነሳ ከሆዳቸው ላይ ድንጋይ ያሥሩ ነበር።[58]

የፆም ትልቁ አላማው እና ዋጋው ከነፍስያ ጋር መታገል እና ስሜትን አሸንፎ አላህን መገዛት ነው።

አምስተኛው የኢስላም መዓዘን የሆነው ሀጅ ለአማኞች በአላህ ላይ መተማመንን (ተወኩል) ማስተማር ዋንኛ አላማው ነው። በሀጅ ስነስርዓት ወቅት ከኢብራሂም (ዐ.ሠ) እና ልጃቸው ኢስማኤል (ዐ.ሠ) ውስጣዊ ጠላትን (ነፍስያን) መዋጋትንና ማሸነፍን እንዲሁም ውጫዊው ጠላትን (ሸይጧንን) መርታትን እንማራለን።

---

[56] ቡኻሪ ፆም 20 ሙስሊም ፆም 55 ሙዋጣእ ፆም 37 አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠነድ II 128

[57] ኢብን ሰዓድ አል-ጦበቃት አልኩብራ 1,400

[58] ያለፈው ምንጭ

በሀጅ ስርዓት ላይ ከሀብታም እስከ ድሀ፣ ከጥቁር እስከ ነጭ፣ ከሽማግሌ እስከ ወጣት አንድ አይነት ነጭ ጨርቅ አገልድመው እኩልነትን፣ አንድነትንና የእምነት ወንድማማችነትን በተግባር ያሳያሉ፡፡

ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) በመጨረሻው ሀጅ ላይ ባደረጉት ንግግር ለሙስሊሞች ፍቅርን ሰብከዋል፡፡ ያኔ የሙስሊም ወንድማማችነትና ፍቅር መሠረት ተጣለ፡፡ ለምሳሌ ኡመር (ረ.ዐ) ሀጀረል አስወድን የመሳምን እድል ለሌሎች ሙስሊሞች ሲሉ አሳልፈው ሰጥተዋል፡፡

የሀጅ ስነ ስርዓት የሚከናወንባቸው ቦታዎች ከፍተኛ መንፈሳዊ ስፍራ ያላቸው ናቸው፡፡

ለምሳሌ የአረፋ ተራራ ወደ አላህ መጠጊያና ምህረት ማግኛ ቦታ ነው፡፡ ሙዝደሊፋ የእዝነት ቦታ ነው፡፡ በቅዱስ ቁርዓኑም አል-ማዕሸረል ሀረም በማለት ጠቅሶታል፡፡[59]

ሚና ለአላህ የመገዛት ምልክት የሆነ ቦታ ሲሆን ኢብራሂም፣ እስማኤል እና እናታችን ሀጀር ሸይጧንን ያሸነፉበት እና ለአላህ እጅ መስጠታቸውን ያሳዩበት ቦታ ነው፡፡

ካዕባ በሠላት ወቅት ፊታችንን ወደርሱ እንድናዞር በአላህ የታዘዝንበት ስፍራ ነው፡፡

﴿ كَلَّا لَا تُطِعْهُ وَٱسْجُدْ وَٱقْتَرِب ۩ ﴿١٩﴾ ﴾ العلق: ١٩

ይከልከል፤ አትታዘዘው፤ ስገድም፤ (ወደ አላህ) ተቃረብም፡፡›› **(አል-ዐለቅ 19)**

ካዕባ የሙስሊሙ አንድነትና የልብ ምት ያለባት ቦታ ናት፡፡

---

[59] አል-በቀራ 198

ከመካ በኋላ በሀጅ ወቅት የምትጎበኘው መዲና የፍቅር ተምሳሌት ናት፡፡ በዚህች ከተማ ነው ልቦች ከፍተኛውን የፍቅር ደረጃ ላይ የደረሱት፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ‹‹ተወዳጁ ወይም ተፈቃሪው›› ሲል የጠራቸው ብቸኛው ሰው ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው፡፡

እንደ ኢማሙ ማሊክ ገለፃ የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) መቃብር ያረፈበት ቦታ ከካዕባ ቀጥሎ የአለማችን የተቀደሰ ስፍራ ነው፡፡ ምክንያቱም ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለአለም ሙሉ እና ለጠቅላላ የሰው ዘር የተላኩ ነብይ ነበሩና፡፡

እነኚህ ስፍራዎች ከአደም (ዐ.ሠ) ጀምሮ በእምነትና መንፈሳዊነት የተጥለቀለቁ ናቸው፡፡ በነብያት ታሪክ ውስጥም ትልቅ ስፍራ አላቸው፡፡

ሐጅ የእምነት ግዴታ ሆኖ አማኞችን ወደ ፍጹም የእምነት ደረጃ የሚመራ ተግባር ነው፡፡

በሐጅ ስነ ስርዓት ልቦች በተቀደሰ የእምነት መንፈስ ይታጠባሉ፡፡ ሰዎች ከፍ ወዳለ ደረጃ ይሸጋገራሉ፡፡

ዘካ አቅሙ ባላቸው አማኞች ላይ የተደነገገ የግዴታ ምፅዋት ነው፡፡ ይህ ስርአት ቀሪውን ገንዘብ ለባለቤቱ የተባረከ ለማድረግ ይረዳል፡፡ እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ ፍትሀዊ የሆነ ክፍፍል እንዲኖር ያደርጋል፡፡ በዚህም ማህበረሰቡ በአንድነት፣ በደስታና በመተሳሰብ ይኖራል፡፡

ዘካ ከአንድ ሰው የአመት ገቢ ሳይሆን ከተጠራቀመ አመት የሞላው ገቢ የሚሠጥ ምፅዋት መሆኑን ማስተዋል ያሻል፡፡ ያለ ስራና እንቅስቃሴ ቁጭ የሚል ገንዘብ ዋጋው እየወረደ እንደሚመጣ የማይታበል ሀቅ ነው፡፡ ለዚህም ኢስላም ከተቀመጠ ገንዘብ ላይ ዘካን በማስከፈል አማኞችን ለኢንቨስትመንት እና ለስራ ያበረታታል፡፡

ገንዘብ የማካበትና የመክበር ፍላጎት በጊዜ ሂደት ወደ ከፍተኛ የውስጥ በሽታነት የመቀየር እድል እንዳለው እሙን ነው፡፡ ለዚህም ኢስላም የገንዘብ ባለቤቶችን ከስግብግብነት ነፃ ለማድረግ እንዲሁም አቅም

ያነሳቸውን ለመርዳትና ለመደገፍ ሲል ዘካን ያዛል፡፡ ዘካ የድሆች ሀቅ ሲሆን በህብረተሰቡ ውስጥ ሠላምና ፍቅርን የማስፋፋት ጉልበት አለው፡፡

﴿ وَفِيٓ أَمۡوَٰلِهِمۡ حَقّٞ لِّلسَّآئِلِ وَٱلۡمَحۡرُومِ ١٩ ﴾ الذاريات: ١٩

‹‹በገንዘቦቻቸውም ውስጥ ለለማኝና (ከልመና) ለተከለከለም (በችሮታቸው) መብት አልለ፡፡›› **(አዝ-ዛሪያት 19)**

አዳብ (ኢስላማዊ ስርዓት) እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ሰጪው ለተቀበዩ ምስጋናን ማሳየት አለበት፡፡ ምክንያቱም አላህን እንዲገዛና ግዴታውን እንዲወጣ ረድቶታልና፡፡ ለአላህ ብሎ የተሰጠ የፍላጎት ምፅዋት ደግሞ በበኩሉ ከህመምና ከተለያዩ ችግሮች መዳኛ ነው፡፡ ቅዱስ ቁርዓን ምፅዋትንና ዘካን ሲያበረታታ ይህን ይላል፡-

﴿ أَلَمۡ يَعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ هُوَ يَقۡبَلُ ٱلتَّوۡبَةَ عَنۡ عِبَادِهِۦ وَيَأۡخُذُ ٱلصَّدَقَٰتِ وَأَنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلتَّوَّابُ ٱلرَّحِيمُ ١٠٤ ﴾ التوبة: ١٠٤

‹‹አላህ እርሱ ከባሮቹ ንስሓን የሚቀበል ምጽዋቶችንም የሚወስድ መኾኑን አላህም እርሱ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ መኾኑን አያውቁም?›› **(አት-ተውባህ 104)** በሀዲስም እንዲህ ተብሏል፡- "ምፅዋት ከችግረኞች እጅ ከመድረሱ በፊት ከአላህ እጅ ይደርሳል፡፡"[60]

በሐዲስም እንዲህ ተብሏል፡- ‹‹ምጽዋት ከችግረኞች ከመድረሱ በፊት ከአላህ እጅ ይደርሳል፡፡

ምፅዋት በምንሠጥበት ጊዜ ክፉ ፊትን፣ መኩራራትን እና ታይታን ማስወገድ አለብን፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ምፅዋታችን ከአላህ እጅ መድረሱ

---

[60] አል ጦበራኒ፡ አልሙዕጀም፡ አልከቢር 1X109፡ አል-ሀራዊ፡አል-አርባ ኢን ፊደኢል፡ አል-ተውሂድ I 74 አል ዳይላሚ አል-ፊርደውስ II52

ይቅርና ከፍጡራን እጅ ላይ ይቀራል። ከዚህም የተነሳ ሠጪው ንብረቱና ግዜው ይህን አለም ሳይሻገር ይቀራል።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ምፅዋት ከመስጠት ልምዳቸው የተነሳ ምንም አይነት የቅንጦት ኑሮ አልነበራቸውም። እናታችን አይሻ (ረ.ዐ) ፦

"ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) መቼም ቢሆኑ ሁለት አይነት ምግቦች በአንድ ቀን ተመግበው አያውቁም" ስጋ የተመገቡ ቀን በዛች ቀን ደግመው ስጋ አይመገቡም፤ ዳቦና ቴምር የተመገቡ ቀንም እንደዛው።"[61]

አቡ ናድር (ረ.ዐ) ባስተላለፉት ደግሞ "እናታችን አይሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፦

"አንድ ቀን ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ጋር ተቀምጠን ነበር። አባቴ አቡ በከር (ረ.ዐ) የበግ እግር አመጡልኝ፤ በምሽት ስጋውን ለመቆራረጥ ስንታገል አንድ ሰው፦ ‹‹ሻማ ወይም ፋኖስ የላችሁም?›› ሲል ጠየቀን። እኔም ‹‹ዘይት ቢኖረን ኖሮ በበላነው ነበር" ስል መለስኩ።[62]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ምፅዋት መስጠት እጅግ ይወዱ ነበር። አንድ ግዜ ለቢላል እንዲህ ብለውታል።

"ቢላል ሆይ! ምፅዋት ስጥ! ምፅዋት በመስጠትህ የልዕልና ባለቤት የሆነው ጌታ ንብረቴን ይቀንስብኛል ብለህ እንዳትፈራ።"[63]

የአላህ መልዕክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) መቼም ቢሆን ንብረት የማከማቸት ሀሳብ ኖሯቸው አያውቅም። ምክንያቱም የአላህ አገልጋይ ነብይ እንደሆኑ ወደ አላህ መመለስ ነበርና የሚፈልጉት። በሀዲሳቸውም ይህንን ብለዋል፦

---

[61] ኢብን ሳድ አል-ጠበቃት አል-ኩብራ 1 405

[62] ኢብን ሳድ አል ጠበቃት አል ኩብራ 1 405

[63] ማማር ኢብን ረሺድ አል-ጃም 11 108፣ አል-ባዕዛር አል-ሙሠነድ IV 204፣ አል ጦበራኒ አል-ሙዕጀሚ አል-አውሳጥ III፣ አል-በይሀቂ፡ ዕቡል ኢማን 86 II118

"አገልጋይ ነብይና ንጉስ ነብይ የመሆን ምርጫ ተሠጥቶኝ ነበር። መላኢካው ራሴን እንዳስተናነስኩ እንድቆይ ፍንጭ ሰጠኝ። እኔም አንድ ቀን መራብን፣ አንድ ቀን መመገብን መረጥኩ"።[64]

ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) የልጃቸው የፋጢማ ቤት ተጊጦ ቢደርሱ አልገባም በማለት ይህን ተናገሩ፡-

"እንደዚህ ካጌጠ ቦታ መግባት ለኛ ተገቢያችን አይደለም"[65]

ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ከዚህ ሁሉ በኂላም እንኳ በሚመሩት የመጠቀ ሕይወት ባለመኩራራት ዘወትር አላህ በርሳቸው ላይ የዋለውን ፀጋ ይቆጥሩ ነበር። ዘወትርም "ላ ፈኽር" (ምንም ኩራት አያስፈልግም) በማለት ይናገሩ ነበር።

## የእዝነቱ ነብይ መተናነስ

ከልክ ያለፈ መደነቅ ሠዎችን ወደ ጉራና መመፃደቅ ይመራል። መልካም ሰዎችንም ያበላሻል። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ግን በአላህ (ሡ.ወ) ተወድሰው እንኳን አልተኩራሩም። ይልቁንም ለተከታዮቻቸው እንዲህ አሉ፡- "የአላህ ባሪያና መልእክተኛ ብላችሁ ጥሩኝ"[66]

አቡ ኡሳማ (ረ.ዐ) ይህን አስተላልፈዋል፡-

"የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ንግግሮች ከቁርዓን የወጡ ሲሆኑ፤ በተከታታይ ዚክር ያደርጉ ነበር። ንግግራቸውን ሲያሳጥሩ ሰላታቸውን ያስረዝሙ

---

[64] ኢብን ሂባል አል-ሠሂህ XVI,280 አል በይሀቂ አል-ሱና አል ኩብራ VII45-49

[65] አቡ ዳውድ፣ ኢብን ማጃህና አህመድ ኢብን ሀንባል

[66] ቡኻሪ አንቢያ 58፣ ዳሪሚ ሪቃቅ 68፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠናድI 23

ነበር። ከችግረኛ ሰዎች ጋር መሆን መቼም አሳፍሯቸው የማያውቅ ከመሆኑም በላይ በዚህ ድርጊት ይደሰቱበት ነበር።"[67]

አነስ (ረ.ዐ) ባስተላለፉት ሀዲስ ደግሞ፡-

"ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እጅግ በጣም በተደጋጋሚ ዚክር ያደርጉ የነበረ ሲሆን የሚቀልዱት እጅግ አልፎ አልፎ ነበር። የባሪያዎችን ግብዣ የሚቀበሉ፣ የታመመን የሚጠይቁና የሞተን የሚቀብሩ ሰው ነበሩ። የኸይበር ጦርነት ወቅት አህያ ላይ ከተምር ቅጠል በተሠራ ኮርቻ ተቀምጠው ነበር። አላህ ድልን በሠጣቸው ቁጥር ይበልጥ እያመሠገኑት እና እየተናነሡ ይሄዱ ነበር።"[68]

ጀሪር (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፡-

"አንድ ሠው መካ በተቃናች ወቅት ወደ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) መጣ። የነብያችንን አካላዊና መንፈሳዊ ግርማ ሞገስ ሲመለከት መንቀጥቀጥ ጀመረ፤ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይህን ሲመለከቱ በለሰለሰ ድምፅ እንዲህ አሉት፡-

"አትፍራ። እኔ ባዕድ (ባዳ) አይደለሁ። እኔ የቁረይሽ ወገን የሆነች በፀሀይ የደረቀ ስጋ ትመገብ የነበረች ሴት ልጅ ነኝ።"[69]

አሚር ኢብን ራቢያ እንደዘገቡት፡-

---

67 ነሳኢ ጽም 31፣ ዳሪሚ ሙቀዲማህ 13፣ ኢብን ሂባን አል-ሠሂህ XII 333፣ አል-ሀኪም አል ሙስተድረክ II 67

68 ቲርሚዝ ጃናይዝ 32፣ ኢብን ማጃህ ዙህድ 16፣ አል-ሀኪም አል-ሙስተድራክ II 506

69 ኢብን ማጃህ አቲማህ 30 አል-ሀኪም አል-ሙስተድራክ II 506 አል-ጦበራኒ አል-ሙእጃሙ አውሳጥ II644

"አንድ ቀን ከነብያችን(ሠ.ዐ.ወ) ጋር ወደ መስጂድ እየተጓዝኩ ነበር። የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ጫማ ተገነጠለና ወስጄ እንድሰራው እንዲፈቅዱልኝ ጠየቅኳቸው፤ ሳይፈቅዱልኝ ቀሩና እንዲህ አሉኝ፦

"ይህ ራስን ከሌሎች አብልጦ መመልከት ነው። እኔ ደግሞ ራሴን ማኩራራት እጅግ እጠላለሁ።"[70]

የአላህ መልዕክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) ይህ የመጪው አለም ደስታን ለሚሹ ሁሉ መመሪያን ሰጥተዋል። ይህም ታላቁ መሪ -ነብያችን ሙሀመድ (ሠ.ዐ.ወ)- በምላሹ ምንም ሳይጠይቁን የሰጡን ምርጥ ስጦታ ነው።

የሐይማኖት አላማው ጥሩነትን ማስፋፋት እና የሰው ልጅን ስብዕና ከፍ ማድረግ ነው። ይህ ደረጃ የሚገኘው ልብን ለአላህ (ሱ.ወ) እና ለረሡል (ሠ.ዐ.ወ) በመስጠት ነው። በቅዱስ ቁርዓን እንዲህ ሲል ተገልፀዋል፦

﴿ إِنَّمَا ٱلْمُؤْمِنُونَ ٱلَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ ٱللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ ءَايَٰتُهُۥ زَادَتْهُمْ إِيمَٰنًا وَعَلَىٰ رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ ﴿٢﴾ ﴾ الأنفال: ٢

"ፍጹም ምዕመናን እነዛ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት በነሡም ላይ አንቀፃችንን በተነበቡ ጊዜ እምነትን የሚጨምሩላቸው በጌታቸው ላይ ብቻ የሚመኩ ናቸው።" **(አል አንፋል 2)**

ሠው ለሚለው ቃል የአረብኛ አቻ ፍቺው "ኢንሳን" የሚለው ነው "ይህ ቃል" ኒስያን (መርሳት) እንዲሁም "ኡንስ" (ጓደኝነት) ከሚሉት ቃላት ጋር ግንኙነት አለው። የ"ኒስያን" (መርሳት) ተቃራኒው ግን በቁርአን 250 ጊዜ የተጠቀሰው (ዚክር) (ማስታወስ) ነው። የዚክር መቀመጫ

---

[70] አል በዛር፣ አል-ሙሰነናድ፣ IX 263 አቡዳውድ ፣ አል-ተያሊስ፣ አል-ሙሰናድ 1፡156 አል ጦበራኒ፣ አል-ሙእጃም አል-አውሳጥ III 174፣ አል-በይሀቂ ፣ ሹዐብ፣ አል-ኢማምን III 275

በታው ደግሞ ልብ ነው፡፡ እውነተኛ አማኞች አላህን ማውሳትንና ማስታወስን (ዚክር ማድረግን) መቼም አይረሱም፡፡

﴿ ٱلَّذِينَ يَذْكُرُونَ ٱللَّهَ قِيَٰمًا وَقُعُودًا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمْ وَيَتَفَكَّرُونَ فِى خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ رَبَّنَا مَا خَلَقْتَ هَٰذَا بَٰطِلًا سُبْحَٰنَكَ فَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ١٩١ ﴾ آل عمران: ١٩١

«(እነርሱም) እነዚያ ቆመው. ተቀም□□ም. በጎኖቻቸው ተጋድመውም አላህን □ሚ□□ሱ. በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያስተነትኑ፡- «□ታችን ሆይ! ይኽን በከንቱ አልፈጠርከውም፤ ጥራት ይገባህ፤ ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን» የሚሉ ናቸው፡፡» **(ኣሊ ዒምራን 191)**

የሠው ልጆች ከፍተኛውን የሠውነት ደረጃ ከፈለጉ አላህን ከማስታወስ ሊዘናጉ አይገባም፡፡

﴿ أَفَمَن شَرَحَ ٱللَّهُ صَدْرَهُۥ لِلْإِسْلَٰمِ فَهُوَ عَلَىٰ نُورٍ مِّن رَّبِّهِۦ ۚ فَوَيْلٌ لِّلْقَٰسِيَةِ قُلُوبُهُم مِّن ذِكْرِ ٱللَّهِ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ فِى ضَلَٰلٍ مُّبِينٍ ٢٢ ﴾ الزمر: ٢٢

«አላህ ደረቱን ለእስልምና ያሰፋለትና እርሱም ከጌታው ዘንድ በብርሃን ላይ የኾነ ሰው፥ (ልቡ እንደ ደረቀ ሰው ነውን?) ልቦቻቸውም ከአላህ መወሳት ለደረቁ ሰዎች ወዮላቸው፤ እነዚያ በግልጽ መሳሳት ውስጥ ናቸው፡፡» **(አዝ-ዙመር 39:22)**

ይህ የቁርዓን አንቀፅ ልቦቻቸው አላህን በመዘከር የተጠመዱት እና አላህን ከማስታወስ የተዘናጉ ፈፅሞ እኩል እንዳልሆኑና አላህን የማያወሱ ሠዎች ከደረጃ ዝቅ ማለታቸውን ያሳየናል፡፡

የሠው ልጅ በባህሪው የሚገዛው ነገር ይፈልጋል፡፡ አንድም ቁስ አምላኪ ይሆናል ወይ ለጌታው ይማረካል፡፡ የሠው ልጅ በቁስ ከተጠመደ የግል ፍላጎትና የቁስ ባሪያ ይሆናል፡፡ አምላካችን አላህ ከዚህ ነገር እንዲህ ሲል ያስጠነቅቀናል፡-

﴿ أَفَرَءَيْتَ مَنِ ٱتَّخَذَ إِلَٰهَهُۥ هَوَىٰهُ وَأَضَلَّهُ ٱللَّهُ عَلَىٰ عِلْمٍ وَخَتَمَ عَلَىٰ سَمْعِهِۦ وَقَلْبِهِۦ وَجَعَلَ عَلَىٰ بَصَرِهِۦ غِشَٰوَةً فَمَن يَهْدِيهِ مِنۢ بَعْدِ ٱللَّهِ ۚ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ٢٣ ﴾ الجاثية: ٢٣

«ዝንባሌውን አምላኩ አድርጎ የያዘውን. አላህም ከዕውቀት ጋር ያጠመመውን. በጆሮውና በልቡ ላይም ያተመበትን. በዓይኑም ላይ ሺፋን ያደረገበትን ሰው አየህን! ታዲያ ከአላህ በኋላ የሚያቀናው ማነው? አትገሠጹምን?»(**አል-ጃሢያህ 45፡23)**

የዚህች አለም ምኞት መራዘም ሞት እንዳለብንና ለምን እንደተፈጠርን ሊያስረሳን እና ለአስከፊ መጨረሻ ሊዳርገን ይችላል።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይህን ሲያስጠነቅቁ

"ተጠንቀቁ። ‹ህልማችሁና የወደፊት እቅዳችሁ ሞትን እስኪያስረሷችሁ ድረስ እንዳይገዝፉ። ካልሆነ ልቦቻችሁ ይደርቃሉ። አይኖቻችሁን ግለፁ፤ መጪው ዓለም እጅግ ቅርብ ነው።"[71]

ከነብያችን ምክሮች እጅግ የተጠቀመው ሠልማን አል ፋሪስ (ረ.ዐ) እንዲህ ብሏል። "3 ነገሮች ያስቁኛል።" በማለት ካብራራቸውና ከሚያስቁት ነገሮች አንዱ፡- “ሞት እያለበት እቅዱና ህልሙን የሚያንዛዛ ሰው መመልከት” ነበር። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- "እጅግ የጃጀ ሽማግሌ እንኳ ለዚህች ምድር ያለው ምኞት እጅግ ወጣት ነው።"[72]

ከዚህ ሀዲስ የዚህች ምድር ጉጉትና ምኞት ከሠዎች ልብ ለመውጣት ምን ያህል አስቸጋሪ መሆናቸውን እንረዳለን። የሰው ልጅ ሰውነቱ እየደከመና አቅም እያጠረው እንኳን ምኞቱን ለማሳጠር ይቸገራል።

የደረቀ መሬት እያንደንዷን የዝናብ ጠብታ የሚመጠውን ያህል የሠው ልጅም በራስ ወዳድነት ስሜት የአለምን እያንዳንዱን ደስታ ማግበስበስ ይሻል። ልዩነቱ የዝናቡን ውለታ መሬት እህል በማብቀል ስትመለስ

---

[71] ኢብን ማጃህ ሙቀዲማህ 7፣ማማር ኢብን ረሺድ አል-ጃሚ XI፡116፣ አል-ቃዲ ሙሠናድ-አል ሺሀብ II263 አል-ጦበራኒ አል-ሙዕጃም አል-አውሳጥ

[72] ቡኻሪና ሙስሊም

የሠው ልጆች ግን ውለታውን ምፅዋት በመስጠት ለመመለስ ይቸገራሉ፡፡ የዚህች ምድር ሀብት ተገዢዎች ሆነውም ይቀራሉ፡፡

መጥፎ ነገሮች በዚህች ምድር ላይ የመኖራቸው አላማ የሠው ልጆችን መፈተን ነው፡፡ አላህ በቁርዓኑ፡-

﴿ وَنَفۡسٖ وَمَا سَوَّىٰهَا ﴿٧﴾ فَأَلۡهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقۡوَىٰهَا ﴿٨﴾ قَدۡ أَفۡلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ﴿٩﴾ وَقَدۡ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ﴿١٠﴾ ﴾ الشمس: ٧ - ١٠

«በነፍስም ባስተካከላትም፤አመጽዋንና ፍርሃትዋንም ባሳወቃት. (አምላክ እምላለሁ)፤ (ከኀጢኣት) ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ፡፡ (በኀጢኣት) የሸፈናትም ሰው. በውነት አፈረ፡፡»**(አሽ-ሽምስ፡ 7-10)**

የሠው ልጆች ትልቅነትና ስኬት የሚለካው ለአላህ በመታዘዛቸው መጠን ነው፡፡

የተቡክ ዘመቻ እጅግ አድካሚ ነበር፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ወደ ቤታቸው ለመመለስ መቶ ኪሎ ሜትሮችን ተጉዘዋል፡፡ ወደ መዲና በሚጠጉበት ወቅት ከድካም የተነሳ መልካቸው ተቀያይሮ፣ ከረሀብ የተነሳ ቆዳቸው አጥንቶቻቸው ላይ ተጣብቆ፤ ፀጉራቸውና ፂማቸው ተዘበራርቀው ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናገሩ፡-

"አሁን ከትንሹ ጦርነት ወደ ከባዱ ተሸጋግረናል...!" ባልደረቦቻቸውም በመገረም "ካደረግነው ዘመቻ የከበደ ጦርነት ይኖረናል እንዴ?" ሲሉ ጠየቁ፡፡ ነብያችንም "አሁን ወደ ከባዱ ጦርነት ተሸጋግረናል፡፡ እርሱም ከራስ (ከነፍስ) ጋር የሚደረግ ጦርነት ነ፡፡ው" በማለት መለሱላቸው፡፡"[73]

---

[73] አል-ባግዳድ ታርብ ባግዳድ XIII 523 (የዚህ ሀዲስ የተወሠነ ክፍሉ በኢብራሂም ኢብን አቢ አብላ ተዘግቦ ነበር) አል-ሚዚ ተህዚብ፤ አል-ካሚል II 144፤ አል ዘሀቢ ሲያር አዕላም አል ኑበላም VI 325)፡፡

ከራስ ጋር የሚደረግ ጦርነት ልብን "አላህን በመገዛት ትምህርት" በማሠልጠን ይካሄዳል፡፡ አላማውም የሠውን ልጅ ከፍ ማድረግና ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ነው፡፡

ይህን ደረጃ ማግኘት የሚቻለው የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) መልእክት በመረዳት ነው፡፡ የሠው ልጅ የተፈጠረበትን አላማ መረዳት ካልቻለ ይህች አለም ውጣ ታስቀረዋለች፡፡

የሠው ልጅ አፈጣጠሩንና አላማውን ካላወቀ ፈፅሞ በምድር ላይ የአላህ ተወካይ መሆን አይችልም፡፡ የአላህ አምባሳደር ለመሆን ሚሞክሩትና የሡን መንገድ የሚከተሉት የአላህ መመልከቻ አይኑ፣ መስሚያ ጆሮው ይሆናሉ፡፡ የህይወታቸው ትልቁ ዓላማም ከአላህ ጋር መገናኘት ነው፡፡[74]

እዚህች ምድር ላይ አንዳንድ ነገሮች በሰው ልጅ እውቀት መግለፅ አይችሉም፡፡ ሌላው ቀርቶ ቃላቶች እንኳን በሌላ ቃላት መገለፅና መተንተንን ይሻሉ፡፡

የዚህች ምድር ፍፁም የሆነው ገላጯ አላህ ነው፡፡ እኛ ይህችን ምድር የምናውቃት እሱ እስካሳወቀን ደረጃ ድረስ ብቻ ነው፡፡

አንዳንድ የአለማችን ሚስጥሮችን ለመረዳት ለአላህ መታዘዝና መገዛት ያሻናል፡፡ ከአባታችን ኢብራሂም (ዐ.ሠ) ህይወት ይህን እንረዳለን፡፡

﴿ إِذۡ قَالَ لَهُۥ رَبُّهُۥٓ أَسۡلِمۡۖ قَالَ أَسۡلَمۡتُ لِرَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿١٣١﴾ ﴾ البقرة: ١٣١

«ጌታው ለርሱ ታዘዝ ባለው ጊዜ (መረጠው)፤ ለዓለማት ጌታ ታዘዝኩ አለ፡፡» **(አል-በቀራ :131)**

ኢማም አል ገዛሊ የህይወት ልምዳቸውን እንዲህ ሲሉ ይናገራሉ፡-

---

[74] ቡኻሪ ሪቃቅ 38፣ አህመድ ኢብን ሀንባሊ አል-ሙሥናድ VI 256፣ ኢብን ሂባን አል ሠሂህ II 58 አል-በይሀቂ አል ሡነን አል ኩብራ III 346

"እውቀቴን የመጨረሻ ጥልቅ ደረጃ ለማድረስ በማደርገው ትግል እጅግ ተጨንቄ ነበር፤ በዚህ መሀል ገደብ እንዳለው ሳስብ በደረሰብኝ መደናገጥ ግራ ተጋባሁ። ሆኖም ወደ ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ሕይወት ስመለስ የሁሉንም ነገር ሚስጥር አገኘሁት።"[75]

ነብዩ ኢብራሂም (ዐ.ሠ) እንዲህ ይላሉ።

﴿إِنِّي ذَاهِبٌ إِلَىٰ رَبِّي سَيَهْدِينِ ﴿٩٩﴾﴾ الصافات: ٩٩

«እኔ ወደ ጌታዬ ኼያጅ ነኝ፤ በእርግጥ ይመራኛልና።» **(አስ-ሷፍፋት፡ 99)**

መውላና ጀላሉዲን ሩሚ ይህን የቁርኣን አንቀፅ ሲያብራሩ፡- "ምክንያታዊነት አንድ የታመመ ሠውን ወደ ዶክተር እንዲሄድ ያደርገዋል። ከዛ ግን ለዶክተሩ ራሡን መስጠት ይጠበቅበታል።[76]

የሠው ልጅም ምክንያታዊነቱ ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ዘንድ ካደረሠው በኋላ ለመልእክተኛው (ሠ.ዐ.ወ) እና ለመልዕክቱ ራሱን መስጠት አለበት።

## ፍቅር፣ እንክብካቤና ስነ ምግባር በእዝነቱ ነብይ (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት ውስጥ

ነብያችን በስነ ምግባርና ግብረገብነት ፈፅሞ የሚደርስባቸው እንደሌለ ለመቁጠር የሚያዳግቱ ሶሀቦች ተናግረዋል። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ምን ግዜም ፊታቸው በፈገግታና በብርሀን የተሞላ ነበር። እጅግ ንጹህ ልብ ነበራቸው ምንም ነገር ምድርን እንዲያቆሽሽ አይፈቅዱም። አንድ ቀን ከሶሀቦቻቸው ጋር በመንዝ ላይ እያሉ አንድ ሰው መንገድ ላይ ፊት

---

[75] ገዛሊ አቡ ሃሚድ፣ አል-ሙንቂዝ ሚነ ደላል (በይሩት 1988) ገፅ 60

[76] ሩሚ፣ ጀላሉዲን መስነዊ ማናዊረን (ቴህራን 1378) ll 3323

ለፊት ሲተፋ ተመለከቱና በቁጣ ፊታቸው ተለዋወጠ። ባልደረቦቻቸው በፍጥነት ሄደው በጫማዎቻቸው በመርገጥ እንዲሸፈን አደረጉት።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ያደፉ (የቆሸሹ) ልብሶችን እጅግ ይጠሉ፤ ያልተበጠረ ፀጉርና የተዘበራረቀ ጺምንም ይነቅፉ ነበር።

ለምሳሌ በአንድ ወቅት አንድ ሰው ፀጉሩና ፂሙ ተዘበራረቆና ሳይበጠር ወደ እሳቸው መስጂድ መጣ፤ ነብያችንም ወደ እሡ በመጠቆም ስለ ፀጉሩና ስለ ፂሙ ጥንቃቄ እንዲያደርግ መከሩት። ሠውዬውም በሌላ ጊዜ ፀጉሩንና ፂሙን አስተካክሎ ተመለከቱት። እንዲህም አሉ "በተዘበራረቀ ፀጉርና ፂም ሰይጣን ከመምሰል እንዲህ ማማር አይሻልምን?"[77]

በሌላ ጊዜ ደግሞ ነብያችን ፀጉሩ የተንጨባረረ አንድ ሰው ተመልክተው ይህን ተናገሩ፡- "ለምንድነው ይሄ ሰው ፀጉሩን የማያበጥረውና የማይታጠበው?"

ኡመር ኢብን ኸጧብ እንዳስተላለፉት አንድ ስነ ምግባር የጎደለው የገጠር ሰው መጥቶ ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ስነ-ምግባር በጎደለው አጠራር መጣራት ጀመረ። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በትእግስት በማለፍ "እባክህን ወደ ውስጥ ግባ" ሲሉ ጋበዙት። ይህም ሆኖ ግን ባልተስተካከለና መላ ቅጡን ባጣው አለባበሱ ተረብሸው ነበር።[78]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ከነፍሳቸው ጥራትና ለነገሮች ከነበራቸው ተቆርቋሪነት የተነሳ አማኞች ያልተገባና ንፅህና የጎደለው አለባበስና ገፅታ እንዲኖራቸው አይሹም።

---

77 ሙዋታ ሻር 7፣ አል-በይሀቂ ሹአብ አል ኢማም ||225

78 ቲርሚዚ ዙህድ 50፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠነድ | 206.

በሌላ ዘገባ አለባበሱ ያልተገባ አንድ ሰው ወደ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) መጣ፤ "ገንዘብ አለህን? የኢኮኖሚ አቅምህ እንዴት ነው?" ብለው ጠየቁት፡፡ እርሱም ጥሩ ገቢ እንዳለው መለሰ፡፡ ነብያችንም (ሠ.ዐ.ወ) "አላህ የሠጠህ ፀጋ ባንተ ላይ እንዲታይ አድርግ" በማለት መከሩት፡፡[79]

በሌላ ሀዲስ "አላህ ለባሮቹ የሰጠውን ፀጋ ምልክት በባሪያዎቹ ላይ ሲመለከት ይደሰታል" አሉ፡፡[80]

ከነዚህ ሀዲሶች የምንማረው በኢስላም የልብና የውጪያዊ ገፅታ ውበት ትልቅ ስፍራ እንዳለው ነው፡፡

ከመኩራራትና ከመመፃደቅ ለመዳን ማንኛውም ሙስሊም አዲስ ልብስ በሚለብስበት ወቅት ይህ ከአላህ ችሮታ መሆኑን የመረዳት ግዴታ አለበት፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አዲስ ልብስ በሚለብሱበት ወቅት የሚያደርጉትን ዱዐ (ፀሎትም) ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

"አላህ ሆይ! ምስጋና ለአንተ የተገባ ነው፤ አንተ ነህ ያለበስከኝ፤ የዚህን ልብስ (በጎ) ገፅታና የተሠራበትን በጎ አላማ እንድትለግሰኝ እጠይቅሀለሁ፡፡ ከዚህ (ልብስ) መጥፎ ገፅታና ከተሰራበት መጥፎ አላማም ባንተ እጠበቃለሁ፡፡"[81] በዚህ ፀሎት ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እያንዳንዱን ነገር የአላህ ለማድረግ እንደሚሹ እንረዳለን፡፡ እንዲሁም ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አንድ ሰው የሚለብስበትና የሚዋብበት ምክንያት ለመመፃደቅ፣ ለመታየትና ሌሎችን ለማሳነስ ከሆነ በፍርዱ ቀን የውርደት ልብስን እንደሚለብስ አስተምረውናል፡፡

---

[79] ነሳኢ ዚህ 54፡ቲርሚዝ ቢር 63፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠናድ IV 137 ኢብን ሂባን አል-ሠሂህ XII 234

[80] ቲርሚዝ አደብ 54፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠነድ II 311፣ አል-ሀኪም አል-ሙስተድራክ II 150

[81] "አቡ ዳውድ ሊባስ 1 ቲርሚዝ ደአማት 55፣ ኢብን ማጃህ አቲማህ 16"

አብደላህ ኢብን አምር እንዳስተላለፉት ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በእለት ተእለት ህይወታችን የምንጠቀማቸውን መጥፎ ቃላት ፈፅሞ ተናግረው አያውቁም፡፡ እንዲህም ይናገሩ ነበር፡-

"በዚህች ምድር ላይ የምትፈፀም ቅንጣት የሆነች መጥፎ ነገር ነገ በፍርዱ ቀን እጅግ ትቆጫለች፡፡"[82]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ምን ግዜም ለህቅና ለተበዳይ የሚቆሙ ናቸው፡፡ በአንድ ወቅት አቡዘር አል-ጊፋሪ ቢላልን "አንተ የጥቁር ልጅ" ብሎ ጠራው፡፡ ነብያችን ይሄን በሠሙበት ወቅት አቡዘርን፡- "አቡዘር አንተ የመሀይምነት ዘመን ተፅዕኖ አልቀቀህም" በማለት ገሠፁት፡፡[83]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እንግዶቻቸውን ፍጹም ከኩራት ነፃ በሆነ መልኩ ራሳቸው ተነስተው ያስተናግዱ ነበር፡፡ ከልጅነታቸው ጀምሮም ከኩራት ነፃ የሆኑና ጊዜያቸውንም አቅም ከሌላቸው፣ ደጋፊ ካጡና ከተገፉ የማህበረሰቡ ክፍሎች ጋር ያሳልፉ ነበር፡፡[84]

አነስ (ረ.ዐ) እንዲህ በማለት ተናግረዋል፡- "ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ለ10 አመታት ያህል አገልግያለሁ፡፡ አንዲትም ቀን ቢሆን ስህተት ስሰራ ለምን ይሄን አደረግክ? በሚል አስደንግጠውኝ አያውቁም፡፡››[85]

---

82 ቲርሚዝ ቢር 61፣ አል-በይሀቂ፣ አል ሱነን አል-ኩብራ 193፣ ማማር ኢብን ረሺድ-አል ጃሚእ XI 146፣ አል ቁዳ ሙስነድ አል-ሺሀብ I 274

83 ቡኻሪ ኢማን 22 ሙስሊም አይማን 38 አቡ ዳውድ አደብ 124 ቲርሚዝ ተፍሲር ሡራ 22፡1 አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠናድ V 161

84 ቡኻሪ ነፈቃት 1፣ ሙስሊም ዙህድ 41-42

85 ሙስሊም ፈዳኢል 51፡ አቡ ዳውድ አደብ 1፡ ዳረሚ ሙቀዲማ 10

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሌላው ቀርቶ በጦርነት ወቅት እንኳን የተማረኩና ከጠላት ወገን የሆኑ ሴቶችንና ህፃናትን በመልካም መያዝን ያዙ ነበር፡፡

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እዝነት ሁሉንም ፍጥረት ያካተተ ነበር፡፡ ህፃናትን በሚመለከቱበት ወቅት በፈገግታና በስስት እየተመለከቱ በእጆቻቸው አንስተው በማቀፍ ያጫውቷቸው ነበር፡፡ ልጆችን ሠላም ከማለት፣ ለነርሱ ፍቅርን ከማሳየት እና ከመቀለድ ተቆጥበው አያውቁም፡፡

በአንድ ወቅት ህፃናት ተሰብስበው የሩጫ ውድድር ሲጫወቱ ተመለከቱ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ህፃናቱን ተቀላቅለው አብረዋቸው እንዲጋልቡ ያደርጉና ትኩረት ይሰጧቸው ጀመር፡፡ አነስም (ረ.ዐ) “እንደ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የቤተሰቡንና የህፃናትን መብት የሚያከብርና ልዩ ስፍራ የሚሠጥ አይቼ አላውቅም” ይላል፡፡[86]

አይሻ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ከልጅ ልጆቻቸው ጋር እየተጫወቱ አንድ የበደዊን ሰው መጣ፡፡ በሁኔታው በመገረምም "የአላህ መልዕክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) ሆይ! ልጆችን ይስማሉ እንዴ? እኛ ልጆችን መሳምንም ሆነ ከነርሱ ጋር መጫወትን አስበነው አናውቅም" አላቸው፡፡

ነብያችንም (ሠ.ዐ.ወ) "አላህ ከልቦቻችሁ ላይ ፍቅርና እዝነትን ከወሰደባችሁ እኔ ምን ማድረግ ይቻለኛል?" በማለት መለሱለት፡፡[87]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የዘይድ ልጅ የሆነውን ኡሳማን እና የልጅ ልጃቸውን ሀሠንን ከጉልበታቸው ላይ በማስቀመጥ ካቀፏቸው በኋላ እንዲህ አሉ፡፡

---

[86] ሙስሊም፡- ፈዳኢል 63፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል ሙሠነድ III,112: ኢብን ሂባን አል-ሠሂህ XV,400፡ አል በይሀቂ አል-ሡነን አልኩብራ II,263

[87] ቡኻሪ አዳብ 18፣ ሙስሊም ፈዳኢል 64፣ ኢብን ማጃህ አደብ 3፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠነድ VI 56,70

"አላህ ሆይ፣ ለነዚህ ህፃናት ደስታንና ፀጋህን ስጣቸው። በነሱ ተደስቻለሁና።[88]

ሕጻናትን መርገምንም ከልክለዋል። ነቢዩ ለሕጻናት ያሳዩአቸው ከነበሩ ፍቅሮችና ርህራሄዎች መካከል እነዚህ ጥቂቶቹ ናቸው። አንድ ልጅ እናቱ እየሰገደች ካለቀሰ፣ እናቱ ሶላቱን በማሳጠር ልጇን እንድታባብል ይፈቅዱላታል። ጥቂቶቹ ናቸው። አንድ ልጅ እናቱ እየሰገደች ካለቀሰ እናቱ ሶላቱን በማሳጠር ልጇን እንድታባብል ይፈቅዱላታል።[89] ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለህፃናት ብቻ አልነበረም ደግነታቸው ለመላው ማህበረሰብ እንጂ። ሙሉ የሌሊቱን ክፍለ ጊዜ በማልቀስና ለተከታዮቻቸው ዱዐ በማድረግ ያሳልፉ ነበር።[90] መላ ህይወታቸውንም የሠው ልጆችን ከእሳት ለማዳን ሠውተዋል።[91]

## ከሠዎች ጋር የነበራቸው ግንኙነት

የአላህ መልዕክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) ልንከተላቸው የሚገባ ምርጥ ምሳሌ ናቸው። የሚናገሩትን በተግባር የሚያሳዩ፣ በየትኛውም ህይወት መንገድ ላለ ሰው ምሳሌ የሆኑ ነብይም ናቸው። የየትኛውንም የህብረተሰብ ክፍል በእዝነትና በፍቅር ነበር የሚቀርቡት። ሙስሊም ለሆኑት ብቻ ሳይሆን ከእስልምና ውጭ ለሆኑ ሰዎችም ጭምር መልካም ባህሪና ምርጥ አቀራረብ ነበራቸው።

---

88 ቡኻራ አዳብ 18፣ ሙስሊም ፈዳኢል 64

89 ቡኻሪና ሙስሊም

90 ሙስሊም ኢማን 346፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠናድ 127፣ ኢብን ሂባን አል-ሠሂህ XVI 217.

91 104 ቡኻሪ ሪቃቅ 26፣ ሙስሊም ፈዳኢል 17

ጃቢር ኢብን አብዱላህ እንደዘገቡት "ሠዎች ሬሳ ተሸክመው እያለፉ ነበር። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ቆመው አሳለፉት፤ እኛም ያንኑ አደረግን። ካለፉ በኋላም፡-

የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ‹‹የአይሁድ ሬሳ እኮ ነው?›› ብለን ጠየቅናቸ። ቢሆንስ? ሰው አይደለምን? ሲሉ መለሱልን።[92]

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የህይወት መመሪያ "ፍጡራንን ለፈጣሪያቸው ስትል ውደድ" የሚል ነበር።

በአንድ ወቅት የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ሙስሊም ካልሆኑ ሠዎች በደረሰባቸው ጫና የተነሳ የኢስላም ጠላቶችን እንዲረግሙ ነብዩን (ሠ.ዐ.ወ) ጠየቁ። ነብያችንም (ሠ.ዐ.ወ)፡- እኔ ለእርግማን አልመጣሁም። ለእዝነት እንጂ" ሲሉ መለሱ።[93]

የሚከተለውንም ዱዓ ለእስልምና ጠላቶች አደረጉ፡- ‹‹ጌታዬ ሆይ፣ እነርሱ አያውቁምና አቅናቸው።››[94]

አብደላህ ኢብን ኡበይ የሙናፊቆች ድብቅ መሪ ነበር። በመዲና ከሙስሊሞች ጋር ቆይቶ እጅግ ወሳኝ በሆነ ሰዓት ሙስሊሙን ጦር ከድቶ ከሀዲዎችን ተቀላቀለ። በዚህ ብቻ ሳያበቃ በተደጋጋሚ ሙስሊሙን ማህበረሰብ ከድቷል። ከእሱ በተቃራኒ ልጁ እጅግ መልካም አማኝ ነበር። አብደላህ ኢብን ኡበይ በሞተ ግዜ ልጁ ወደ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በመምጣት የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ቀሚስ ጠየ። በቀሚሱ

---

[92] 105 ቡኻሪ ጃናኢዝ 50፣ ሙስሊም ጀናኢዝ 81

[93] ሙስሊም ጅሀድ 104፣ አቡ-ያዕአል-ሙሠነድ XI-35፣ አል በይሀቅ አል ሡነን አል-ኩብራ III 362 - አል ሙዕጃም አል አውሳጥ III 223

[94] ቡኻሪ አንቢያ 54፣ ሙስሊም ጀሃድ 104፣ ኢብን ማጃህ ፊተን 33። ኢብን ሂባን አል ሠሂ III 254

የአባቱን እሬሳ ለመገነዝ፡፡ ነብያችንም (ሠ.ዐ.ወ) ወዳጃቸውንና ተከታያቸውን ላለማስከፋት ደጋግሞ የካዳቸውና የባለቤታቸውን የአይሻን ስም በማጥፋት ዘመቻ ላይ የተሠማራው ሠው ሬሳ እንዲሸፍንበት ልብሳቸውን አውጥተው ሰጡ፡፡[95]

ከዚህ የተሻለ የሠብአዊነት ምሳሌ ከቶ ከየት ይገኛል፡፡ በአንድ ወቅት አንድ በደዊን በፀሎቱ ላይ "እኔንና ሙሐመድን ብቻ ማር ሌሎቹን ግን ..." ሲል የእዝነቱ ነብይ አዳመጡት፡፡ "ሠፊ የሆነውን የአላህን እዝነት እያጠበብከው ነው" አሉት፡፡[96]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በአካባቢያቸው ብቻ የተወሠኑ ሰው አልነበሩም፡፡ ይልቅስ አለምንና የሁሉንም ዘመን ሠዎች በደስታ፣ በእዝነትና በፍቅር ለማስተሳሰር የተላኩ፣ ዘረኝነትንና ክፋትን በማጥፋት የሠውን ልጅ ከሠብአዊነት ጣሪያ ላይ ያደረሱ ነበሩ፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ከአስተማሪዎች ሁሉ ምርጥ አስተማሪ የነበሩ ሲሆን ልጆቻቸውን ከነህይወታቸው ይቀብሩ ለነበሩና ለባሪያዎቻቸው ቅንጣት እዝነት ላልነበራቸው ሠዎች እዝነትን በማሳወቅና በተግባርም በማሳየት ምድርን እንዲቀይሩ አስችለዋቸዋል፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ማንንም አግልለውም ሆነ ለይተው አያውቁም፡፡ ሁሉንም እንደ ሁኔታው ያስተናግዳሉ፡፡

ለምሳሌ አንድ ቀን አንድ በደዊን ወደ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እርዳታ ጥየቃ መጣ፡፡ ነብያችንም (ሠ.ዐ.ወ) በእጃቸው ያለውን ነገር ሁሉ ከሠጡት

---

[95] ቡኻሪ ጀናኢዝ 23 ሙስሊም ሙናፊቁን 14፣ አቡ ዳውድ ጃናኢዝ 1፣ ኑሳኢ ጃናኢዝ 40 አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠነድ II 18

[96] ቡኻሪ አደብ 27፣ ኢብን ማጃህ ጠሀራህ 78፣ አህመድ ኢብን ሀንበል አል-ሙሠነድ II 239

በኋላ ‹‹ይሄ በቂህ ነው?" ሲሉ ጠየቁት፡፡ መልካም ባህሪ ያልነበረው በደዊን "የሚበቃኝን ያህል አልሰጠኸኝም" ሲል መለሰላቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛ ባልደረቦችም በበደዊኑ አለመብቃቃትና ግብረገብ አለመሆን ተበሳጩ፡፡ እርምጃም መውሰድ ፈለጉ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ግን አስቆሟቸውና ተጨማሪ ነገር ሠጡት፡፡ በመቀጠልም "አሁንስ ይበቃሀልን?" ሲሉ ጠየቁት፡፡

"አዎን፡፡ አላህ በእኔ፣ በቤተሰቦቼና በዘመዶቼ ልክ በረከት ይስጥዎት›› ሲል ተናገረ፡፡ ነብያችንም (ሠ.ዐ.ወ) በበደዊኑ እና በባልደረቦቻቸው መሀከል የተፈጠረውን አሉታዊ ነገር "ባልደረቦቼ ተበሳጭተውብሀል፡፡ ስለዚህም ለኔ የተመኘኸውን ለእነሱም ተመኝላቸው" አሉት፡፡ በደዊኑ የተባለውን አደረገ፡፡ በደዊኑ ከሄደ በኋላ ወደ ባልደረቦቻቸው በመዞር ይህንን ተናገሩ፡- ‹‹በእኔና በበደዊኑ መሀከል የሆነው ነገር ግመሉ ያመለጠችውን ሰው ታሪክ ይመስላል፡፡ ያመለጠችውን ግመል ለመያዝ ሰዎች እየተንጫጩ ከኋላዋ ይሮጣሉ፡፡ ግመሏ የባሠ እየደነበረች ትሮጣለች፡፡ የግመሏ ባለቤት ለሠዎች "እኔንና ግመሌን ተዉን፡፡ እኔ ከናንተ በላይ አውቃታለሁ፡፡ ከእናንተ በተሻለ እይዛታለሁ" አላቸው፡፡ ጥቂት ቴምሮችንም ሰብስቦ ወደ ግመሏ ተጠጋ፡፡ ግመሏም በዝግታ ወደ እሡ መጠጋት ጀመረች፤ ቀስ ብሎም ገመድዋን አስገባላትና እላይዋ ላይ ወጥቶ መጋለብ ያዘ፡፡ እኔም በደዊኑ ያንን ሲናገር እናንተን ብከተል ኖሮ በደዊን በመደንበር ወደ ጀሀነም በተጓዘ ነበር፡፡"[97]

ይህ የሚያሳየን ሠዎችን በማስተማር ስራ ላይ ስነ ልቦናቸውን መመልከትና እንደየሁኔታቸው ማስተናገድ ትልቁ ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡

---

[97] አል ሀይታሚ መጅ ሙአል ዘዋ ኢድ 160

[97] ቲርሚዝ ዙህድ 37 ደረሚ ሪቃቅ 118፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙስነድ III 63. ነሳኢ አል-ሱነን አል-ኩብራ III 443 አል-በይሀቂ አል-ሡነን አል-ኩብራVII 12

ከዚህ በተጨማሪ ከዚህ ታሪክ የምንማረው የሠው ልጅ በተፈጥሮው ለደግነትና ለችሮታ የተለየ ቦታ መስጠቱን ነው።

አንድን ሠው በደግነት ስንቀርበው ጠላታችን ከነበረ ጠላትነቱ ይወገዳል ወይም ይቀንሳል። ጠላትም ወዳጅም ካልነበረ ወደ ወዳጅነት ይጠጋል። ወዳጅ ከነበረ ደግሞ ወደ በለጠ ወዳጅነት ይሸጋገራል። በኛ ባህላዊ አባባል መሠረት፦‹‹የአንድ ሲኒ ቡና መልካም አቀባበል ለ40 አመት ይወሳል።››

## ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ለድሆችና ለተቸገሩ ሰዎች ያሳዩ የነበረው ደግነት

ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ችግረኞችን የሚቀርቡት በፍቅርና በወዳጅነት ነበር። አብደላ ኢብን አምር እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፦

አንድ ቀን ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ወደ መስጂድ መጡ። ችግረኞች በአንድ ጎን ተቀምጠዋል። በእነሱ በኩል ተቀመጡና ከእነሱ ጋር መሳሳቅና ማውራት ያዙ፤ ከዚያም ይህን ተናገሩ፦ "ለስደተኛ ድሆች መልካም አቀራረብ ይኑራችሁ። እነሱ ከሀብታሞች 40 አመት ቀድመው ነው ጀነት የሚገቡት። ምክንያቱም ከገንዘብና ከንብረት ላይ የሚደረግ ምርመራ የለባቸውምና"[98]

ከዛም ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይህን ዱአ አደረጉ፦ “አላህ ሆይ! ልክ እንደ ድሆች አኑረኝ። እንደነርሱም ግደለኝ። ከእነርሱ ጋርም ቀስቅሰኝ”

"ሁሉም ነብያት ጀነት የሚገቡ ቢሆንም ሁላቸውም በተሠጣቸው ፀጋ እና በተላኩበት መልእክት ይጠየቃሉ (ይመረመራሉ)። ቁርአን ይህን ሁኔታ ሲያብራራ፦

﴿ فَلَنَسْـَٔلَنَّ ٱلَّذِينَ أُرْسِلَ إِلَيْهِمْ وَلَنَسْـَٔلَنَّ ٱلْمُرْسَلِينَ ﴾ الأعراف: ٦

«እነዚያንም ወደነሱ የተላኩባቸውን (ሕዝቦች)፣ መልክተኞቹንም በእር□□ እንጠይቃለን፡፡» **(አል-አዕራፍ፡ 6)**

ሀብታም የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ነበሩ፡፡ ነብያችንም (ሠ.ዐ.ወ) ለነዚህ ባልደረቦቻቸው ህይወትና ንብረታቸውን በአላህ መንገድ ለሚደረግ ትግል በማዋላቸው አመሰግነዋቸዋል፡፡ አላህም በቁርአኑ፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ ٱشْتَرَىٰ مِنَ ٱلْمُؤْمِنِينَ أَنفُسَهُمْ وَأَمْوَٰلَهُم بِأَنَّ لَهُمُ ٱلْجَنَّةَ يُقَـٰتِلُونَ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ فَيَقْتُلُونَ وَيُقْتَلُونَ وَعْدًا عَلَيْهِ حَقًّا فِى ٱلتَّوْرَىٰةِ وَٱلْإِنجِيلِ وَٱلْقُرْءَانِ وَمَنْ أَوْفَىٰ بِعَهْدِهِۦ مِنَ ٱللَّهِ فَٱسْتَبْشِرُوا۟ بِبَيْعِكُمُ ٱلَّذِى بَايَعْتُم بِهِۦ وَذَٰلِكَ هُوَ ٱلْفَوْزُ ٱلْعَظِيمُ ﴾ التوبة: ١١١

«አላህ ከምእምናን ነፍሶቻቸውንና ገንዘቦቻቸውን ገነት ለእነሱ ብቻ ያላቸው በመኾን ገዛቸው፡፡ በአላህ መንገድ ላይ ይጋደላሉ፡፡ ይገድላሉም፤ ይገደላሉም፡፡ በተውራት በኢንጅልና በቁርኣንም (የተነገረውን) ተስፋ በእርሱ ላይ አረጋገጠ፡፡ ከአላህም የበለጠ በኪዳኑ የሚሞላ ማነው? በዚያም በእርሱ በተሻሻጣችሁበት ሽያጫችሁ ተደሰቱ፡፡ ይህም እርሱ ታላቅ ዕድል ነው፡፡ » **(አል-ተውባህ :111)**

ከሀብታሞች መሀከል የሆኑት አቡበከር ሢዲቅ (ረ.ዐ) የነብያችን የቅርብ ወዳጅ ነበሩ፡፡ ከሀብትና ንብረታቸው ባሻገር እጅግ የመተናነስ ኑሮን ይኖሩ ነበር፡፡ አላህ (ሡ.ወ) በቅዱስ ቁርአኑ ከነብዩ ጋር በሰውር ዋሻ ለነበራቸው ቆይታ ያወሳቸዋል፡፡ እኚህ በቁረይሾች ዘንድ የተከበሩ የንግድ ሰው -እንደ አይሻ (ረ.ዐ) ገለፃ- ሲሞቱ ከአንድ ግመልና ከአንድ አገልጋይ ውጭ ዲርሀም (የብር ሳንቲም) ሆነ ዲናር (የወርቅ ሳንቲም) በእጃቸው ላይ አልቀረም፡፡ አገልጋዩም ለኡመር (ረ.ዐ) (ቀጣዩ ኸሊፋ) የሚሰጥ ነበር፡፡ አቡበከር (ረ.ዐ) ሁሉንም ንብረታቸውን ያዋሉት በእውነት መንገድ ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ጎን በመሆን ነበር፡፡

አቡበከር (ረ.ዐ) እጅግ አስቸጋሪ በነበረው የኢስላም የመጀመሪያዎች አመታት በከሀዲያን ስር ያሉ እስልምናን የተቀበሉ ባሪያዎችን ነፃ በማውጣት ገንዘባቸውን በአላህ መንገድ አውለዋል። ንብረትና ሀብታቸው ከጉራና መመፃደቅ ይልቅ ወደ መልካም ስራ ይመራቸው ነበር። አቡበከር (ረ.ዐ) ከሀብትና ንብረት ጋር እንዴት ፍፁም ኢስላማዊ ህይወት መኖርና ሐብትን እንዴት በአላህ መንገድ ማዋል እንደሚቻል ለመረዳት ትልቅ ምሳሌ ነበሩ።

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረው ነበር፡- "የሁሉንም ሰዎች ውለታ መልሰና። የአቡበከር ሲቀር። የአቡበከር ውለታ ከባድ ነውና አላህ በፍርዱ ቀን ይመልስለታል። በአቡበከር ንብረት የተጠቀምኩትን ያህል በማንም ንብረት አልተጠቀምኩም። ከሁሉም የቀረበ ጓደኛ ምረጥ ብባል የምመርጠው አቡበከርን ነው።" [99]

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ሲናገሩ "ሰዎች ሁሉ እንደ ማበጠሪያ ጥርስ እኩል ናቸው። ከሚለያዩበት መልካም ባህሪያቸው በቀር።"[100]

ከኢስላም በፊት የአላህ መልእክተኛ ባልደረቦች በጎራ በጎራ የተከፋፈሉ ሀብታምና ደሀ፣ ባሪያና አሳዳሪ፣ የእገሌ ዘር እና የእገሌ ዘር በመባባል እርስ በርስ ደም ይፋሰሱ ነበር። ከኢስላም መምጣት በኋላ ግን ወንድማማችነት የሚሠማቸውና የሚተሳሰቡ ህዝቦች ሆኑ።

ይህ ታሪክ ይህን ሁኔታ የበለጠ ያብራራዋል። መካ ከተቃናች በኋላ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.አ.ወ) ቢዛንታይንን ለሁለተኛ ግዜ ለማጥቃት

---

[99] 113 ቲርሚዝ 15፡ ኢብን ማጃህ ሙቀዲማህ 11፣ አህመድ ኢብን ሀንበል አል-ሙሠናድ II 253፡366፣ ኢብን ሂባን አል-ሠሂህ XV 273

[100] አል-ቃዲእ ሙስነድ አል-ሺሀብ I 145፣ አል-ሀጢብ አል-ባግዳዲ ታርክ በግዳድ VII 57፣ ኢብን ዲየእ አል-ካልሚ ዱአፋ III 248፣ ኢብን ሂባን አል-መጅሩሂን 1፡198፣ ኢብን ሀጀር አል-አስቀላኒ ሊስንድን አል-ሚድዝ II 42

እቅድ አወጡ፤ ለዚህም የዘይድ ልጅ የሆነውን ኡሳማ (ረ.ዐ) የጦሩ አዛዥ አድርገው ሾሙት:: ኡሳማ የ21 አመት ወጣትና ነፃ የወጣ ባሪያ ልጅ ነበር፡፡ ሁሉ ነገር ነብያችን ከዚህ አለም በሞት ከመለየታቸው በፊት እንዳቀዱት ይሆን ዘንድ አቡበክርን (ረ.ዐ) (የወቅቱ ከሊፋን) ጨምሮ ታላላቅ ሠሀቦች ከዚህ የ21 አመት የባሪያ ልጅ ኋላ ተሠልፈው በሱ አመራር ስር መጓዝ ቀጠሉ፡፡ ከኡሳማ (ረ.ዐ) በቀር ሌሎች በእግር ነበሩ፡፡ ኡሳማም በመንገዳቸው መሀል ከፈረስ ወረዱና አቡበክርን (ረ.ዐ) በፈረስ እንዲጓዙ ጋበዙ፡፡

አቡበክርም ይህን መለሡ፡- "ኡሳማ ሆይ! የአላህ መልእክተኛ የሾሙት አንተን ነው፡፡ በአላህ መንገድ እግሮቼ ትንሽ አቧራ ይቅመሱ"[101]

ይህ የሚያሳየን ከኢስላም በኋላ ባሪያና አሳዳሪ፣ ጥቁርና ነጭ፣ ደሀና ሀብታም ምንም ቦታ እንደሌላቸው ነው፡፡ ማእሩር ኢብን ሠውይድ ይህን ታሪክ አስተላልፈዋል፡-

"አቡዘርን አዲስ ልብስ ለብሶ ተመለከትኩት፡፡ ባሪያውም ልክ እንደሱ አዲስ ልብስ ተጎናፅፏ፡፡ ለምን እንደሆነ ጠየቅኩት፡፡ እሡም፡- ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ይሄን ብለዋል አለኝ፡-

"አገልጋዮቻችሁ ወንድሞቻችሁ ናቸው፡፡ በአላህ ፍቃድ አገልጋያችሁ ሆነዋል:: ማንኛውም አገልጋይ ያለው ሙስሊም ከሚመገበው ይመግበው፣ ከሚለብሰው ያልብሰው፣ የማይችለውን ስራ ፈፅሞ አይዘዘው፤ ካዘዘውም ያግዘው"[102]

አንድ ወቅት ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አንድ ጥቁር አገልጋይ አስታውሰው፡- "ምነው ካየሁት ቆየሁ፡፡ የት ሄዷል?" ሲሉ ጠየቁ፤ "ሞቷል" ብለው

---

[101] 115 ኢብን ከሲር አል-ቢዳው ዐን-ነንያህ III 309

[102] ቡኻሪ- ኢማን 22፣ ሙስሊም አይመን 40፣ አቡዳውድ አዳብ 124፣ ቲርሚዝ ቢር 29፣ አህመድ ኢብን ሀንበል-አል ሙስነድ ቅፅ 58 ገጽ 161

መለሱላቸው፡፡ ነብያችንም (ሠ.ዐ.ወ) "ለምን አልነገራችሁኝም?" ሲሉ ተቆጡ፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ትኩረት ይሰጡታል ብለው ስላልገመቱ ነበር ሶሐቦች ያልነገሯቸው፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ግን ወደ ቀብሩ እንዲወስዷቸው ጠየቁ፤ ቀብሩ ላይም ፀሎት አደረጉለት፡፡[103]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባሪያዎችን ነፃ ማውጣትና እነሡን ከፍ ማድረግ ያስደስታቸው ነበር፡፡

ከውዷ ባለቤታቸው ከኸዲጃ (ረ.ዐ) በስጦታነት ከተበረከተላቸው ከአገልጋያቸው ከዘይድ ኢብን ሀሪስ ጋር የነበራቸው ግንኙነት አስገራሚ ነበር፡፡ ዘይድን ነፃ ካወጡት በኋላ ከእሳቸውና ከቤተሰቦቹ እንዲመርጥ ጠየቁት፡፡ እሱም ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) መረጠ፡፡ በዛ አስቸጋሪና የቁረይሾች ተንኮል አስከፊ በነበረበት ወቅት እንኳን ከእሳቸው ጋር መሆንን መረጠ፡፡ ነብያችንም አስቸጋሪ ጊዜዎችን ካለፉ በኋላ ለዘይድ ከፍ ያለ ቦታ ሰጡት፡፡ በተቡክ ጦርነትም ጦሩን በአዛዥነት እንዲመራ ሾሙት፡፡ በዚህ ጦርነት የመስዋዕትነት ማእረግን ያገኘ ሲሆን ለትውልድ ታሪኩ የሚተላለፍ አንፀባራቂ ኮኮብ ሆኗል፡፡ ህይወቱም ከባርነት እስከ ንጉስነት የተጓዙትን ነብዩላህ ዩሡፍን (ዐ.ሠ) ይመስላል፡፡[104]

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) በሀዲሳቸው እንዲህ ይላሉ፡- "ባሪያዎቻቸውን የሚያሠቃዩ ጀነትን አያገኙም"[119]

[103] ቡኻሪ ሠላት 72፣ ሙስሊም ጀናኢዝ 71፣ አቡ ዳውድ ጀናኢዝ 57፣ ኢብን ማጃህ ጀናኢዝ 32፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል ሙስነድ II 353-388.

[104] ኢብን ሐጀረል አስቀላኒ አል-ኢሰባህ ፊተምይዝ አል-ሠሀባህ II 598-601፣ ኢብን አብዱልበር-አል-ኢስቲአብ

ለሰው ልጆች ካላቸው እዝነትና ፍቅር የተነሳ አገልጋዮችን ‹‹ባሪያ›› ብሎ መጥራትን ከልክለዋል፡፡ ‹‹ልጄ›› ብለው እንዲጠሯቸውም አዘዋል፡፡[105]

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ከባሪያዎች ዘንድ ይሄዱና ይጫወቱ ነበር፡፡ የታመሙትን ይጠይቁ፤ የሞቱትን ይቀብሩም ነበር፡፡ ግብዣዎቻቸውንም በክብር ይታደሙ ነበር፡፡ አቡዳውድ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ነብያችን እንዲህ ብለዋል፡- "ለስግደቶቻችሁ አትኩሮትን ስጡ፡፡ በስራችሁ ባሉ አገልጋዮች ጉዳይ አላህን ፍሩ፡፡" (አቡዳውድ፣አዳብ 124)[106]

ሁሉም የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረቦች የነብያችንን (ሰ.ዐ.ወ) ምርጥ ባህሪ ለመላበስ ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡ ይህ የኡመር (ረ.ዐ) ታሪክ ጥሩ ማሳያ ነው፡፡ አስለም (ረ.ዐ.) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፡-

አንድ ቀን ከዑመር ኢብኑል ኸጧብ (ረ.ዐ) ጋር በመሆን ገበያ ወጣን፡፡ እንዲት ወጣት ሴት ከኡመር ጀርባ በመጠጋት፡- "የምዕመናን መሪ ሆይ! ባለቤቴ ልጆችን ጥሎብኝ ሞተ፡፡ ልጆቼ ስለ ራሳቸው እንኳን ጥንቃቄ የሚያደርጉበት እድሜ ላይ አልደረሱም፡፡ የምናርሰው መሬትም ሆነ የምናረባው እንሰሳ የለንም፡፡ ልጆቼ በረሀብ እንዳይሞቱብኝ እሠጋለሁ፡፡ እኔ በሁደይቢያ ስምምነት ላይ የነበረው የሁፋፍ ኢብን አይመን አል ጊፋሪ ልጅ ነኝ …."

ዑመርም ይህን በሰሙ ጊዜ "ታላቅ ሰው" በማለት በዘካነት የተሰበሰቡ ንብረቶች ወደሚቀመጡበት ስፍራ በመጓዝ ሁለት ትልልቅ እህል የተሞሉ ከረጢቶችን በግዙፍ ግመል ላይ በመጫንና በከረጢቶቹ ላይ ልብሶችን በመጨመር መጡ፡፡ የግመሉን ልጓም ለሴትየዋ ካስያዝዋት በኋላ፡-

---

105 ቡኻሪና ሙስሊም

106 ቲርሚዝ ቢን ማጃህና አህመድ

"ግመሉን ውሰጂ። ይህን ከመጨረስሽ በፊት አላህ የበረከቱን በር ይከፍትልሻል" አሏት። ከዛም ዱዓ አደረጉላት። ባቅራቢያቸው የነበረ አንድ ሠው ይህን ተመልክቶ "የምእመናን መሪ ሆይ! ለዚህች ሴት ከልክ በላይ ነው የሠጧት" አለ ዑመርም (ረ.ዐ)፡- "የዚህች ሴት አባት በሀደይቢያ ስምምነት ላይ ከአላህ መልእክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) ጋር አብሮ ተቀምጧል። በጌታዬ እምላለሁ። እኔ ራሴ ለዚህ ምስክር ነኝ። የዚህች ሴት ወንድምና አባት ቤተ መንግስቱን በያዝንበት ግዜ ትልቁን ድርሻ ተወጥተዋል። በእነሱ የተነሳ እኛም ከቱሩፋቱ ተቋድሰናል"።[121]

አስለም (ረ.ዐ) በሌላ ዘገባ፡- "በአንድ ወቅት መዲና በሚገኝ ኮረብታ በምሽት እየተንሸራሸርን ነበር። አንዲት ሴት በእሳት ላይ ውሀ ጥዳ ተቀምጣለች። ልጆቿ ያለቅሳሉ፤ ኡመርም (ረ.ዐ) ጠየቁ "ልጆቹ ለምንድን ነው የሚያለቅሱት?" "እርቧቸው" አለች ሴትየዋ።

ኡመር ከተጣደው ድስት ውስጥ ያለው ድንጋይ እንጂ ሌላ አለመሆኑን ተመለከቱ። ይህች እናት ይህን የምታደርገው ልጆቿ ምግብ እየሠራችልን ነው በሚል ተስፋ ዝም እንዲሉና እንቅልፍ እንዲጥላቸው መሆኑን ሲረዱ አይናቸው በእንባ ተሞላ። ወዲያውም ግምጃ ቤት (በይተል ማል) በጥድፊያ አመራን። ዑመር እህል በትከሻቸው ተሸከሙ። ‹‹ልያዝልዎት›› ስላቸው እንዲህ በማለት ከለከሉኝ፡-

"አስለም ሆይ፣ እኔው እራሴ እሸከመዋለሁ። በእነዚህ ህፃናት በቀጣዩ አለም የምጠየቀው እኔ እንጂ አንተ አይደለህም›› አሉ። ወደዚህች ሴት ቤት ምግብ ተሸክመን ተመልሰን መጣን። ዑመር (ረ.ዐ) ራሳቸው ምግብ ማብሰል ጀመሩ። ጭሡና አመዱ ፂማቸው ላይ ሲከማች እስክመለከት ድረስ። ለህፃናቱ ምግቡን ካቀረቡ በኋላ ቁጭ ብለው በጉጉት ይጠብቋቸው ጀመር። አንዲት ቃል መናገር እስክፈራ ድረስ አንበሳ መስለው ነበር። ልጆቹ ጠግበው መሳቅ እስኪጀምሩ ድረስ ዑመር (ረ.ዐ) ከተቀመጡበት አልተነሱም። ከዛም ልጆቹ በፈገግታ መጫወት ሲጀምሩ

ተነሱና፡- ‹‹አስለም ሆይ፣ እኚህ ህፃናት መሳቅ ሳይጀምሩ ጥያቸው መሄድ አልፈለኩም፤ ሲጫወቱ ስመለከት ተደሰትኩ” አሉኝ፡፡

በኢስላም ለችግረኞች ደግና አዛኝ የሆነ ሰው ችግራቸውን በትእግስት ካሳለፉት ችግረኞች እኩል ምንዳ አለው፡፡ በችሮታው የቀጣይ አለም ደስታን ያገኛል፡፡ ችግረኛው ስቃይን በመሸከሙ የሚመነዳውን ያህል፡፡

"በባህሪው መልካምነት የሚንፀባረቅበት አማኝ ያስደንቀኛል፡፡ ይህ ምርጥ ባህሪ የሙእሚን ብቻ ነው፡፡ ጥሩ ነገር ቢያጋጥመው ለአላህ ምስጋናውን ያደርሳል፡፡ ይህ ለሡ ጥሩ ነው፡፡ አስቸጋሪ ነገር ቢያገጥመውም ይታገሳል፡፡ ለአላህ ምስጋና ያደርሳል፡፡ (ይህም ለሡ መልካም ነው)፡፡[107]

በአንድ ወቅት ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በመዲና ተቀምጠው እያለ የተቸገሩ ጎሳዎች ወደ እሳቸው መጡ፡፡ እኚህ ጎሳዎች ጫማ የሌላቸውና ከረሀብ የተነሳ ቆዳቸው ከላያቸው ላይ የተጣበቀ ነበሩ፡፡ ነብያችን የነዚህን ሠዎች ሁኔታ ሲመለከቱ እጅግ አዘኑ፡፡ ፊታቸው ተቀያየረ፡፡ ቢላልን ጠርተው አዛን እንዲልና ምዕመናንን እንዲሠበስብ ነገሩት፡፡ ባልደረቦቻቸውም ያላቸውን በማዋጣት ልክ የሌለው ልግስናቸውን አስመሰከሩ፡፡[108]

በየትኛውም ማሕበረሰብ ውስጥ ድሃ፣ ሐብታምና መካከለኛ መደብ ምንጊዜም ይኖራሉ፡፡ በነዚህ የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት የሚመለከቱ መርሆዎች በቁርአንና በሐዲስ በብዛት ይገኛሉ፡፡ በአላህ እና በነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) የተወደሱ የሰው አይነቶች ቢኖሩ አመስጋኝ፣ ሀብታምና ታጋሽ ደሀ ናቸው፡፡

ሀብታም ማድረግ ያለበት አላህ (ሱ.ወ) ከሠጠው ነገር ላይ መስጠት ሲሆን ደሀ ደግሞ አላህ ባመጣበት ነገር መታገስ ነው፡፡

---

[107] ሙስሊም አህመድና ቢን ሂባን

[108] ሙስሊምና አህመድ

አብዱረህማን ኢብን አውፍ “አቡበከር እና መሰሎቻቸው የአመስጋኝ ሀብታሞች ምርጥ ምሳሌ ናቸው። አቡዘር አልጊፋሪ፣ አቡ ደርዳእ እና መሰሎቻቸው ደግሞ የታጋሽ ድሆች ምርጥ ምሳሌ ናቸው” ብለዋል።

የእነዚህ ሠዎች አኗኗር አንድ አይነት እና ተቀራራቢ ሲሆን ለዚህም የህይወት መመሪያቸው "ሁሉም ሀብት የአላህ ነው" የሚለው ነው። ለዚህም ኢስላም የጀነት ቁልፍ ያረገው ሀብትን ወይም ድህነትን ሳይሆን አላህን አመስጋኝ መሆንን ነው።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እንደተናገሩት፡- "አላህ ይህን ማህበረሰብ የሚረዳው በደካሞች ዱዓ፣ ቅንነት ነው።"[109]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ጦርነቶችን ሲከፍቱ በድሆች ፀሎት እንዲጀመር ያደርጉ ነበር። የሡፋ ህዝቦችን ችግር ከተመለከቱ በኋላ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ። "አላህ ያዘጋጀላችሁን ብታውቁ ኖሮ ድህነታችሁ እንዲጨምር በተመኛችሁ ነበር።[110]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ስግብግብነት እንዲወገድ ሲያስተምሩ "አንድ ሠው ከሚጠለልበት ቤት፣ ከሚበላው ምግብና ከሚጠጣው ውሀ እንዲሁም ሠውነቱን ከሚሸፈንባቸው አልባሳት በቀር መብት የለውም"[111]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በሌላ አስተምህሮታቸው "ከከውሰር ወንዝ መጀመሪያ የሚጠጡት ድሆች ሲሆኑ አላህ በእሱ ላይ የተመኩትንና የታገሡትን ይወዳል።[112]

---

[109] ቡኻሪ፣አቡ ዳውድ፣ ቲርሚዚ፣ ነሳኢና አህመድ

[110] ቲርሚዚ ቢን ሂባን በዛር እና ጦበራኒ

[111] ቲርሚዚ አህመመድ ሐኪምና በይሐቂ

[112] ቲርሚዝ

በሌላ ዘገባም "እናንተ መሀከል "የተጎሳቆሉና ገፅታቸው የከሠለ ሰዎች አሉ። ፀሎት ቢያደርጉ ግን የነሡ ጥያቄ ፈፅሞ አይመለስም። በራእ ኢብን ማሊክ ከእነሱ ውስጥ ነው።" [113]

በራእ (ረ.ዐ) የሚቆይባት ቦታም ሆነ ምግብ ያልነበረው የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረባ ሲሆን ድህነቱን በሠላም ተቀብሎ በትዕግስት የሚኖር ሰው ነበር። ኡመር (ረ.ዐ) ዘመን የአላህ መልዕክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ጦርነት ሊሸነፉ ሲሉ በራእን (ረ.ዐ) ጠርተው ዱዓ እንዲያደርግ ጠየቁት። እሡም አደረገ። ከዛም ይህን አለ፡-

"በጌታዬ ይሁንብኝ ነገ ታሸንፋላችሁ። እኔ ደግሞ መስዋዕት እሆናለሁ" በነጋታው ሙስሊሞች አሸነፉ። በራእም (ረ.ዐ) ለረጅም ጊዜ ሲጠብቀው የነበረውን ነገር አገኘ። በዚህ የበራእ ዱአ እንደማይመለስ ነብያችን የተናገሩት ትንቢት እውን የመሆኑን ተአምር መመልከት እንችላለን።[114]

የነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ህይወት በተአምራት፣ በታማኝነት፣ በሀቀኝነት፣ በወዳጅነት፣ በመተናነስ .... የተሞላ ነው። ለባለቤታቸው አይሻ እንዲህ ብለው ነበር፡-

"አይሻ ሆይ! ደካሞችን ውደጂ፣ አስጠጊያቸው፣ አላህ የፍርዱ ቀን ያስጠጋሻልና።››

"አይሻ ሆይ! የለመነሽን ሰው በባዶ እጅ ፈፅሞ አትመልሺ፤ ራስሽን በቴምር ግማሽ ቢሆን ከእሳት ጠብቂ"[115]

## ሰዎች በነብያችን ትምህርት ያገኙት ሂደታዊ ለውጥ

113 ቲርሚዝ ጦበራኒ በዛር

114 ኢብን አብዱል በር

115 ቲርሚዚና በይሐቂ

ኢስላም የለውጥ መልእክት ነው፡፡ ነገር ግን ቀድሞ የነበረን መልካም ነገር አይቃወምም፡፡ የነበረውን ስርአት መልካም ጎኑን ቀጥሎ መጥፎውን ማስወገድ እንጂ ሁሉንም የማፈራረስ አላማ የለውም፡፡

በራሳቸው መተማመን ያላቸው ሠዎች ብቻ ፈጣን ለውጥን ማምጣት ይችላሉ፡፡ ህብረተሰብን ግን በአንድ ሌሊት አስተምሮ (ለውጦ) መጨረስ ፈፅሞ አይቻልም፡፡ በሂደት እንጂ፡፡ ለዚህ ምርጥ ምሳሌ ኢስላም የባሪያ ስርአትን ያስወገደበት መንገድ ነው፡፡

ኢስላም ባርነትን የተዋጋው መጀመሪያ በበሪያ አያያዝ ላይ ለውጥን በማወጅ ነው፡፡ በተደጋጋሚ ባርነትን የማያበረታቱ ነገሮችን በማወጅ ባርነትን ባዶ እንዲቀር አደረገው፡፡ የባሪያዎችን ስፍራ ከፍ እያደረገና የአሳዳሪዎችን ግዴታ እያበዛ በባሪያና በአሳዳሪ መካከል ያለውን ልዩነት አጠበበው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ከባሪያ ጋር አንድ ላይ መመገብና ልብስ መጋራትን ለመጀመሪያ ጊዜ ተገበሩ፡፡ ሰውን መጨቆኛ መሳሪያ የነበረው የባሪያ አሳዳሪ ስርአት በኢስላም ባህሪውን አጣ፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ባሪያዎችን ነፃ ያወጡ አሳዳሪዎች ነጻ የለቀቋቸውን ባሪያዎች እንዲያስተምሩና እንዲመግቡ ደነገጉ፡፡ ባሪያዎችን ያልተገባ አያያዝ መያዙ ገነትን እንደሚያሳጣ አስጠነቀቁ፡፡ ባሪያን ነፃ ማውጣት ትልቅ የአምልኮ አይነት መሆኑን አስተማሩ፡፡ በአንድ ወቅት አቡዘር ባለማወቅ አገልጋዩን አላግባብ መያዙን ተመለከቱ፤ በቁጣ ይህን አሉት፡-

"አቡዘር ሆይ! ኢስላም ከመምጣቱ በፊት የነበረው የመሀይምነት አሻራ አልለቀቀህምን? ሲሉ ጠየቁት፤ በመቀጠልም፡- ‹‹የአላህን ፍጡር በክፉ አትያዙ፣ ደመነፍሳችሁ አያሸንፏች፡፡ ነፃ አውጧቸው፡፡ ከልክ በላይ አትዘዟቸው፤ ከልክ በላይ ካዘዛችኋቸው አግዟቸው፡፡"[116]

---

[116] ቡኻሪ፣ ሙስሊም

አንድ ሠው ባሪያውን ለሴት ልጁ ዳረው፤ ከቆይታ በኋላ ሊያፋታቸው ፈለገ፡፡ባሪያውም ለነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አቤቱታ አቀረበ፡፡ ነብያችንም (ሠ.ዐ.ወ) "የጋብቻና ፍቺ መብቶች የአንተ አይደሉም፡፡ ጣልቃ አትግባ" በማለት ገሠፁት፡፡[117]

የአላህ መልዕክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) አማኞች የባሪያዎችን ጥፋት በተደጋጋሚ ይቅር እንዲሉ ያስተምሩ ነበር፡፡ አንድ ግዜ አንዲት ባሪያ ዱቄት ልትገዛበት የተሰጣትን ብር መንገድ ላይ ጣለችው፡፡ ቅጣት በመፍራት ወደቤት መመለስ አልቻለችም፡፡ ታለቅስ ጀመር፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ታሪኳን በሰሙ ጊዜ የጣለችውን ያህል ብር ከሠጧት በኋላ ወደ አሳዳሪዎቿ ወሰዷት፡፡ ከዛም ለባለቤቶቿ የፍቅር ስሜት እንዲኖራቸው ምክር ለገሷቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ለዚህች ባሪያ ይቅርታ አደረጉላት፡፡

ኢስላም ለባሪያ አሳዳሪ ስርዓት ጊዜያዊ እውቅና ሰጥቶ የነበረበት ምክንያት በጦርነት የሚማረኩና እጅ የሚሰጡ ሰዎች በመኖራቸው ነው፡፡ እንዲህም ሆኖ ኢስላም ለባሮች ከአሳዳሪዎቻቸው ያልተናነሰ መብት ይሰጥ ነበር፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

"ምግብ ለሚያዘጋጅላችሁ ሰው ድርሻውን ስጡት፡፡ ከጎናችሁም ይቀመጥ፤ ይህን ማድረግ ካልቻላችሁ አጉርሡት፡፡ የልዕልና ባለቤት የሆነው አላህ እነሱን ለእናንተ ባሪያ አደረገ፡፡ ቢሻው ኖሮ እናንተን የእነሱ ባሪያ ያደርጋችሁ ነበር፡፡"[118]

አብዛኞቹ የአላህ መልእክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) ወዳጆች የባሪያዎችን መብት መጣስን በመፍራት ባሪያዎቻቸውን ነፃ ይለቁ ነበር፡፡ ይህም የኢስላም ብልሀት የተሞላበት የማስተማር ዘዴ ነው፡፡

---

[117] ቢን-ማጀህ፣ በይሀቅ፣ ዳረሚና ጦበራኒ

[118] ቡኻሪ፣ ሙስሊም

## ከሴቶች ጋር በተያያዘ የነብያችን ባህሪ

ከኢስላም በፊት ሴቶች ምንም አይነት የሰብአዊነት ክብር ሳይሠጣቸው እንደ መገልገያ መሳሪያ እየታዩ ቆይተዋል፡፡ አድገው ሴተኛ አዳሪ እንዳይሆኑ በመፍራት ወላጆች ልጆቻቸውን ያለምንም ርህራሄ ከነህይወታቸው ይቀብሩ ነበር፡፡ በሴቶች ላይ የሚፈፀመው ግፍ ከመብዛቱ የተነሳ ለማወቅ አስቸጋሪ ነበር፡፡ አላህ በቁርአኑ፡-

﴿ وَإِذَا بُشِّرَ أَحَدُهُم بِالْأُنثَىٰ ظَلَّ وَجْهُهُ مُسْوَدًّا وَهُوَ كَظِيمٌ ﴿٥٨﴾ يَتَوَارَىٰ مِنَ الْقَوْمِ مِن سُوءِ
مَا بُشِّرَ بِهِ ۚ أَيُمْسِكُهُ عَلَىٰ هُونٍ أَمْ يَدُسُّهُ فِي التُّرَابِ ۗ أَلَا سَاءَ مَا يَحْكُمُونَ ﴿٥٩﴾ ﴾ النحل: ٥٨
- ٥٩

«አንዳቸውም በሴት ልጅ በተበሰረ ጊዜ. እርሱ የተቆጨ ኾኖ. □ቱ □ቁሮ □□ላል፡፡ በርሱ ከተበሰረበት ነገር መጥፎነት. በውርደት ላይ ኾኖ. ይያዘውን? ወይስ በዐፈር ውስጥ ይደብቀውን?[119] (በማለት ያም) ከሰዎች ይደበቃል፤ ንቁ! የሚፈርዱት (ፍርድ) ምንኛ ከፋ!» **(አን-ነሕል፡ 58-59)**

በነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አማካኝ የሴት ልጅ መብቶች መታወቅና መከበር ጀመሩ፡፡ ሴት ልጅ የማህበረሰቡ ጥብቅነትና ክብር ተምሳሌት ሆነች፡፡ እናትነት የሚገባውን ታላቅ ስፍራ አገኘ፡፡ ነብያችን በሀዲሳቸው "ጀነት የምትገኘው ከእናት እግር ስር ነው"[120] ሲሉ አስተማሩ፡፡ በነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ጥረት እናቶች የሚገባቸውን ቦታ አገኙ፡፡

በአንድ ጉዞ ላይ አንጃሻህ የተባለው ባሪያ በሚያሰማው እንጉርጉሮ የተነሳ ሴቶችን የተሸከመው ግመል ደንብሮ እንዲሮጥ ምክንያት ሆነ፡፡[121]

---

[119] ነሳኢ፣ አህመድ ቢን ማሃ

[120] ነሳኢ፣ አህመድ ቢን ማሃ

[121] ግመሎቹ ማራኪ ድምፅ ሲሰሙ ፍጥነት ይጨምራሉ

ነብያችንም (ሠ.ዐ.ወ) ሴቶች እንዳይጎዱ በመጨነቅ "አንጃሻህ ሆይ፣ እንቁዎቹን አደራ። እንቁዎቹን አደራ›› በማለት ተናገሩ።[122] ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ)፦ መልካም ሽቶ እና ሴቶች የዚህች ምድር መደሰቻዎች ናቸው፡ ፡ ሠላት የአይናችን ማረፊያ እንደሆነችው ሁሉ›› ሲሉ ተናግረዋል።[123]

ደስተኛ ቤተሰብ በመፍጠር ዙሪያ የጥሩ ሴት ድርሻ ታላቅ መሆኑ የማይታበል ሀቅ ነው። ከእናት ልብ ወዲያ በፍቅር የተሞላ ቦታ ከየት ይገኛል? እናቶች ከአዛኙ ጌታ እዝነትን በከፍተኛ ሁኔታ የተቸሩ ፍጡራን ናቸው። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሲያስተምሩ፦ "ከእናንተ ውስጥ ምርጡ ለቤተሰብ ምርጥ የሆነ ነው"[124] በሌላ ሀዲሳቸው "አንድ ሰው በራሡ፣ በሚስቱና በልጆቹ ላይ ያወጣው ወጪ እንደ ምፅዋት ይቆጠርለታል።"[125] በዚህም ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የደስተኛ ቤተሰብ መሠረቱ ፍቅር መሆኑን አስተምረውናል።

## ከእንሰሳት ጋር በተያያዘ የነብዩ ባህሪ

ከኢስላም በፊት የነበሩ ሰዎች እንሰሳትን ያለምንም ምህረትና እዝነት ነበር የሚይዙት። እንሰሳት በህይወት እያሉ ከሠውነታቸው ላይ ስጋ ወይም ጭራቸውን ይቆርጡ ነበር። የእንሰሳት ፍልሚያ በማዘጋጀት እንዲጎዳዱ እያደረጉ ይዝናኑ ነበር። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይህን አስቁመዋል። አውግዘዋልም።

---

122 ቡኻሪና አህመድ

123 ነሳኢና አህመድ

124 ቲርሚዚ ቢን ማጃህ ዳርሚን አህመድ

125 ቢን ማጃህ አህመድ ጦበራኒ

አንድ ቀን ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ፊቱ ላይ በእሳት በመጠበስ ምልክት የተደረገበት አህያ ተመለከቱ። እጅግ በጣም በማዘን "የአምላክ ቅጣት ይህን ባደረገ ሰው ላይ ይሁን" ሲሉ ተናገሩ።[126]

ምልክት ማድረግ ካስፈለገ እንኳን የእንሰሳዋን ስቃይ በማያበዛ ስፍራ እንዲሆን ያስተምሩ ነበር።

አንድ ጊዜ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አጥንቱና ቆዳው ብቻ የቀረ ግመል ተመለከቱ። ባለቤቱንም "በዚህ ንግግር በማያውቅ እንስሳ ጉዳይ አላህን ፍራ! እስኪራብ አትጠብቅ" በማለት ምክር ለገሱት።[127]

አብዱላህ ኢብን ጃእፋር (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት አንድ ቀን ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ወደ ባልደረባቸው አትክልት ስፍራ መጡ።ታስሮ የነበረ ግመል ነብያችንን (ሰ.ዐ.ወ) ሲመለከት ማልቀስ ጀመረ። ጭንቅላቱን በማሻሸት አባበሉት! ግመሉም ማልቀሱን አቆመ። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ወደ ግመሉ ባለቤት በመጠጋት፡-

"ይህን ግመል የሠጠህን አላህን አትፈራምን? ግመሉ እንደምትመታው እና እንደምታሰቃየው ነግሮኛል" አሉት።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አዛኝ ወይም እዝነት አልባ የመሆንን ልዩነት እንዲህ ሲሉ አብራርተውታል፡-

"አንዲት ሴተኛ አዳሪ በበረሃ ውሃ ከመጠማቱ የተነሳ አሸዋ እየላሰ የነበረ ውሻ ተመልክታ በማዘን በጫማዋ ውሃ ቀድታ አጠጣችው። አላህም ሀጢያቷን ሁሉ በዚህ የተነሳ ማራት። በተቃራኒው አንዲት ሴት ስለ ድመቷ ፊፅሞ ግድ በማጣት ሁሌም ከማስራቧም ባሻገር ነፍሳትን እንኳ

---

126 ቡኻሪ

127 አቡዳድ ቢን ኡበይድ

ለቃቅሞ እንዲበላ ባለማስቻሏ ምክንያት ድመቱ በረሀብ ስለሞተ ይህች ሴት በዚህ ጭካኔዋ የተነሳ የጀሀነም ሆነች፡፡››[128]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሠዎችን ያለምክንያት ለመግደል የማይሣሡና የገዛ ልጃቸውን ከነህይወታቸው ይቀብሩ የነበሩ ሠዎችን እዝነትና ርህራሄ አስተምረዋል፡፡ ለሠው ልጅ እንኳን ግድ ያልነበራቸውን ፍጡራን ለእንስሳት የሚጨነቁ አዛኝ አደረጓቸው፡፡ ኢብራሂም ቢን አብደላህ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፡-

ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ጋር በመሆን በመጓዝ ላይ ነበርን፡፡ እርሳቸው ለጉዳይ ከኛ ገለል አሉ፡፡ አንዲት ወፍ ከሁለት ጫጩቶች ጋር ተመለከትን፡፡ ጫጩቶቿንም ወሠድንባት፡፡ ወፏ በጭንቅላታችን ላይ ማንዣበብ ያዘች፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ወዲያውኑ፡- ‹‹ማነው ይህቺን ወፍ ጫጩቶቿን በመውሰድ ያበሳጫት? አሁኑኑ ወደ ጎጆዋ መልሱ" ሲሉ ተቆጡ፡፡[129]

በኢስላም አደን የተፈቀደ ቢሆንም ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በእንስሳት መራቢያ ግዜ እንዳይፈፀም አስጠንቅቀዋል፤ ይህም አካባቢያዊና ስነ-ሕይወታዊ ደህንነትን ለመጠበቅ ነው፡፡ ይህም ነብያችን ለዱር እንሰሳ ሳይቀር የነበራቸውን መቆርቆር ያሳያል፡፡ በዚህ አያበቃም የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እዝነት፡፡ እንደ ጊንጥና እባብ ያሉ ጎጂ እንሰሳት እንኳን አደጋ እንዳያደርሱ ከተሰጋ በአንዴ እንዲገደሉ ነው ያዘዙት፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በማጣጣር እንዳይሰቃዩ በማሰብ ነበር፡፡ አደገኛ እንሰሳትን በተመለከተ እንኳ ይህን ምክር መስጠት የእዝነትና የርህራሄ ጥግ አይደለምን?

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እንሰሳትን መራገምን አውግዘዋል፡፡ ከበጥኑቡዋጥ ወታደራዊ ጉዞ ሲመለሱ አንድ ከአንሷሮች (ረዳቶች) የሆነ ሰው

---

[128] ቡኻሪና ሙስሊም

[129] አቡዳውድና አህመድ

ከጓደኛው ጋር የተጋራው ግመል ቀስ እያለ በመሄዱ ሲራገም ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሠሙት፡፡ እንዲህም አሉት፡- "እኛን ከረገምከው ግመል ጋር አታጎዳኘን፡፡ ራስህን፣ ልጆችህንና ንብረትህን አትርገም፡፡››[130]

ይህ ሀዲስ መጨረሻ የሌለውን የኢስላም እዝነት ያሳየናል፡፡[131] የቅዱሳት መሪ በመባል የሚታወቀው በይዘዲ ቢስታሚ ለፍጡራን ከነበረው ርህራሄ እና ፍጡራንን ለአላህ ብሎ ከመውደዱ የተነሳ ብዙ አድርጓል፡፡ ለምሳሌ፡-

በጉዞ ላይ ባለበት ወቅት ደከመውና ከዛፍ ስር ተኛ፤ ሲነቃም ተነስቶ መንገዱን ቀጠለ፡፡ ጥቂት ከተጓዘ በኋላ በተሸከመው ኮረጆ ላይ ከዛፍ ስር የወጡ ጉንዳኖች መኖራቸውን አስተዋለ፡፡ ወደመጣበት ቦታ በመመለስም ጉንዳኖቹን ከነበሩበት አስቀመጠ፡፡ ከቤታቸው ሊያርቃቸው አልፈቀደምና፡፡

ይህ የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ምሳሌ ምን ያህል በልቡ እንዳሳደረና ህይወታቸውን እንደኖረው ያሳየናል፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አጥብቀው ከተናገሯቸው ነገሮች መሀል፡-

"እዝነት በልቡ ያለው ሠው ሁሉም አይነት ጥሩነት አለው"[132]

አዛኝነት የአንድ ሙስሊም መለያ ባህሪው መሆን አለበት፡፡ አላህ በቁርአኑ ደጋግመን አንድናነበው ያስቀመጠልንና የየትኛውም ስራችን መክፈቻ የሆነው "ቢስሚላሂረህማንን አል-ረሂም" "በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህና እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው" የሚለው መልዕክት የሚያስታውሰን የአላህን አዛኝነት ነው፡፡

---

[130] ሙስሊምና ቢን ሂባን

[131]ክላውድ ፊራር የተባለ ክርስትያን ተጓዥ የእስልምና የሞራል ትምህርት በሙስሊሞችና በሌሎች ሕዝቦች መካከል የፈጠረውን የእንስሳት አያያዝና እንክብካቤ ልዩነት ጽፏል፡፡

[132] ቡኻሪና ሙስሊም

ከአላህ ምርጥ ወዳጆች አንዱ የሆኑት ፋደይል ኢብን ኢያድ በአንድ ወቅት ተቀምጠው ያለቅሳሉ፡፡ ምን እንደሆኑ ሲጠየቁ አንድ ሰው መጥፎ እንደሰራባቸውና በዚህ ምክንያት ጀሀነም እንዳይገባ በመፍራት እንደሚያለቅሱ ተናገሩ፡፡

እኚህ የነብያችን አስተምህሮት ውጤት የሆኑ ሠው እዝነት ምን እንደሆነ አሳይተዋል፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በሀዲሳቸው "በምድር ላሉት እዝነት አሳዩ፣ በሠማይ ያለው እንዲያዝንላችሁ ብለዋል፡፡"[133]

## የነብዩ እዝነት ለወላጅ አልባዎች

በሀዲስ እንደተገለፀው "ምርጥ ቤት ማለት ወላጅ አልባ ህፃን በአግባቡ የተያዘበት ቤት ነው፤ መጥፎ ቤት ደግሞ ወላጅ አልባ ህፃን የተበደለበት ነው፡፡"[134] በቁርአንም ስለ ወላጅ አልባ ህፃናት እንዲህ ተብሏል፡-

﴿ فَأَمَّا ٱلْيَتِيمَ فَلَا تَقْهَرْ ﴾ الضحى: ٩

«የቲምንማ. አትጨቁን፡፡»**(አድ-ዱሓ፡ 9)**

በሌላ ሀዲስ ፡-

"የየቲምን ፀጉር የዳበሠ በነካው ፀጉር ልክ ምንዳ ይመነዳል"[135]

ከዚህም በተጨማሪ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሁለት ጣቶቻቸውን በማገጣጠም፡ - እኔና በስሩ ያለን የቲም በደንብ የያዘ ሰው በጀነት እንዲህ ነን" ሲሉ ተናገሩ፡፡[136]

---

[133] ቲርሚዝ ሃኪምና በይሀቂ

[134] ቡኻሪ ቢን ማጃህ

[135] አህመድና ጦበራኒ

[136] ቡኻሪ፣ ቲርሚዚና አህመድ

ለነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አንድ ሰው ቀልቡ እንደደረቀበት ነገራቸው፡፡ እሳቸውም ይህን መከሩት፡-

"የየቲምን ፀጉር ደባብስ፡፡ ድሆችንም መግብ፡፡"[137]

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ከየቲምነት ተነስተው ለአለም ሙሉ መዳኛ ሰበብ መሆናቸውን ገጣሚው እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፡-

የየቲሞች ባለቤት አላህ ነው ታላቁ

በፍቅር ያዟቸው ከቶ እንዳታሳቅቁ

የቲም ደካማ ነው ከቶም እንዳትል

እንባው መሳሪያ ነው በጉንጩ ሲኮል፡፡

## ነቢዩ ለጎረቤት መልካም መሆንን አስመልክተው የሰጧቸው ምክሮች

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በሀዲሳቸው ለጎረቤቶች መልካም እንድንሆን ያዙናል፡፡ እንዲህም ይሉናል፡- "ጅብሪል በተደጋጋሚ ስለ ጎረቤት ሀቅ ያስተምረኝ ነበር፡፡ የውርስ ባለመብቶች ሊያደርጋቸው ነው ብዬ አስካስብ ድረስ፡፡››[138]

በሌላ ሀዲስ፡-

"ሙስሊም ያልሆኑ ጎረቤቶች አንድ፣ ሙስሊም የሆኑት ደግሞ ሁለት መብት አላቸው፡፡ ሙስሊምም ዘመድም የሆነ ጎረቤት ደግሞ ሦስት መብት አለው"[139] የጎረቤት ሀቅ በእነሡ መስኮት አሻግሮ

---

137 አህመድና በይሐቂ

138 ቡኻሪና ሙስሊም

139 አቡበከር አልቁረሺ፣ መካሪመል አኽላቅ ቅጽ 1 ገጽ 105

አለመመልከትን፣ በምግብ ሽታ አለመረበሽን እና እነሱ የማይወዱትን ነገር አለማድረግን ይጨምራል።

ድሃ የነበሩት አቡዘር አል-ጊፋሪ (ረ.ዐ) እንዲህ ይላሉ፡- "ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ከምግቤ ውስጥ ውሀ በርከት አድርጌ እንድጨምር አዘዙኝ፤ ለጎረቤቴ ማካፈል እችል ዘንድ"[140]

አቡዘር የኢኮኖሚ አቅማቸው ደካማ ከሆኑት የአላህ መልዕክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) ሶሐቦች ውስጥ ነው። በመሆኑም ምግቡን ለማብዛት ያለው አማራጭ ውሀን አብዝቶ መጨመር ብቻ ነው። ይህ የሚያሳየው ድህነት እንኳን የጎረቤትን ሀቅ ላለማክበር ምክንያት እንደማይሆን ነው። ኢብን አማር (ረ.ዐ) የሚከተለውን አስተላልፈዋል፡-

"ሠባት ደሀ ቤተሰቦች ነበሩ። አንደኛው ቤተሰብ የበግ ጭንቅላት ተላከለት። ነገር ግን ከመመገብ ይልቅ ጎረቤቶቼ የበለጠ ተርበው ይሆናል በማለት ወደ ሁለተኛው ቤት ላከው። ሁለተኛው ቤተሰብ በተመሳሳይ አስተሳሰብ ወደ ሶስተኛው ቤት ላከው። እንዲህ እያለ የበጉ ጭንቅላት ወደ መጀመሪያው ቤት ተመልሶ መጣ።››[141]

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እዝነት ለሞቱ ሰዎችም ጭምር ነበር። ምን ግዜም አንድ ሰው ከመቀበሩ በፊት እዳ (ብድር) ያለበት እንደሆነ ይጠይቁ ነበር፡ ፡ ከዛም ብድሩ ተከፍሎ እስኪያልቅ የጀናዛ ስግደቱን ያቆዩት ነበር።[142] የእዝነት ነብይ ናቸውና ማንም ሰው ከነ እዳው መቃብር እንዲገባ አይሹም።!

## የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የወንጀለኞችና የምርኮኞች አያያዝ

---

140 ቢን ማጃህና ጦበራኒ

141 አልሐሲም

142 ቢን ሐሰንና ሐሺም

በኢስላም አመለካከት ወንጀልን ለማጥፋት መደረግ ያለበት የመጀመሪያው ስራ የአጥፊዎችን ባህሪ ማረቅ ነው። ለወንጀለኞች የሚወሰነው ቅጣትም አንድ ቤተሰብ ልጁን ለመመለስና ለማረቅ ከሚያደርገው የተለየ አይደለም። በወንጀለኛ ላይ የሚወሰነው ውሳኔ ወንጀለኛውን ለማግለል ሳይሆን ወደ ማህበረሰቡ እንዲቀላቀል ለመርዳት ነው።

አባድ ኢብን ሹራህቢል የተባለ ድሀ ግለሰብ ከአንድ ሰው የአትክልት ስፍራ ውስጥ የተወሰኑ የቴምር ፍሬዎች ሰረቀ። በዚህ ጊዜ ባለቤቱ ስለተመለከተው በቁጣ ክፉኛ ደበደበው። አባድ እጅግ ተጎዳ። ወደ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በመሄድም አቤቱታውን አቀረበ። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይህን አሉ፡-

"እንዳልተማረና ምን እንደሚሠራ እንደማያውቅ አታውቅምን? ከሁሉ በላይ ደግሞ ተርቧል። ልትመግበው በተገባህ ነበር።"[143] የቴምሩ ባለቤት ይህ ንግግር ስለሰረፀው ለሰውየው ቴምሮችና ሁለት ጆንያ ስንዴ ሰጥቶ አሠናበተው።

ይህ የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ንግግር ወንጀለኞችን ለመጠበቅና እነሡን ለማበረታታት ሳይሆን ወንጀሉን ያመጣውን የማህበረሰብ ችግር ለመቅረፍ ያለመ ነው። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ)፡- ልጄ ፋጡማ እንኳ ሰርቃ ባገኛት እጇን ከመቁረጥ አልመለስም" ብለዋል።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለጦር ምርኮኞች እጅግ ያዝኑ ነበር። ይህንን ንግግርም ያዘወትራሉ። "ወንድሞቻችሁ ናቸው። ከምትበሉትና ከምትጠጡት ስጧቸው"[144]

---

[143] ነሳኢና አቡ ዳውድ

[144] ሙስሊም

## ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ከኢስላም ጠላቶችና ሙስሊም ካልሆኑ ወገኖች ጋር በተያያዘ የነበራቸው ባህሪ

አቡ ባስራ አል-ጊፋሪ ወደ ኢስላም ከመግባቱ በፊት የነበረውን ህይወት ሲያስረዳ "ወደ መዲና በመጣሁ ጊዜ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ተቀበሉኝ፡፡ በዛኑ ምሽት የሰባት ፍየሎችን ወተት ጠጣሁ፡፡ ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ስለ ስግብግብነቴ አንድም ቃል አልተናገሩም፡፡ በዛን ምሽት አንዲትም የመከፋት ምልክት ሳያሳዩ እንደራባቸው ተኙ፡፡ በዚህ ምርጥ ባህሪ ተሸንፌ ለኢስላም ተገዛሁ..."

ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ለአለም እዝነት ሆነው እንደ መላካቸው መጠን ለሁሉም ፍጡራን አዛኝና ተንከባካቢ ነበሩ፡፡ አንድ ቀን ጠላቶችን የሚራገምና በነሱ ላይ ጥፋትን የሚጠራ ዱዓ እንዲያደርጉ ባልደረቦቻቸው ጠየቁዋቸው፡፡ ነብያችን ግን ይህን መለሱ፡- "እኔ የዕዝነት ነብይ ነኝ፡፡"[145]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ወደ ጣኢፍ በተጓዙ ግዜ የከተማዋ መሀይሞች፣ ጣኦታውያንና ልበ ደረቆች በድንጋይ ደበደቧቸው፡፡ ጅብሪል (ዐ.ሠ) ወደ እሳቸው መጣና እንዲህ አላቸው፡፡ "እነዚህን ሁለት ተራሮች ላጋጭና በመሀል የሚኖሩትን የጣኢፍ ህዝቦችን ላጥፋቸው?" ነብያችን ግን በዚህ ሀሳብ አልተደሰቱም፡፡ እንዲህ ሲሉ ዱዓ አደረጉ፡- "ጌታዬ ሆይ! እነዚህን ህዝቦች ቀጥተኛውን መንገድ ምራቸው፡፡

ከዝርያቸውም ሙስሊም የሆኑ ልጆችን ፍጠር፡፡[146]

በዚህ ዱዓ የተነሳም የጣኢፍ ህዝብ ሙሉ ለሙሉ ኢስላምን ተቀበለ፡፡

---

[145] ሙስሊምና ቲርሚዝ

[146] ቡኻሪና ሙስሊም

## የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይቅር ባይነት

አላህ ይቅር ማለትን ይወዳል፡፡ ከልቡ ለተፀፀተ ሙእሚን ሁሉ ይቅርታ ሊያደርግ ቃል ገብቷል፡፡ አምላካችን አላህ ከይቅር ባይነቱ ባሻገርም ሰዎች ይቅርታ አድራጊ እንዲሆኑ አዟል፡፡ የአላህን ይቅርታ ለማግኘት መስፈርቶቹ መፀፀት፣ የአላህን ትዕዛዝ መቀበልና ከከለከላቸው ነገሮች መራቅ ናቸው፡፡

ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት ውስጥ እጅግ ገራሚው ይቅርታ አድራጊነታቸው ነው፡፡ ምሳሌ፡-

በኡሁዱ ጦርነት ወቅት የአጎታቸው ሀምዛን ጉበት ለበላችው ሂንድ ይቅርታ ማድረጋቸው እጅግ ይደንቃል፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) መካን ከተቆጣጠሩና ሂንድ ሙስሊም ከሆነች በኋላ አንድ ቀን ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ኋላ በመምጣት "የአላህ መልዕክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) ሆይ! አወቁኝን?" አለቻቸው፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ከአምስት አመት በፊት ኡሁድ ላይ ሀምዛ ሲገደል በደስታ የጮኸችውን ጩኸት በማስታወስ "እንዴት ያንን ጩኸት እረሳዋለሁ?" አሏት፡፡ ይህን ከቶ የማይረሳ መጥፎ ትዝታ ተቋቁመው ግን የአላህን አንድነትና የነብዩን (ሠ.ዐ.ወ) መልዕክተኛነት በመቀበሏ ይቅርታ አደረጉላት፡፡

በሌላ በኩል ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በጭንቀትና በፍርሀት በመካ ይጠባበቃቸው ለነበረውና በግፍ ላባረራቸው የመካ ህዝብ ይህን አሉ፡- "የቁረይሽ ህዝብ ሆይ፣ ምን እንደማደርጋችሁ ነው የምትጠብቁት?" ቁረይሾች ሲመልሱ፡-

"ይቅርታ እንደምታደርግልን እንጠብቃለን፤ አንተ እጅግ ደግና አዛኝ ወንድማችን ነህ፡፡ ደግና አዛኝ የነበረ የወንድማችን ልጅም ነህ፡፡››

ነብያችንም (ሠ.ዐ.ወ) ይህን መለሱ፡-

"ነብዩላህ ዩሱፍ ለወንድሞቹ ከመለሰው የተለየ አልመልስላችሁም፡፡ ዛሬ በእናንተ ላይ ምንም ፍርድ አልፈርድም፡፡ ሂዱ፡፡ ነፃ ናችሁ፡፡ አላህም ይቅር ይበላችሁ፡፡" [147]

በሌላ ንግግራቸውም፡-

"ዛሬ የምህረት ቀን ነው፤ ዛሬ አላህ የኢስላምን ጉልበት በቁረይሾች ላይ ያበረታበት ቀን ነው፡፡"

ከኢስላም ቀንደኛ ጠላቶች አንዱ የሆነው የአቡጃህል ልጅ ኢክርማ በጥመቱ የተነሳ መካ በሙስሊሞች ቁጥጥር ስር ስትሆን ወደ የመን ተሠደደ፡፡ ሚስቱ ግን መካ በመቅረት ሠለመች፡፡ የኋላኋላ ኢክሪማ በሚስቱ ግፊት ወደ መካ በመመለስ ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ጋር ተገናኘ፡፡ ነብያችንም እንዲህ አሉት፡-

‹‹የሸሸኸ ፈረሰኛ፡፡ እንኳን ደህና መጣህ"[148]

በመቀጠል ነብያችን በኢስላም ላይ ያደረሰውን ጥፋት አንድም እንኳን ሳያነሱበት ይቅርታ አደረጉለት፡፡

ሀቢር ኢብን አስዋድ ሌላኛው የኢስላም ጠላት ሲሆን የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ልጅ ዘይነብ ከመካ ወደ መዲና በግመል በምትጓዝበት ወቅት ግመሏን ሆነ ብሎ በማደናቀፍ ከግመሉ እንድትወድቅ አደረገ፡፡ በዚህ ጊዜ ዘይነብ (ረ.ዐ) እርጉዝ ነበረች፡፡ በዚህ አደጋ የተነሳም ልጇን አጣች፡፡ ሀቢር ይህን እና የመሳሰሉ ብዙ ጥፋቶችን አጥፍቷል፡፡ መካ በተቃናች

---

[147] ነሳኢና መይሐቂ

[148] ኢብን ሐጀረል አስቀላኒ አል ሰሐባ ቅፅ4 ገፅ 538

ጊዜም ሊያመልጥ ሞክሮ አልተሳካለትም። በስተኋላ ላይ በመስለም ወደ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) መጣ። ነብያችንም ይቅርታ አደረጉለት።[149]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በተደጋጋሚ "ጌታዬ ሆይ! ህዝቦቼን ማራቸው። አያውቁምና" ይሉ ነበር።[150]

ሀማማህ የተባለ ነጋዴ ኢስላምን በመቀበሉ ምክንያት ከቁረይሾች ጋር የነበረውን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ አቋረጠ። በርሱ ቀዬ የሚያልፈውን የቁረይሾች የንግድ መስመር ለመቁረጥም ወሰነ። በዚህም የተነሳ ቁረይሾች ደነገጡ። ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ንግዱን እንዲቀጥል ሐማማህን እንዲያናግሩላቸው ጠየቁ። ነብያችም (ሠ.ዐ.ወ) ለሐማማህ ደብዳቤ ፃፉለት። በዚህም ምክንያት ንግዱን ቀጠለ። ሙስሊሞችን ለሦስት አመታት በማእቀብ የቀጡና ያንገላቱ ቁረይሾችን ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ይቅርታ አደረጉላቸው። ቁረይሾች በዚህ ወሰን የለሽ ይቅር ባይነት በመደነቅ ወደ እስልምና ገቡ።

አንድ ቀን 80 ሰዎች ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ለመግደል መጡ፤ እንዳጋጣሚ ሆኖ ሁሉም ተያዙ። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ግን ለእያንዳንዳቸው ይቅርታ አደረጉላቸው።

ኸይበር በሙስሊሞች ቁጥጥር ስር ከዋለች በኋላ አንዲት ሴት ለነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የተመረዘ ምግብ አመጣችላቸው። ነብያችን ምግቡ መመረዙን አወቁ። አይሁዷ ሴትም ስራዋን ተናዘዘች። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ግን ይቅርታ አደረጉላት"[151]

በቅዱስ ቁርአን እንዲህ ይላሉ፡-

---

149 ያለፈው ምንጭ ገጽ 524-527

150 ቢን ማጃህና አህመድ

151 ቡኻሪና ሙስሊም

﴿ خُذِ ٱلۡعَفۡوَ وَأۡمُرۡ بِٱلۡعُرۡفِ وَأَعۡرِضۡ عَنِ ٱلۡجَٰهِلِينَ ١٩٩ ﴾ الأعراف: ١٩٩

«ገርን ጠባይ ያዝ፤ በመልካምም□እዘዝ፤ ባለጌዎቹንም ተዋቸው፡፡»
**(አል-አዕራፍ፡ 199)**

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የመልካም ስነ ምግባርና ለሠው ልጆች ምጥቀት ምሳሌ ናቸው፡፡ መልካምነታቸው ከጥልቅ ማንነታቸው የሚመነጭ ነበር፡፡ አዲይ ኢብን ኻቲም ይህን ታሪክ ተናግሯል፡-

"ኢስላምን ሳልቀበል በፊት ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) እቤታቸው ጋብዘውኝ ነበር፡፡ በመንገድ ላይ አንዲት አሮጊት ሴት ነብዩን አስቁማ ማውራት ጀመረች፡፡ የምትናገረውን እስከምትጨርስ ለረጅም ጊዜያት ቆመው አዳመጧት፡፡ እኔም በጌታዬ ይሁንብኝ ይህ ሰው ንጉስ አይደለም" አልኩ፡፡

ቤት ከገባን በኋላም ከቆዳ የተሰራና ውስጡም ቅጠል የሆነ ፍራሽ ሰጡኝ፡፡ "እርሶ እዚህ ላይ ይቀመጡ›› ብልም እኔ እንድቀመጥ ጋበዙኝ፡፡ ግብዣቸውን አምቢ ማለት ስላልፈለግኩ ከፍራሹ ላይ ተቀመጥኩ፡፡ እሳቸው ከመሬት ላይ ተቀመጡ፡፡ ይህን ጊዜ ለራሴ፡-

"ይህ አንድ ንጉስ የሚያደርገው ነገር አይደለም" አልኩ፡፡ ጨዋታ ጀመርን፡፡ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የ"ራኩሲ"[152] ሐይማኖት ተከታይ መሆኔን ነገሩኝ፡፡ በእምነቴ የተከለከለ ቢሆንም የህዝቡን 1/4ኛ ግብር ስለወሰድኩ ደነገጥኩ፡፡ በቅፅበት ይህ ሰው ነብይ መሆኑን ተገነዘብኩ፡፡ ምክንያቱም የደበቅኩትን ሚስጥር ሳይቀር ያውቃልና፡፡[153]

እነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች የነቢዩን ድንቅ ባህሪ ያሳያሉ፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በቁርአን የተጠቀሰው የሞራል ትምህርት ቋሚ ምሳሌ ናቸው፤ ጠላቶቻቸውንና የበደላቸውን ይቅር ብለዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ

---

[152] /ከክርስትናና ከሳብያን እምነት በመቀላቀል የተፈጠረ ሀይማኖት ነው፡፡

[153] ኢብን ሂሻም አልሲራ አልነበዊያህ ቅጽ 2 ገጽ 580 አህመድና ጦበራኒ

ምሳሌዎች የነብዩን ድንቅ ባህሪ ያሳያሉ። በአላህና በኢስላም ላይ ካልሆነ በቀር በእሳቸው ላይ የሚፈፀምን በደል ከቁብ አይቆጥሩትም። ተወዳጁ ባልደረባቸው ኡሳማ (ረ.ዐ) ከከፍተኛ የማህበረሰብ ክፍል የወጣች ሴት በስርቆት ወንጀል በተያዘች ግዜ ይቅርታ እንዲደረግላት ጠየቋቸው። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በንዴት ፊታቸው ተለዋወጠ።

"ልጄ ፋጡማም ሠርቃ ብትያዝ እንኳ እጇን ከመቁረጥ ወደ ኋላ አልልም" ሲሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ተናገሩ"[154]

ይህ ምሳሌ ብቻውን ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ምን ያህል ለፍትህ ቀናኢና ሁሉንም በእኩል አይን ተመልካች እንደነበሩ ያሳያል።

# የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለጋስነት

ኢብን አባስ (ረ.ዐ) ይህን አስተላልፈዋል፦

"የአላህ መልእክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) ደግነታቸው እና ልግስናቸው በረመዳን ይጨምራል። ምንም ነገር ለጠየቃቸው ሰው አሉታዊ መልስ ሰጥተው አያውቁም"[155]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እስካላቸው ድረስ የጠየቃቸውን ሠው ባዶ እጁን አይመልሱትም። የሚሠጡት ነገር ባይኖራቸው እንኳ ጠያቂውን በፈገግታ ያስተናግዱ ነበር።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ከዚህ ሁሉ ቸርነታቸው በኋላም እንኳ ዘወትር፦ ‹‹እኔ አዳይ ብቻ ነ። ሠጪ አላህ ነው›› ሲሉ ይደመጡ ነበር። አንድ ቀን አንድ ሰው ወደ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) መጣ። የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) አንድ ሸለቆ የሚሞሉ ፍየሎች ተመለከተ። ከፍየሎቹ እንዲሰጠው ጠየቀ።

---

154 ቡኻሪና ሙስሊም

155 ቡኃሪ፣ ነሳኢ፣አህመድና ቢን አባስ

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሁሉንም ሠጡት፤ ሰውዬውም ወደ ህዝቦቹ በመመለስ፦ "ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) እጅግ ለጋስ ነው፡፡ ድህነትን ፈፅሞ አይፈራም"[156] ሲል ተናገረ፡፡

በሌላ ታሪክ አንድ ሰው ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ሊጎበኝ መጣ፡፡ እርዳታ እንዲሰጠውም ጠየቀ፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ምንም አልነበራቸውም፡፡ ብድር ፈልጎ እንዲበደርና ብድሩን እሳቸው እንደሚከፍሉለት ቃል ገቡ፡፡

አባታችን ኢብራሂም (ዐ.ሠ) በተመሳሳይ ልግስና ይታወቃሉ፡፡ አንዲት ቀንም ቢሆን ከእንግዳ ውጪ ተመግበው አያውቁም ነበር፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የሞተን ሠው ብድር ይከፍላሉ ወይም ሌሎች እንዲከፍሉለት ያደርጋሉ፡፡ የሟች ብድር ሳይከፈል የጀናዛ ሶላት እንዲሰገድ አይፈቅዱም ነበር፡፡ እንደዚህም ይላሉ፦

"ለጋስ ሰው ለአላህ ቅርብ ነው፤ ለጀነትና ለህዝቦቿም እንዲሁ፡፡ ከጀሀነም እሳት ግን እጅግ የራቀ ነው፡፡ ንፉግ ሰው ግን ከአላህ፣ ከጀነትና ከህዝቦቿ የራቀ ሲሆን ለጀሀነም እሳት ግን የተጠጋ ነው"[157]

በሌላ ሀዲስ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፦ "እውነተኛ አማኝ ፈፅሞ ንፉግና ስርአት አልባ አይሆንም"[158]

## የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ለጋስነት

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ነብዩን (ሠ.ዐ.ወ) ለመምሰል እርስ በራስ ይፎካከሩ ነበር፤ እንደ ምሳሌ ዑመር (ረ.ዐ) ይህን ሀዲስ አስተላልፈዋል፦

---

[156] ሙስሊም፣ አህመድ፣ ቢን ሒባንና ኹዘይማህ

[157] ቲርሚዚና ጦበራኒ

[158] ቲርሚዝ

"አንድ ቀን ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ምፅዋት እንድንሰጥ አዘዙን፡፡ በዛን ወቅት የተወሠነ ብር በእጄ ላይ ነበር፤ ለራሴም፡- ዛሬ አቡበከርን በልግስና መብለጥ አለብኝ፣ ስል ወሰንኩና የንብረቴን ግማሽ ለነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አስረከብኩ፡፡ ነብዩም፡- ‹‹ለቤተሰብህ ምን ያህል አስቀረህ?" ሲሉ ጠየቁኝ፡፡ እኔም "የሰጠሁዎትን ያክል" ስል መለስኩ፡፡ ከዛም አቡበከር (ረ.ዐ) ሙሉ ገንዘባቸውን ይዘው መጡ፡፡ ነብያችንም "አቡበከር ሆይ፣ ለቤተሰቦችህ ምን ተውክላቸው?›› ሲሉ ጠየቁ፡፡ ‹‹አላህንና መልእክተኛውን›› ሲሉ መለሱ -አቡበከር፡፡ ይህን መልስ ከሠማሁ በኋላ ለራሴ ይህን አልኩ፡-

"አቡበከርን (ረ.ዐ) በምንም ጉዳይ ልበልጠው አልችልም"[159]

አቡበከር (ረ.ዐ) እና ኡመር (ረ.ዐ) የዚህችን ምድር ምቾት በመናቅ እና ለጠፊዋ አለም ባለመታለል ጉዳይ ትክክለኛ የረሡል (ሠ.ዐ.ወ) ምትክ ናቸው፡፡ በአኗኗራቸው የቢዘንታይን እና የኢራን መሪዎች እጅግ ተደምመዋል፡፡ ሌሎች የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረቦችም ቢሆኑ የደግነት እና የመልካም ስነ-ምግባር ምሳሌዎች ናቸው፡፡

ለምሳሌ አንድ ቀን አንድ ለማኝ ወደ ዓሊ (ረ.ዐ) ይመጣና እርዳታ ይለምናቸዋል፡፡ አሊ (ረ.ዐ) ለልጆቻቸው ለሀሠን እና ለሁሴን ይህን አሉ፡-

"ወደ እናታችሁ ሂዱና ያለንን ስድስት ዲርሀም አምጡ፡፡ ሀሠን እና ሁሴንም ወደ ቤት በመሄድ ስድስቱን ድርሀም ይዘው መጥተው ለአባታቸው ሰጡ፡፡ አሊ (ረ.ዐ) ለለማኙ ሠጡት፡፡ በሠአቱ ግን ይህ ስድስት ዲርሀም ለዚህ ቤተሰብ እጅግ አስፈላጊ ነበር፡፡

አሊ (ረ.ዐ) ከቤታቸው እንደደረሱ ግመሉን መሸጥ የሚፈልግ ሰው ወደ እሳቸው መጣ፡፡ ይህን ግመል በ40 ዲርሀም እንደሚሸጠውና ገንዘቡን ሌላ ጊዜ እንደሚወስደው ተናግሮ ግመሉን አስሮ ሄደ፡፡ ብዙም ሳይቆይ

---

159 ቲርሚዚ፣አቡዳውድ፣ዳሪሚና ሐኪም

ሌላ ሰው መጣና ይህን ግመል 200 ዲርሀም መግዛት እንደሚፈልግ ተናግሮ ወዲያውኑ ዋጋውን በመክፈል ግመሉን ይዞ ሄደ፡፡

አሊም (ረ.ዐ) ለመጀመሪያው ባለ ግመል 40 ዲርሀሙን በመክፈል የቀረውን ገንዘብ ለፋጡማ (ረ.ዐ) ሠጧትና እንዲህ አሉ፡፡

"ይህ የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ቃል ኪዳን ነው፡፡ ጥሩ ምግባር የሰራ ማንኛውም ሠው የሠራውን 10 እጥፍ ይመነዳል፣ ብለዋል፡፡ 10 ዲርሀም ለቸገረው ሰጠን፡፡ አላህ አስር እጥፉን መልሶ ሰጠን፡፡"

ሁዘይፋ (ረ.ዐ) ባስተላለፉት ሀዲስ ደግሞ፡-

"በየምሩክ ጦርነት ወቅት ጦርነቱ እጅግ ተጋግሎ ዋለ፡፡ ከጦርነቱ በኋላ ቁሸለኛ ሙስሊሞች በሚያቃጥለው አሸዋ በመሞት ላይ በነበሩበት ወቅት የአጎቴ ልጅ የሆነውን ሀሪስ ፍለጋ በየሰዉ መሀል መሹሎክሎክ ጀመርኩ፤ የመጨረሻ እስትንፋሳቸውን በመተንፈስ ላይ ከነበሩ ወታደሮች መሀከልም አገኘሁት፡፡ በደም ተጥለቅልቆ በአይኖቹ እንኳን ማውራት ከማይችልበት ደረጃ ላይ ነበር፡፡ የተሸከምኩትን ከቆዳ የተሰራ ውሀ መያዣ በማሳየት ውሀ ይፈልግ እንደሆነ ጠየቅኩት፤ ከንፈሮቹ ደርቀው ውሃ እንደተጠማ ያስታውቁ ነበር፡፡ በአይኖቹ የህመሙን መጠን ሊነግረኝ እየሞከረ መሰለኝ፡፡ የውሀ መያዣዬን ከፍቼ ውሃ በአፉ ላይ ላንቆረቁርለት ስዘጋጅ ኢክሪማ ከሩቅ ‹‹ውሃ! ውሃ! እባካችሁ ጠብታ ውሃ›› ሲል ጮኸ፡፡ የአጎቴ ልጅ ይህን ድምፅ ሲሰማ ውሀውን ለኢክሪማ እንድወስድለት በአይኖቹ ጠቆመኝ፡፡

የተሰዉ ሠዎችን እየተረማመድኩ አልፌ ኢክርማ ጋር ደረስኩ፡፡ ለኢክሪማ ውሀውን ልሰጠው ስቃረብ አያሽ፡- "ለአምላክ ብላችሁ ጠብታ ውሀ ስጡኝ›› ሲል ጮኸ፡፡ ኢክሪማ ይህን ሲሰማ ለአያሽ ውሀውን እንድወስድለት በእጁ ጠቆመኝ፡፡ ሀሪስ እንዳደረገው ሁሉ እርሱም ላለመጠጣት ወሠነ፡፡ አያሽን ከተሠዉ ሰማዕታት መሀል ፈልጌ ሳገኘው ይህን የመጨረሻ ቃሉን ሠማሁ፡-

ባንተ መንገድ በትክክል አልኖርንምና የሠማዕታትን ደረጃ አትንፈገን፤ ጥፋታችንን ይቅር በለን፡፡››

መስዋዕት ሊሆን ተቃርቦ ነበር፡፡ ውሀውን ባደርስለትም የሚጠጣበት ጊዜ አልነበረውም፡፡ የመጨረሻውን የምስክርነት ቃል ሸሀዳ እያሠማ ነበር፡፡

ውሀውን ለኢክሪማ ለማጠጣት እየሮጥኩ ስመለስ ኢክሪማ ተሠውቷል፤ ወደ ሀሪስ ብመለስ የእሱም ነፍስ ወደ አላህ ተመልሳለች፡፡ አንድ ኮዳ ውሀ ከ3 ሸሂዶች ተርፎ ተመለሠ፡፡››

ሁዘይፋ (ረ.ዐ) በወቅቱ የተሰማውን እንዲህ ሲል ይገልፃል፡- "በህይወቴ ብዙ አጋጣሚዎችን አልፌያለሁ፡፡ እንደዚህኛው ግን በእኔ ላይ ተፅእኖ ያሳደረ አጋጣሚ ፈፅሞ የለም፡፡ እነዚህ ሰማእታት እርስ በርሳቸው የነበራቸውና በተግባርም ያሳዩት እጅግ መዋደድና መተሣሰብ ይደንቃል፡፡ ከኢስላም በቀር ሌላ የሚያስተሳስራቸው ነገር ፈፅሞ የለም፡፡ ይህ ገድላቸው ምንግዜም ከአይምሮዬ የማይወጣ ነገር ሆኖ ቀርቷል፡፡[160]

## የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሀቀኝነት፣ ታማኝነትና ግብረገብነት

የአላህ መልዕክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) እውነትን ከውሸት ለማይለዩ ሠዎች እጅግ ያዝኑ ነበር፡፡ ቀጥተኛውን መንገድ ለማስተማር ያንኳኳቸው በሮች በላያቸው ላይ ተዘግተዋል፡፡ ግና መልካም ባህሪያቸውና ለማያውቁ ሰዎች ማዘናቸውን አላቆሙም፡፡ እንዲህ እንዲሉ በአላህ ታዘዋል፡-

---

160 አል-ሐኪም፣ አል-ሙስተድራክ III 270፣ አል-ጠበራኒ፣ አል-ሙዕጃም፣ አል-ክቢር III259 አል-ሚዝ ተህዚብ፣ አል-ከማል ቅፅ 301፣ ኢብን ሙባረክ፣ አል-ዘሁድ1፡185፣ አል-ቁርጡቢ ተፍሲር XVIII. 28

﴿ قُلْ مَآ أَسْـَٔلُكُمْ عَلَيْهِ مِنْ أَجْرٍ وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلْمُتَكَلِّفِينَ ﴿٨٦﴾ ﴾ ص: ٨٦

በላቸው፡- «በርሱ ላይ ምንም ዋጋ አልጠይቃችሁም፤ እኔም ከተግደርዳሪዎቹ አይደለሁም፡፡» **(ሷድ፡ 86)**

እንደ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ታማኝ አልነበረም፡፡ ገና በልጅነታቸው ነበር ንግድን የተዋወቁት፡፡ በአጎታቸው አቡ ጧሊብ አማካኝነት፡፡ ለሁሉም የህብረተሠብ ክፍል ከመታመናቸው የተነሳ "ሙሀመዱል አሚን" (ሙሐመድ ታማኙ) የሚል ስም አትርፈዋል፡፡

ደሀውም ሀብታሙም በአንድነት ‹‹ታማኙ›› ሲሉ ይጠሯቸው ነበር፡፡ በህብረተሰቡ ዘንድ የተከበረችው ኸዲጃ በሀቀኝነታቸው በመማረክ ለትዳር ጠየቀቻቸው፡፡ ኸዲጃ (ረ.ዐ) ለክፉ ጊዜያት አጋር፣ የስነ ልቦናዊ ድጋፍ ሰጪና አበረታች በመሆን በአስቸጋሪ ጊዜያት ሁሉ ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ጎን ቆማለች፡፡

ነብያችን እጅግ ንፁህ ህይወት እንደኖሩ ጠላቶቻቸው ሳይቀር የመሰከሩት ሀቅ ነው፡፡ በወቅቱ የኢስላም ቀንደኛ ጠላት የነበሩት አይሁዶች ሳይቀሩ በመሀከላቸው አለመስማማት ሲፈጠር የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ዳኝነት ፍለጋ ይሄዱ ነበር፡፡ ረሡለላህ (ሠ.ዐ.ወ) ለክርስቲያኖችና ለአይሁዶችም ፍትሀዊ ነበሩ፡፡ ለሌላው ህዝብ እንዲህ እንደሆኑት ሁሉ፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለአሊ (ረ.ዐ) ስለ ፍትህ ሲመክሩት ይህን ይላሉ፡-

"ሁለቱንም ወገን ሳታዳምጥ በፍፁም እንዳትፈርድ! ትክክለኛ ፍርድ መስጠት የምትችለው የሁለቱንም ወገን ከሠማህ በኋላ ብቻ ነው፡፡"[161]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ወደ መዲና በተሰደዱ ጊዜ በአደራ ከእሳቸው ዘንድ የነበሩ ንብረቶችን በአሊ በኩል እንዲመለሱ አድርገዋል፡፡[162]

---

[161] አህመድ ኢብን ሀንበል አል-ሙሠነድ I 90

## የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አይን አፋርነት

እንደ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረቦች አገላለፅ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) የሰዎችን አይን ከምትሸሽ ልጃገረድ በላይ አይን አፋር ነበሩ፡፡

ጮኸው ተናግረው አያውቁም ነበር፡፡ ሰዎች በአጠገባቸው ሲያልፉ ንግግራቸውን ዝቅ በማድረግ ከፊታቸው ላይ ፈገግታ ይታያል፡፡ ያልተገባ ንግግር በሚሰሙበት ወቅት በተናጋሪው ፊት ምንም አይናገሩም፤ ፊታቸው በራሱ ሁሉን ነገር ያስረዳል፡፡ ጮኸው ስቀውም የማያውቁ ሲሆን ፈገግታ ግን ከፊታቸው አይለይም፡፡ በሀዲስ እንደተዘገበው፡-

"አይንአፋርነት ከእምነት ነው፤ አይን አፋር ሰዎች ጀነትን ያገኛሉ! ሀፍረተ ቢስነት ከቀልብ ድርቀት ይመጣል፡፡ ደረቅ ቀልብ ያላቸው ደግሞ ወደ ጀሀነም ይጓዛሉ፡፡"[163]

በሌላ ሐዲስ እንዲህ ተብሏል፡-

‹‹ኢማንና ትህትና የሚኖሩት በአንድ ላይ ነው፡፡ አንደኛው ሲወገድ ሌላኛው አብሮ ይወገዳል፡፡››[164]

‹‹ስርዓት አልበኝነት ሐፍረትን ያከናንባል፡፡ ትህትና ግን ያስውባል፡፡››[165]

---

162 ኢብን ሂሻም አል-ሲራ አል-ነበዊያ I 482 ኢብን ከሲር አል-ቢዳያህ ወ ኒሀያን II 176

163 ቡኻሪ ኢማን 16፣ ሙስሊም ኢማን 57-59፣ አቡዳውድ ሡና 14፣ ቲርሚዝ ኢማን 7፣ ነሳኢ ኢማን 16፣ ኢብን ማጃህ ዙህድ 17፣ ሙዋጣእ ሁስን አል ኹሉቅ 10፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሥነድ II 56. 147

164 ጦበራኒና በይሐቂ

165 ሙስሊምና አቡ ዳውድ

ትክክለኛ ግብረገብና መረጋጋት ሞትን ለማስታወስ ስለሚረዳ ከዚህች አለም ፍቅር ለመላቀቅ ትልቅ መድህኒት ነው። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለባልደረቦቻቸው ትክክለኛ የሆነ የአላህ ፍቅርና ክብር እንዲኖራቸው ያስተምሩ ነበር። አላህን መውደድ ትእዛዙን ማክበር ማለት፡-

ይህ ፍቅር ለእያንዳንዱ የሠውነት ክፍላችን የተከላከሉ ነገሮችን አለማድረግንና ሞትን ያስታውሳል። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እንዳስተማሩት የዚህች አለም ፍቅር ከልባቸው የሚወጣላቸው ሰዎች ለቀጣዩ አለም የጓጉ ብቻ ናቸው።[166]

## የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ከራስ ወዳድነት የፀዳ ባህሪ

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የሌሎች ህመም ያማቸው ነበር። በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ ህመምና ችግራቸውን ለመፍታትና እነሱን ለስኬት ለማብቃት ይለፉ ነበር። ይህም ባህሪያቸው በቅዱስ ቁርአን እንዲህ ተገልጿል፡-

﴿ لَقَدۡ جَآءَكُمۡ رَسُولٞ مِّنۡ أَنفُسِكُمۡ عَزِيزٌ عَلَيۡهِ مَا عَنِتُّمۡ حَرِيصٌ عَلَيۡكُم بِٱلۡمُؤۡمِنِينَ رَءُوفٞ رَّحِيمٞ ﴾ التوبة: ١٢٨

«ከጎሳችሁ የሆነ. ችግራችሁ በርሱ ላይ ጽኑ የሆነ. በናንተ (እምነት) ላይ □ሚ□□. በምእመናን (ላይ) ሩህሩህ አዛኝ የኾነ መልክተኛ. በእር□□ መጣላችሁ።»(አት-ተውባህ፡ 128)

[166] ቲርሚዝ ሲፋቱል ቂያማ 24፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠነድ I 387፣ አል-ሀኪም፤ አል-ሙስተድራክ IV359፣ ኢብን አቢ ሸይባህ አል ሙሰነፍ VII177፣ አልጦበራኒ አል ሙዕጃም አል-አውሳጥ VII226

በዚህ የቁርዓን አንቀፅ የልእልና ባለቤት የሆነው አላህ (ሡ.ወ) ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) የራሱ መገለጫ በሆኑት ስሞች "ረዑፍ" እና "ረሂም" (ሩህሩህና አዛኝ) ሲል ጠርቷቸዋል፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ዘወትር ለህዝባቸው ስኬት የሚጥሩና የሚጨነቁ ነብይ ነበሩ፡፡ በዚህ ብቻ አያበቁም፤ እያንዳንዱን ግለሰብ ደስተኛ ለማድረግ የቻሉትን ሁሉ ያደርጉ ነበር፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እንደ ሌሎች መሪዎች ለህዝባቸው ጥሩ በመመኘት ብቻ አልቆሙም፤ ይልቁንም በዚህችም ሆነ በቀጣዩ አለም ስኬታማ እንዲሆኑ ህዝባቸውን መርተዋል፡፡ በአንድ ወቅት አንድ ሶሀባ የሚገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ ጥሩ ይሁን መጥፎ እንዴት ማወቅ እንደሚችል ጠይቋቸው እንዲህ ሲሉ መለሱ፡- ‹‹የኢባዳ ዓላማ የመጭውን ዓለም ስኬት ማግኘት ሆኖ እያለ አንተ የዚህችን ዓለም ስኬት ለማግኘት ያዋለው በመጭው ዓለም ምንም ነገር አያገኝም፡፡››[167]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በንግግራቸው፣ በተግባራቸውና በሁለመናቸው ለሰው ልጅ አዛኝና ተቆርቋሪ ነበሩ፡፡ ለእውነተኛ ኃይማኖት ሲሉ ብዙ መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡ የሠው ልጆች ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይገቡ ዘንድ የነበራቸው ምኞትና ጉጉት ወደር አልነበረውም፡፡

አቡጃህል ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) መተናኮሉን ሀምዛ (ረ.ዐ) ሲሰሙ በንዴት አቡጃህልን ከተበቀሉ በኋላ ወደ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በመምጣት፡-

"ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ሆይ፣ ደስ ይበልዎት፤ አቡጃህልን ተበቅዬዋለሁ" በማለት ተናገሩ፡፡ ነብያችንም (ሠ.ዐ.ወ)፡-

---

[167] አህመድ ሀንባል አል-ሙሥነድ V134፣ ኢብን ሂባን አል-ሠሂህ II32፣ አል ሀኪም አል ሙስተድራክ IV 346፣ በይሀቂ ሹአብ አል-ኢማምን ቅፅ 374

"እኔ ከበቀል ጋር ምንም ግንኙነት የለኝም። ኢስላምን ብትቀበል ግን ደስ ይለኛል" አሉት። ሐምዛም የመልሳቸውን ጥበብ ተመልክቶ ኢስላምን ተቀበለ።[168]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለቁሳዊ አለም ተሸንፈውም ሆነ ኀጉተው አያውቁም፤ የበደላቸውንም አንዴም እንኳን ተበቅለው አያውቁም።[169]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሠዎችን ላደረሡት ጥፋት ከሰው ፊት ተናግረው አያውቁም። ስለ ጥፋቱ ሲጠይቁም እንዲህ ብቻ ይሉ ነበር፡-

‹‹ይህን ግድፈት ያየሁት ለምን ይሆን?››[170]

ሰውየውን በቀጥታ፡- ‹‹አጥፍተሐል›› ከማለት ይልቅ፡- ‹‹ይህን ነገር ያየሁት ምን ሆኜ ይሆን?›› በማለት ጥፋቱን ወደርሳቸው አተያይ በማስጠጋት የሰውየውን ስሜት ለመጠበቅና ቀልቡን ላለመስበር ይጥራሉ።

ነብያችን ለባልደረቦቻቸው ልቦች መጨነቅ በንግግርም በተግባርም ይታይ ነበር። ይህንንም ተናግረዋል።

"አማኞች ሆይ! አላህ ይጠብቃችሁ! አላህ እንዲንከባከባችሁ፣ እንዲጠነቀቅላችሁ፣ እንዲያግዛችሁ፣ እንዲመራችሁ፣ በሱ ጥበቃ ስር

---

[168] ኢብን ሂሻም አስ ሲራ፡አልነባዊህ I 292 አል ሀኪም፣ አል-ሙስተድራክ III2113 አልጠበራኒ፣ አል-ሙዕጃም፣ አል-ከቢር II139 ኢብን ከሲር አል-ቢዳያህ ወን-ኒሃያህ

[169] አል ቡኻሪ ሙናቂብ 23፣ ሙስሊም ፋዳኢል 77፣ አቡ ዳውድ አደብ 4፣ ሙዋጣእ ሁስነል ኹሉቅ 2፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠነድ V: 130-223

[170] ቡኻሪ አይማን 3-ኢብን ሂባን አል-ሠሂህ IV534፣ አል ሀኪም አልሙስተድራክ II 515.

እንዲያስተዳድራችሁ፣ ከማንኛውም መጥፎ ነገር እንዲከላከልላችሁ እና በሀይማኖታችሁ ላይ እንዲያጠነክራችሁ ፀሎቴ ነው"[171]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) መልእክቱን የካዱ ሠዎችን ከመጥላት እና ከማንቋሸሽ ይልቅ እጅግ ያዝኑላቸው ነበር፡፡ በማዘን ሳያበቁ በተደጋጋሚ ዱዓ ያደርጉላቸው ነበር፡፡ ለዚህም ይህ የቁርዓን አንቀፅ ተላከላቸው፡፡

﴿ فَلَعَلَّكَ بَٰخِعٞ نَّفۡسَكَ عَلَىٰٓ ءَاثَٰرِهِمۡ إِن لَّمۡ يُؤۡمِنُواْ بِهَٰذَا ٱلۡحَدِيثِ أَسَفًا ٦ ﴾

«በዚህም ንግግር (በቁርኣን) ባያምኑ በፈለጎቻቸው ላይ በቁጭት ነፍስህን አጥፊ ልትሆን ይፈራልሃል፡፡» **(አል-ካህፍ፡ 6)**

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) "ለፈጣሪያቸው ስትል ሁሉንም ፍጡራን ውደድ" የሚል መመሪያ የነበራቸው ሲሆን ባልደረቦቻቸውም ከዚህ አስተምህሮት በመነሳት ለፍጡራን ኢስላምን ለማዳረስ የቻሉትን ሁሉ አድርገዋል፡፡

---

[171] አል-ባዛር አል-ሙሰናድ V395 አል-ጠበራኒ አል-ሙዕጀሞ አል-አውሰጥ IV 208፣ አቡ ኑአይም አል-ኢስበሀኒ ሂልያህ አል-አውሊያ IV 168 አል ባግዳዲ ሙስ ዋዲህ II 147

## ታማኝነታቸውና ውለታ ከፋይነታቸው

ቃልን ማክበር ከጀሀነም መዳኛ መንገዶች አንዱ ሲሆን የነብያትና የመልካም ሰዎች መገለጫ ነው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) በታማኝነታቸው ለጠቅላላው የሰው ዘር ምሳሌ እና አስተማሪ የሚሆኑ ናቸው፡፡ አይሻ (ረ.ዐ) ባስተላለፉት ሀዲስ፡-

"በአንድ ወቅት አንዲት አሮጊት ሴት ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ልትጎበኝ መጣች፡፡ ሞቅ ያለ ጨዋታ ከተጫወቱ በኋላ ሴትየዋ ተነስታ ሄደች፡፡ እኔም ይህን ጠየቅኩ፡-

የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ለዚህች ሴት ወሬ ትኩረት ሰጥተው ሲያዳምጧት ነበር፡፡ ምን እንዳለችዎ ለማወቅ ጓጉቻለሁ፡፡ ማነች?›› እሳቸውም፡- ‹‹ኸዲጃ በህይወት እያለች እየመጣች ትጠይቀን የነበረች ሴት ናት›› አሉኝ፡፡[172]

በሌላ ሀዲስ፡-

ከሁነይን ዘመቻ በኋላ ሰዎች ተሰብስበው ወደ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ዘንድ መጡ፡፡ ለጦር ምርኮኞቻቸው ነፃነትን ሊጠይቁ ነበር አመጣጣቸው፡፡

"ሙሀመድ ሆይ! የጡት እናትህና እህትህ ከእኛ ጎሳ ናቸው›› ሲሉም ተናገሩ፡፡ ስለዚህ ለጥቢ እናታቸው ውለታ ሲሉ በዛች ቀን በሺዎች የሚቆጠሩ የጦር ምርኮኞች ያለምንም ችግር ነፃ ለቀቁ፡፡[173]

ነብያችን በጠና በታመሙበት የመጨረሻ ህመማቸው ጊዜ ወደ መስጂድ መጡ፡፡ ይህንንም ተናገሩ፡-

---

[172] አል-ሀኪም- አል-ሙስተድራክ I 62 አል-ቂአዲ ሙሠነድ አል-ሺሀብ II አል-በይሐቂ VI 517

[173] ቡኻሪ አል-ጦሪቅ፣ አል ሳጊር I5 አል-ጦበራኒ፣ አል-ሙዕጃም

"እናንተ ስደተኖች ሆይ! (ከመካ ተሰደው የመጡትን) ረዳቶቹን (የመዲና ሰዎችን) በጥሩ ሁኔታ ያዝዋቸው። የህዝብ ቁጥር እየጨመረ ቢሆንም እነሱ ባሉበት አሉ። የተቸገርን ጊዜ መጠለያ ሆነውናል፤ ለመልካሞች መልካም ሁኑ፤ የሚያጠፉትን ይቅር በሉ።››

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የመዲና ሰዎችን ውለታ አለመርሳታቸው ለሁላችንም ምሳሌ የሚሆን ተግባር ነው።

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ታማኝነትና ውለታ ከፋይነት ተዘርዝሮ አያልቅም። ለምሳሌ ከስደት በፊት ጠላቶቻቸው እንዴት እንደሚገድሏቸው ሲያሴሩ እሳቸው ግን በአደራ የተቀመጡ ንብረቶቻቸውን እንዴት እንደሚመልሱላቸው ነበር የሚጨነቁት።

በኡሁድ ጦርነት ወቅት ሁለት የቅርብ ወዳጆች የነበሩ ባልደረቦቻቸው በአንድ ጉድጓድ ተቀበሩ። ነብያችንም (ሠ.ዐ.ወ) ይህን አሉ፡-

"ይህ በዚህች አለም ጥሩ የመሆናቸው ውጤት ነው።"[174]

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባልደረቦች እርስ በርስ ጥልቅ ፍቅር ነበራቸው። ይህም ፍቅርን ከትክክለኛው አፍቃሪ ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የመማራቸው ውጤት ነው። ኡስማን (ረ.ዐ) ወደ መካ ተጓዙ። ከዛም ከመካ ጣኦታውያን ለሀጅ ስነስርአት ብቻ ሙስሊሞች ወደ መካ እንዲመጡ ፍቃድ ጠየቁ። የመካ ሙሽሪኮች ግን አንስማማም በማለት እምቢታቸውን ገለፁ። ኡስማንን ግን ሐጅ እንዲያደርጉ ፈቀዱላቸው።

ኡስማን (ረ.ዐ) ግን፡- ‹‹ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ሐጅ ካላደረጉ አላደርግም፤ ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ከተካዱበት ቦታ ላይ መቆየት አልችልም›› አሉ። ኡስማን (ረ.ዐ) ይህን በሚያደርጉበት ወቅት ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የባልደረቦቻቸውን

---

[174] ኢብን አቢ ሸይባህ አል-ሙሠነድ VII 367 አህመድ ሀንባል አል-ሙሠነድ ቅፅ 299 ኢብን ሂሻም አል-ሲራ አል-ነባዊያ II 98.

በይዓ እየተቀበሉ ነበር። ምክንያቱም ዑስማንን ጣኦታያያን ገድለዋቸዋል ብለው ስለገመቱ። የሁሉንም ባልደረቦች እጅ በማደራረብ ይህን አሉ።

"ጌታዬ ይህ በይዓ ለኡስማን ነው። በእርግጥም እሱ የአንተ ነብይ አገልጋይ ነው።››[175]

አማኝ መሆን ማለት ነብዩን (ሠ.ዐ.ወ) ለመምሰል መሞከር ነው። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሁለገብ ተምሳሌት ናቸውና።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ብዙ ተአምራቶችን አሳይተዋል። የሰው ልጆች የስነ ምግባር አስተማሪም ናቸው። በማህበረሰቡ ውስጥ ክብር ያለው ስልጡን ዜጋን አፍርተዋል።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በህይወታችን ሚዛናዊ እንድንሆን አስተምረውናል። የዚህችን እና የቀጣዩን አለም ያስማማ መሀከለኛ ጎዳና አሳይተውናል።

ታሪክን ብናጠና ሠዎች በተሰማሩበት (በአንድ ዘርፍ) ስኬታማ ሊሆኑ ይችላሉ። ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ግን ሁለ ገብ የነበሩና በሁሉም ዘርፍ የተሳካላቸው ምርጥ ሰው ነበሩ። ነብዩ የተናገሯቸው ተከታዮቹ ድንቅ የሞራል መርሆዎች የርሳቸውን እጅግ የመጠቀ ሞራላዊና ስነምግባራዊ ሕየወት ለማየት የሚረዱ ናሙናዎች ናቸው። እንዲህ ይላሉ፡-

175 አህመድ ሀንባል አል-ሙሠነድ IV 324፣ ኢብን አብድልባር፣ አልቲርሚዝ XII148፣ ኢብን ሂሻም አል ሲራ አል ነባዊ II 315፣ ኢብኑል ከሲር አል-ቢድያህ -ኒሃያህ II 169.

## ጌታዬ ዘጠኝ ነገሮችን አዘዘኝ

1. አላህን ብቻህንም ሆነ ከሠዎች ጋር ስትሆን ፍራ
2. ደስተኛም ሆነክ ስትናደድ ፍትሀዊ ሁን
3. ደሀም ሆንክ ሀብታም በቁጥብነት ኑር
4. እነሡ ላንተ መልካም ባይሆኑም እንኳን ለዘመዶችህ መልካም ሁን
5. ለጠየቀህ ስጥ
6. ለበደለህ ይቅርታ አድርግ
7. ዝምታህ ማስተንተን ይሁን
8. ንግግርህም አላህን ማስታወስ ይሁን
9. ስትመለከት ትምህርት ውሰድ[176]

ከነብያችን (ሡ.ዐ.ወ) ሠይፍ ላይ ይህ ፅሁፍ ይገኛል፡-

"የበደለህን ይቅርታ አድርግለት፤ ዘመዶችህን እርዳ፤ ላንተ ግድ ባይኖራቸውም እንኳን፡፡ መጥፎ ላደረገብህ በጥሩ መልስ፤ ከራስህ ፍላጎት ጋር የሚጋጭ ቢሆንም እንኳ እውነቱን ብቻ ተናገር፡፡››[177]

ሁዘይፋ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፡፡

"ማናችሁም ብትሆኑ በድርጊታችሁ የሌሎች ጥገኛና ተለጣፊ መሆን የለባችሁም፤ አንዳንድ ሠዎች ለሠዎች ያለኝ አቀራረብ በነሱ አቀራረብ ላይ ይወሰናል፡፡ ጥሩ ከሆኑልኝ ጥሩ እሆናለሁ፡፡ መጥፎ ከሆኑብኝ

---

[176] ኒሳኢ ሳህው 62፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠነድ IV 148፣ ኢብን አቢ ሸይባህ አል ሙሠነፍ VI 45 አልጦበራኒ አል-ሙዕጃም አል-አውሳጥ V328.

[177] አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠነድ IV 148 አል ሀኪም አል-ሙስተድራክ II 563 አል-ጦበራኒ፣ አል ሙጃም አል-ከቢር XVII 269 አል-በይሀቂ አል-ሡና አል-ኩብራ X235

ደግሞ መጥፎ እሆናለሁ፤ይላሉ። ፊፅሞ እንዲህ አይነት ሰዎች አትሁኑ። ይልቅም ይኼን የህይወት መመሪያችሁ አድርጉ፡-

"ጥሩ ሲሆኑልህ ጥሩ መሆን መጥፎ ሲሆኑ ደግሞ እነሱን አለመምሰል።››[178]

በሌላ ዘገባም እንዲህ ብለዋል፡-

## አላህ 3 ነገሮችን ይጠላል

1. ሀሜት
2. አባካኝነት
3. አላግባብ መጠየቅን[179]

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በሌላ ምክራቸው፡-

"በወንድማችሁ ችግር አትሳቁ፤ ምናልባትም አላህ እሱን ከችግሩ አትርፎ እናንተን በሱ ቦታ ሊያስቀምጣችሁ ይችላልና"[180]

የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት ያጠና ማንኛውም ሰው ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ምንጊዜም የፍቅርና የእዝነት ነብይ እንደነበሩ ማወቅ አያቅተውም። ማንንም በድለውም ሆነ አውግዘው የማያውቁ ሲሆን ጭቆናን አምርረው ተቃውመዋል፤ መቃወም ብቻ ሳይሆን ጭቆናና ግፍን ለማስቆም ብዙ ከፍለዋል።

ለምሳሌ፡- በጣኢፍ በድንጋይ በተደበደቡበት ወቅት አላህን የጠየቁት ብቸኛው ነገር እኚህን ህዝቦች እንዲምራቸው ነበር።[181]

---

[178] ቲርሚዝ ቢር 62

[179] ቡኻሪ ዘካ 53፣ ሙስሊም አቂዳ 12፡13፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠነድ II 327፡ 360፣ ኢብን ኹዘይማ አል-ሠሂህ I:10

[180] ቲርሚዝ ቂያማ 54፣ አል ጦበራኒ- አል-ሙዕጃም አል አውሳጥ IV 111፣ አል ቁዳይ ሙሠነድ አል ሀቢብ II 77፣ አል በይሀቅ ሹአብ አል-ኢማን V315.

ከ10 አመታት በኋላ መካ ሲገቡ ያደረጉት ብቸኛው ነገር ትዕግስት፣ መተናነስና ምህረት ነው። የካዕባ ቁልፍ ለረጅም ጊዜ በእጁ የቆየውን ኡስማን ኢብን ጦልሀ ቁልፉን አልተቀበሉትም ነበር። በዛን ቀን ይህ ተናገሩ፡-

"ዛሬ የታማኝነትና የደግነት ቀን ነው"[182]

አልጋ ወራሽ ሳያዘጋጁ የወረዱ ብቸኛው ንጉስ ነብዩ ናቸው። ይህንንም ተናገረዋል፡-

"እኛ ነብዮች የሚወረስ ንብረት አንተውም። ትተነው ያለፍነው ማንኛውም ነገር ለሙስሊሞች ምፅዋት ነው።"[183]

ጥለውልን ያለፉት ብቸኛው ውርስ መልካም ባህሪያቸው እና ፍፁም ምሳሌነታቸው ነው።

---

[181] ቡኻሪ ባድ አል-ኽላቅ 7፣ ሙስሊም ጂሀድ 111፣ ነሳኢ አል-ሡና አል-ኩብራ IV 405፣ ኢብን ሂባን አል-ሠሂህ XIV 516.

[182] ኢብን ሂሻም አል-ሲራ አል-ነባዊያ II 412 ኢብን ኻጢር አል-ቢዳያህ ዋን-ኒሃያህ II 300.

[183] ቡኻሪ ኹሙስ 1፣ ሙስሊም ጂሀድ 54፣ አቡ ዳውድ ኢማራህ 19፣ ቲርሚዚ ሲየር 44፣ ነሳኢ ፋይእ 9፣ ሙዋጣእ ቀለም 27፣ አህመድ ኢብን ሀንባል ሙሰነዳ I 4

# ማጠቃለያ

ከሁሉም ፍጡራን ይልቅ አላህ ለሠው ልጅ የራሱን ባህሪዎች አጋርቶታል፤ ዘልአለማዊነት ሲቀር፤ የሰው ልጅ መልካም የማድረግ አቅምም ሆነ ጥፋትን የመከተል ምርጫ ተሠጥቶታል። በመሆኑም የሀይማኖት አላማው እንሰሳዊ የሆነውን የሠው ልጅ ባህሪ ገርቶ ጥሩ ባህሪዎችን ማጎናፀፍ ነው። ይህን ሂደት የተዋጣ ለማድረግ ደግሞ ሁሉም የሠው ዘር ሊመለከተውና ሊከተለው የሚችል ምርጥ ሠው ወይንም ተምሳሌት ያስፈልጋል። ለዚህም ሲባል አላህ (ሡ.ወ) ነብያችንን (ሠ.0.ወ) መርጦ ላከልን።

﴿ وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن رَّسُولٍ إِلَّا لِيُطَاعَ بِإِذۡنِ ٱللَّهِۚ ﴿٦٤﴾ ﴾ النساء: ٦٤

«ማንንም መልክተኛ በአላህ ፈቃድ ሊታዘዙት□እንጅ አልላክንም።»
**(አን-ኒሳእ፡ 64)**

﴿ لَّقَدۡ كَانَ لَكُمۡ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ لِّمَن كَانَ يَرۡجُواْ ٱللَّهَ وَٱلۡيَوۡمَ ٱلۡأٓخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرٗا ﴿٢١﴾ ﴾ الأحزاب: ٢١

«ከናንተ፥ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለኾነ ሰው፥ አላህንም በብዙ ለሚያወሳ፥ በአላህ መልዕክተኛ መልካም መከተል አላችሁ፤» **(አል-አሕዛብ፡ 21)**

የእያንዳንዷ ደቂቃ ህይወታቸው የተዘገበና ጥቃቅን ነገሮቻቸው ሳይቀር ተፅፈው የተላለፉ ብቸኛው ነብይ፣ ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.0.ወ) ናቸው። ድርጊታቸው፤ ቃላቶቻቸው፣ስሜታቸው አንዷት ሳትቀር ለሰው ልጅ በምሳሌነት ታገለግል ዘንድ ተቀምጣለች።

﴿ وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٖ ﴿٤﴾ ﴾ القلم: ٤

«አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ።»**(አል-ቀለም፡ 4)**

አላህ (ሡ.ወ) ነብያችንን (ሠ.0.ወ) ለሁሉም ሰዎች ምሳሌ እንዲሆኑ ስለ ፈለገ ሁሉንም የህይወት ምእራፍ አሳለፋቸው። ምንም ከሌለው ወላጅ

አልባ ህፃንነት እስከ ነብይነት እና ሀገር አስተዳዳሪነት፡፡ አላህ (ሡ.ወ) ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት እንድንረዳ የፈለገው በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ ያለ ሠው ከነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት መማርና እሳቸውን ተምሳሌት ማድረግ እንደሚችል ነው፡፡

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ባላቸው የላቀ ስብእና የተነሳ የመጨረሻው ነብይ ሆነው ተመረጡ፡፡ አባታችን ኢብራሂም (ዐ.ሠ)፣ የመጨረሻው ነብይ (ነብያችን ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ)) ከሳቸው ዝርያ እንዲሆኑ አላህን ለመኑት፤ ነብዩላህ ኢሳም (ዐ.ሠ) ቢሆኑ ይህንኑ ለመኑ፡፡ የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እናት አሚና ረሡልን (ሠ.ዐ.ወ) ከመውለዷ በፊት በህልሟ ተመለከተቻቸው፤ በትክክል በአላህ መንገድ ነበር የተጓዙት፡፡ የምርጥ ባህሪ ባለቤትና ተወዳዳሪ የሌላቸው ተምሳሌት፡፡

የዚህችንና የቀጣይዋን አለም ደስታ ማግኘት የሚሻ ሰው የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ህይወት መከተሉ ምንም አማራጭ የሌለው ነገር ነው፡፡

﴿ قُلۡ إِن كُنتُمۡ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِي يُحۡبِبۡكُمُ ٱللَّهُ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٣١ ﴾ آل عمران: ٣١

‹‹በላቸው:- «አላህን የምትወዱ እንደ ኾናችሁ. ተከተሉኝ፤ አላህ ይወዳችኋልና፤ ኀጢኣቶቻችሁንም ለናንተ ይምራልና፤ አላህም መሓሪ አዛኝ ነው፡፡» **(ኣሊ-ዒምራን፡ 31)**

በዚህ የቁርአን አንቀፅ መሠረት ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) መከተል የሚቻላቸው አላህን የወደዱ እና ለዚህም ለቀጣይም ህይወታቸው ያሰቡ ናቸው፡፡

የረሡልን (ሠ.ዐ.ወ) መንገድ ለመከተል የመጀመሪያ እርምጃ የአላህን (ሱ.ወ) ፍቅር መረዳት ነው፡፡ ከዛም ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የነበራቸውን ግብረገብና መልካም ፀባይ በራስ ላይ ለማምጣት መሞከር፡፡

ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) የተከተሉና እሳቸውን የመሰሉ ከመላእክትም በላይ የላቀ ደረጃን ይሸለማሉ። ነብዩን የተከተለ ቤተሰብ የጀነት ቤተሰብ ይሆናል። የእርሳቸውን ፈለግ የተከተለ ማህበረሰብ የተሳካለትና ደስተኛ ማህበረሰብ ይሆናል።

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ሠብአዊ ፍጡራንን የመምራት ሀላፊነት ተሰጥቷቸው ነበር። በእሳቸው አስተምህሮት ግብረገብና መልካም ባህሪ እውቅና ሲሰጠው አፀያፊና ነውረኛ ምግባሮች ተወገዱ፤ ጨካኞች በቃችሁ ሲባሉ የተጨቆኑት ነፃ ወጡ። አማኞች እንዴት የአላህ ባሪያ ብቻ እንደሚሆኑ ተማሩ። የሀበሻው ንጉስ ነጃሺ ቃላት ይህን ይመሰክራል፡-

"ሙሀመድ (ሠ.ዐ.ወ) የአላህ መልእክተኛ መሆኑን እመሠክራለሁ፤ እሱ በእየሱስ ይመጣል ተብሎ የተመሰከረለት ነብይ ነው። አሁን ህዝቤ ላይ ያለብኝ ሃላፊነት ባይኖርብኝ ኖሮ እሡ ዘንድ ሄጄ ጫማውን በተሸከምኩ ነበር"[184]

ሠዎች የኢስላምን የሁለት ዓለም ደስታ ሰጪነት በተመለከቱ ጊዜ የወንዝ ውሀ ወደ ባህር የሚቸኩለውን ያህል ወደ እሳቸው ተጣደፉ። ይህንንም አላህ (ሡ.ወ) በቅዱስ ቁርአን ሲገልፅልን፡-

﴿إِذَا جَآءَ نَصۡرُ ٱللَّهِ وَٱلۡفَتۡحُ ١ وَرَأَيۡتَ ٱلنَّاسَ يَدۡخُلُونَ فِي دِينِ ٱللَّهِ أَفۡوَاجٗا ٢ فَسَبِّحۡ بِحَمۡدِ رَبِّكَ وَٱسۡتَغۡفِرۡهُۚ إِنَّهُۥ كَانَ تَوَّابَۢا ٣﴾ النصر: ١ - ٣

‹‹የአላህ እርዳታና (መካን) መክፈት በመጣ ጊዜ፤ ሰዎችንም ጭፍሮች እየኾኑ፤ በአላህ ሃይማኖት ውስጥ ሲገቡ ባየህ ጊዜ፤ ጌታህን ከማመስገን ጋር አጥራው፤ ምሕረትንም ለምነው፤ እርሱ ጸጸትን በጣም ተቀባይ ነውና።››**(አን-ነስር፡ 1-3)**

---

[184] አቡ ዳውድ ጃናይዝ 62፣ አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠነድ I 46፣ አቡ ኡስማን አል-ኮራሲኒ ኪታብ አል-ሡና II 228.

ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) የተከተሉ የተረጋጋና ስኬታማ ህይወትን መርተዋል፤ ይመራሉም፤ ምሳሌያቸውም በጫካ መሀል እንደሚበቅል ውብ ፅጌረዳ ነው፡፡ በመጪው አለም የሚያገኙት ደስታ ደግሞ ከዚህ እጅግ እጥፍና ድርብ ነው፡፡ በፍርዱ ቀንም የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ጥብቅናን ያገኛሉ፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) በሀዲሳቸወ ሲያብራሩ፡-

"ከሠው ልጆች ለመቀስቀስ የመጀመሪያው እኔ ነኝ፤ ሠዎች መናገር ሲቸግራቸውና ተስፋ ሲጨልምባቸው ጥብቅና እቆምላቸዋለሁ፡፡ አላህን ለማናገር የተባረክኩ ሰው እኔ ነኝ፡፡ ይሄን የምላችሁ በራሴ ለመኩራራት አይደለም፡፡[185]

የእዝነቱ ነብይ የፍርዱ ቀን የአጥፊዎች ጠበቃ ሆነው ይቆማሉ፡፡ አላህም ጥብቅናቸውን ይቀበላቸዋል፡፡ በሌላ ሐዲስ ነብዩ እንዲህ ብለዋል፡-

“የፍርዱ ቀን ሠዎች ከመደናገጣቸው የተነሳ ወደ አደም (ዐ.ሠ) በመሄድ ጥብቅና እንዲቆምላቸው ይጠይቃሉ፡፡

አደምም፡- "እኔ ጥብቅና ልቆምላችሁ አልችልም፡፡ የአላህ የቅርብ ወዳጅ ወደሆነው ወደ ኢብራሂም ሂዱ›› ይሏቸዋል፡፡ ኢብራሂምን (ዐ.ሠ) ይጠይቃሉ፤ እርሳቸውም " እኔ ጥብቅና መቆም አልችልም ወደ ሙሳ (ዐ.ሠ) ሂዱ፡፡ እሱ የአላህ ቃል ነውና›› ይሏቸዋል፡፡ ሠዎችም ወደ ሙሳ ሄደው ጥብቅናውን ሲጠይቁ፡- "እኔ ጥብቅና መቆም አልችልም፡፡ ወደ ኢሳ ብትሄዱ ይሻላል፡፡ እርሱ የአላህ ቃልና እስትንፋስ ተሰኝቷልና›› ይላቸዋል፡፡ ወደ ኢሳ በመሄድ አማላጅነቱን ሲጠይቁ፡- ‹‹እኔ ለዚህ ተግባር በቂ አይደለሁም፡፡ እስኪ ወደ ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ሂዱ፡፡ ይላቸዋል፡፡

---

[185] ቲርሚዝ-ማናቂብ 1 ዳሪሚ ሙቀዲማህ 8፣ አህመድ ሀንባል አል-ሙሠነድ I 281፣ አል-ሀኪም አል-ሙስተድራክ I 83፣ ኢብን ሂባን አል-ሠሂህ XIV 398.

ከዛም ወደ እኔ ይመጣሉ። እኔም ‹‹ጥብቅና የመቆም ፍቃዱ አለኝ›› እልና ወደ ጌታዬ እጠጋለሁ። አሁን የማላውቀውን አላህን የማወደሻ ቃላት ተጠቅሜ አላህን አወድሳለሁ። ሱጁድም እወርድለታለሁ። ከዛም አላህ (ሡ.ወ) እንዲህ ይለኛል።

"ሙሀመድ ሆይ! ቀና ብለህ ተናገር። ንግግርህ ይደመጣል፤ ጠይቀኝ ፍላጎትህ ይሟላል፤ ጥብቅናህም ተቀባይነት አግኝቷል።"

ከዛም እኔ ይህን እናገራለሁ፦

"ጌታዬ ሆይ ህዝቦቼን! ህዝቦቼን!"

የልዕልናው ባለቤት አላህም ይህን ይላል፦

"ሙሐመድ ሆይ! ሂድና ጉልህ እምነት ያላቸውን አውጣ" የተባልኩትን አደርጋለሁ። ተመልሼ፣ በተመሳሳይ ቃል ህዝቦቼን ስል እጠይቃለሁ።

አላህም (ሱ.ወ)

"የአቶም (የሠናፍጭ) ፍሬ ያህል እምነት ያላቸውን አውጣ" ሲል ፍቃድ ይሠጠኛል። የተፈቀደልኝን አደርግና ጌታዬን ማወደስ እቀጥላለሁ።

ጌታዬም "ሙሀመድ ሆይ! ቀና በልና ተናገር። ንግግርህ ይደመጣል። መሻትህ ይፈፀማል። ጥብቅናህም ተቀባይነት ያገኛል" ይለኛል።

እኔም "ህዝቦቼን ህዝቦቼን" እላለሁ።

ጌታዬም "ከሠናፍጭ ፍሬ የቀለለ እምነት ያላቸውንም ቢሆን አውጣ" ይለኛል። የተባልኩትን አደርግና በድጋሚ ጌታዬን ማወደስ እቀጥላለሁ።

አላህም (ሡ.ወ) "ሙሀመድ ሆይ! ቀና በል። ንግግርህ ይደመጣል። መሻትህ ይፈፀማል። ጥብቅናህም ተቀባይነት ያገኛል›› ይለኛል።

እኔም ‹‹ጌታዬ ሆይ! "ከአላህ በቀር አምላክ የለም" ሲሉ የመሠከሩትን ሁሉ አትርፍልኝ" እላለሁ።

“በሀይሌ በስልጣኔና በልእልናዬ ይሁንብኝ "ከአላህ በቀር አምላክ የለም" ያሉትን” ከእሳት አድንልሐለሁ›› ይለኛል፡፡[186]

ይህን ቅድስና ለመጎናፀፍ ከእንሰሳዊ ባህሪ መራቅና የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ባህሪ ከራስ ጋር ማስተሳሰር ይጠይቃል፡፡

አንድ ሰው ነበር፡፡ ሙስሊም ቢሆንም የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ተምሳሌት በልቡ አላኖረም፤ አንድ ቀን ነብያችንን በህልሙ ተመለከታቸው፡፡ እሳቸው ግን ምንም የፍቅር ምላሽ ሳያሳዩት ቀሩ፤ በጣም በመበሳጨት ይህን ጠየቀ፡-

"የአላህ መልእክተኛ (ሠ.ዐ.ወ) ሆይ በእኔ ደስተኛ አይደሉምን?"

"አይደለሁም" ሲሉ መለሱለት

ለምን? ሲል ጠየቀም፡፡

"ምክንያቱም አላውቅህም" አሉት፡፡

"ይሄማ ሊሆን አይችልም፡፡ የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኔኮ ከህዝቦችዎ ነኝ፡፡ አዋቂዎች እርሶ ህዝቦችዎን ሁሉ እናት ልጇን የምታውቀውን ያህል ያውቃሉ ሲሉ ሠምቻለሁ"

"ይህ እውነት ነው፡፡ ግን በአንተ ላይ ምንም የእኔን ፈለጎች (ሡና) አላይም፡፡ ምንም አይነት ውዳሴ (ሠለዋት) ከአንተ አልደረሰኝም፡፡ እኔ የማውቀውና የምለየው የእኔን ሱና የተገበረን ነው፡፡"

ሠውዬው በታላቅ ድንጋጤ ከእንቅልፉ ተነሳ፡፡ ከሀጢያቱም ተመለሰ፡፡ የነብያችንን ፈለግ (ሡና)ም መከተል ጀመረ፤ በአገኘውም አጋጣሚ ሁሉ ሠለዋት ማድረስን ተያያዘው፡፡ ከቆይታ በኋላ በድጋሚ ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) በህልሙ ተመለከተ፡፡ ነብያችንም (ሠ.ዐ.ወ) ይህን አሉት፡-

---

[186] ቡኻሪ ተውሂድ 36፣ ሙስሊም ኢማን 322፣ ቲርሚዢ ቂያማ 11

"አሁን በደምብ አውቅሀለሁ። ጥብቅናም እቆምልሀለሁ።››

ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እጅግ ውብና የላቀ ስብእና የነበራቸው ፍጡር ናቸው፤ ለሰብአዊነት ታግለዋል፤ ተከራክረዋል፤ ብቸኛውና ትክክለኛው መሪያችን እና አስተማሪያችን ናቸው። ቀልቦቻቸው በደረቁና በሞቱ ሰዎች ላይ ሳይቀር ፍቅርን ዘርተዋል፤ አለምልመዋል፤ ቅዱሱን መፅሀፍና እውቀትን ሠጥተው መሀይምነትን አስወግደውልናል። ለህዝባቸው ፍቅር አልቅሰዋል። እኛም እሳቸውን ከምንም ነገር አብልጠን መውደድ እንዳለብን ታዘናል።

"ማንም ሠው ፍፁም እምነት አይኖረውም፣ እኔን ከቤተሰቦቹ፣ ከልጆቹና ከማንኛውም ሰው አብልጦ እስካልወደደኝ ድረስ።"[187]

ይህ ሀዲስ የተሟላ እምነት እንዲኖረን ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) በሙሉ ልብ መውደድ እንዳለብን ያስጠነቅቀናል። ከዚህ ፍቅር ልባቸው የተገለለ ሠዎች ከመንፈሳዊ ምጥቀትና አዋቂነት የወጡ ናቸው። የአላህ ፍቅር በውስጣችን ማደግ የሚችለው በረሡል (ሠ.ዐ.ወ) ፍቅር ኮትኩተን ስናሳድገው ብቻ ነው።

የነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ፍቅር በውስጡ ያለና የሌለ ልብ ሲወዳደሩ ምሳሌያቸው እንደ ወርቅ እና ድንጋይ ናቸው። ከፀሀይ ብርሀን ተቀብላ የምታንፀባረቀው ጨረቃ የፀሀይ መኖር አመላካች ናት፤ ልክ እንደዚሁ በምድራችን ያሉ መልካም ሰዎች የነብያችን ማሳያ ነፀብራቆች ናቸው። እነዚህን ቃላት ከልቡ ያለ ሰው ነፍሱ በመንፈሳዊነት ታንፀባርቃለች።

"አሽሀዱ አንላ ኢላሀ ኢለላህ ወአሽሀዱ አነ ሙሀመደን አብዱሁ ወረሡሉ።"

---

[187] ቡኻሪ ኢማን 8፣ ሙስሊም ኢማን 70፣ ነሳኢ ኢማን 19.

"ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሠክራለሁ። ሙሐመድም የአላህ መልእክተኛና ባሪያ መሆናቸውን እመሰክራለሁ።"

አንዳንዴ ለነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ያለን ፍቅር እጅግ ከፍ ይልና ለመግለፅ የሚያስቸግር የእምነት ጥፍጥና ይሰጠናል።

የሀበሻው ቢላል (ረ.ዐ) ታሪክ ትልቅ መማሪያ ነው። ቢላል ማንም የሚረዳው የሌለው ብቸኛ ነበር። ችግሩን የሚካፈለው ጓደኛም አልነበረውም። አንድ ተራ ባሪያ ብቻ ነበር። በድንገት ግን እምነት አገኘ፤ እምነቱን ለመጠበቅ ያደረገው ተጋድሎ ለቀጣዩ ትውልድ ምሳሌ አደረገው።

ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ከማግኘቱም በላይ በፍቅራቸው ልቡ ተሞላች። ራሱን የነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) አካል አደረገ፤ ነገር ግን ከእምነት እጅግ የራቀው አሳዳሪው በእዛ እንደ እሳት በሚለበልብ አሸዋ ላይ አስተኝቶ አሰቃየው፤ ገረፈው፤ ሰውነቱ ደማ፤ ተለበለበ፤ በዙሪያው ያሉ መሀይማን ተሳለቁ፤ ይህንንም አሉ፦

"አንተ ቆሻሻ ባሪያ! ወደኛ መንገድ ተመለስ እና እራስህን አድን"

ቢላል ግን እንደቆሰለ አንበሳ በቁጣና በጀግንነት፦ ‹‹አላህ አንድ ነው›› ሲል ደጋግሞ መሰከረ። ይህ ፅናቱ ያናደዳቸው መሀይማን ስቃዩን አበረቱበት። ቢሆንም አላረካቸውም። ስለዚህም በአንገቱ ዙሪያ ገመድ አጥልቀው ይጎትቱት ያዙ። ቢላል ግን ከዚህ ሁሉ ስቃይ በነብያችን ፍቅር ተጠለለ። ስጋው እየተሰቃየ ቢሆንም ልቡ በታላቅ ደስታ ላይ ነበረች። ይህ ለነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) የነበረው ፍቅር በነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ልብ ውስጥ አነገሰው። ከባርነት ወደ መጀመሪያው ሙአዚንነት ተሸጋገረ።

ቢላል ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) ከመውደዱ የተነሳ በመጨረሻው እስትንፋሱ ይህን እያለ ነበር፡፡ "ደስተኛ ሁኑ! ደስተኛ ሁኑ! ወደ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) እየተመለስኩ ነው"[188]

ከሀዲስ እንደምንማረው "ሰው የሚሆነው (የሚቀሰቀሰው) ከሚወደው ጋር ነው፡፡"[189]

ወደ ዘልአለማዊነት በምናደርገው ጉዞ ልንከተለው የሚገባው መርህ በቀጣዩ የቁርአን አንቀፅ ተመልክቷል፡-

﴿وَمَآ ءَاتَىٰكُمُ ٱلرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَىٰكُمْ عَنْهُ فَٱنتَهُوا۟ ۚ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ ۖ إِنَّ ٱللَّهَ شَدِيدُ ٱلْعِقَابِ ﴿٧﴾﴾ الحشر: ٧

‹‹መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት፡፡ ከርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ፡፡ አላህንም ፍሩ፤ አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና፡፡›› **(አል-ሐሽር፡ 7)**

"አላህ ሆይ ይህችን ትንሽዬ ስራችንን ለምህረትህ ማግኛ ሰበብ አድርግልን፡፡ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለሰው ዘር ባመጡት እምነት የተባረክን አድርገን፡፡ ጌታችን ሆይ! በመጨረሻው ነብይህ (ሠ.ዐ.ወ) ፍቅር የተጠመቁ አድርገን፡፡ የእሳቸውን ትድግና ከሚያገኙት አድርገን፡፡

ይህች አነስተኛ መፅሐፍ ለአለማት የተላኩትን እና የፍጡራን ቁንጮ የሆኑትን ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) ለማስተዋወቅ ፈፅሞ እንደማትበቃ እናውቃለን፡፡ በዚህች ቅንጣት ስራ ስለ ነብያችን (ሠ.ዐ.ወ) አስተዋውቀናል ማለት በራሱ ያሳፍረናል፡፡ የእኛ ቃላት የሚያሳዩት ምን ያህል ነብያችንን (ሰ.ዐ.ወ) ለመግለፅ ደካሞች መሆናችንን ብቻ ነው፡፡ አላማችን በጥቂቱም ቢሆን ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) የማወደስና የማስታወስ

---

188 ኢብን አብዱልበር አል-አስቲአብ 1፡78

189 ቡኻሪ-አዳብ 96 ሙስሊም ብር 165፣ ቲርሚዝ ዙህድ 50፣ ዲሪሚ ሪቅድ 7፣አህመድ ኢብን ሀንባል አል-ሙሠነድ IV 395፣ ኢብን ሂባን አል ሰሂህ II 316፣ አል-ሁማይድ አል ሙሠነድ II389.

ስራ መስራት ነው፡፡ ነብያችንን (ሠ.ዐ.ወ) የምንረዳውና የምናውቀው በሌላ በምንም ሳይሆን ልቦቻችንን ለሳቸው ፍቅር በማስገዛት ነው፡፡

አላህ ሆይ! ክንፎቻችንን በመንፈሳዊው ሠማይ ላይ ዘርጋልን!

አሚን፡፡